# አውራምባ ታይምስ

በመረጃ ቅርብ ይሁኑ

3ኛ ዓመት ቁጥር 129 ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዋጋ 5.00 ብር




16

## ወ/ት ብርቱካንን ማነው የሻራቸው?



«ረመዳን የጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦ እና የጥሞና ወቅት ነው»

በባራክ ሁሴን ኦባማ

ገፅ 7



«እዛ ማዶ - ሆ! ይታያል መኪና እማማ ዘነቡ - ሆ! የኛ ማዶና??»

በደረጀ ሀብተወልድ

ገፅ 8

«እምዬ ቀበሌ» ቻው ቻው...

ገፅ 9




4

የ1985ቱን የፕሬስ አዋጅ ተከትሎ ከ380 በላይ ለሆኑ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሕትመት ፍቃድ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በተከታዮቹ አምስት ዓመታት ብቻ ግማሽ ያህሉ የነጻ ፕሬስ ፍሬዎች በተለያዩ ጫናã ች ሕትመታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ:: ምርጫ 97ትን ተከትሎ እየሆነ ያለው ግን ፈጽሞ የተለየና የዘርፉን መፃኢ ዕጣ ወደ መቃብሩ የሚመራው ነው የሚለው ውብሸት ታዬ 17 ዓመታት ወደ ኋላ መለስ ብሎ በችግሩ መንስዔዎችና የመፍትሔ አማራጮች ላይ ቀጣዩን ጽሁፍ ያስነብበናል::

# እየከሰመ ያለው ፕሬስ መጻኢ ዕጣ

## አጠያያቂው የአቶ መለስ አዲስ የውጭ ፖሊሲ

3



የስዊድን ጠ/ሚኒስትር

## ፀረ - ሙስና ኮሚሽን የ45 ሺህ ባለስልጣናት ኃብትና ንብረት ሊመዘግብ ነው

የፌደራል ስነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን «የሙስና እንቅስቃሴን ለመግታት» ሲባል የባለስልጣናት፣ የሲቪል ሰርቪስ ኃላፊዎች ከነቤተሰቦቻቸው በአጠቃላይ የ45 ሺህ ኢትዮጵያውያን ሀብትና ንብረት መመዝገብ እንደሚጀምር አስታወቀ::

የኮሚሽኑ የስነምግባር ትምህርት እና ኮሚኒኬሽን የስራ ሂደት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ብርሀኑ አሰፋ በትናንትናው ዕለት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ የምዝገባው ሂደት የፊታችን ህዳር ወር እንሚጀምር አስታውቋል::

ከውጭ አማካሪ ተቋማት ጋር በመተባበር ስራው እንደሚከናወን የገለፁት አቶ ብርሀኑ ሂደቱ የግለሰቦችን የሀብት ምንጭ ከመመዝገቡ በፊት እንደሚጣራ አስታውቋል::

የኮሚሽኑ ሕግ ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑት አቶ ግርማ ወርቁ በበኩላቸው «የሀብትና ንብረት ምዝገባው በኃላፊነት ቦታ ላይ ተቀምጠው በዚህች አገር አንጡራ ኃብት ላይ በሚወስኑ ኃኃፊዎች ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ገልፀዋል::

አቶ ግርማ ጨምረው እንዳብራሩት ምዝገባው ከመንግስት ባለስልጣናትና ሚኒስትሮች ሌላ የዳኞች፣ አቃቢያነ ህግ፣ ትራፊክ ፖሊስና ሌሎች ውሳኔ ሰጪ የመንግስት አካላትን እንደሚያካትት አስረድተዋል::

የሀብትና ንብረት ምዝገባው የሚመለከታቸው ባለስልጣናት በምዝገባው ወቅት የቤተሰቦቻቸውን የገቢ ምንጭም ጭምር ማሳወቅ እንደሚጠበቅባቸውና ሀብትና ንብረታቸውን በማያስመዘግቡት ላይ ግን ህጋዊእርምጃ ከመውሰድ ባሻገር የተደበቀው ሀብትና ንብረት 25 በመቶው ለጠቋሚዎቹ በሽልማት መልክ እንደሚሰጥ ተገልጿል:: ኮሚሽኑ

ወደ ገፅ 19 ዞሯል

## 89 ኢትዮጵያውያን ኬንያ ውስጥ ታሰሩ

ኬንያ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገሬ ገብተዋል ያለቻቸውን 89 ኢትዮጵያውያን በቁጥጥር ስር ማዋሏን የኬንያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (KBC) አስታወቀ::

እድሜያቸው 18 እና 45 መካከል የሚገኙት እነዚህ ኢትዮጵያውያን ስራ ፍለጋ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለማቅናት በኬንያ በኩል ሲያቋርጡ በሳምንታት ውስጥ በቁጥጥር ስር መዋላቸው የተገለጸ ሲሆን ያለምንም ህጋዊ የጉዞ ሰነድ ወደ ኬንያ በመግባት ተወንጅለው ከትናንት በስቲያ ሐሙስ «ኪበራ» በተባለ የኬንያ ፍርድ ቤት መቅረባቸው ታውቋል::

ከሁለት ወር በፊትም በተመሳሳይ ሁኔታ 44 ኢትዮጵያውያን የታሰሩ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት እስካሁን በጉዳዩ ላይ የሰጠው ምንም አይነት ይፋዊ መግለጫ የለም::

## እንደ ኖርዌይ ብናድግ አይሻልም?

ገፅ 10

## የአክሲዮን ማሕበራት አዲስ የምዝበራ ሥልት

ገፅ 21

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አውራምባ ታይምስ
ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

የካቲት 2000 ዓ.ም ተመሠረተ

አውራምባ ታይምስ፡- በብሉ አርዝ ጀነራል ቢዝነስ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር ስር የሚታተም፤በፖለቲካዊ ና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቁጥር 020/2/6572/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው፡፡

ማኔጂንግ ኤዲተር
ዳዊት ከበደ

ዋና አዘጋጅ
ፍፁም ማሞ
(አድራሻ የካ ክ/ከ
ቀበሌ 03/04 የቤ.ቁ 1540)

ም/ዋና አዘጋጆች
ግዛው ለገሰ
ውብሸት ታዬ

አዘጋጅ
አቤል ዓለማየሁ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች

ሰናይት ግርማ
ኤልያስ ገብሩ
ሱራፍኤል ግርማ

ዓምደኞች
አበበ ቶላ
ትዕግስት ወንድሙ

ማርኬቲንግ ዳይሬክተር
ለውጡ ኃይሌ

ሽያጭና ማስታወቂያ
ሲሳይ ጌትነት

ኮምፒውተር ፅሁፍ
መቅደስ ፍስሐ

ግራፊክስ ኤዲተር
ነብዩ መስፍን
(0911 18 09 33)
E-Mail:nebiyou1st@yahoo.com

የዝግጅት ክፍሉ ስልክ
ስልክ፡- 0911 62 92 78
0911 62 92 82
0911 11 03 90
ፖ.ሣ.ቁ 19325
awrambatimes@gmail.com
http://www.awramba.com
የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
የቤት ቁጥር 181
ዋናው ፖስታ ቤት ጀርባ
ከአምሳደር ወደ ንግድ ማተሚያ
ቤት በሚወስደው መንገድ ላይ
ከተስፋ ድርጅት ፊት ለፊት

ብሉ ኤርዝ ጀነራል ቢዝነስኃላ/የተ/የግል/ማ
Blue Earth General Business PLC

አታሚ፡-
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡-አራዳ
ቀበሌ፡-17
የቤት፡-ቁ.984

## ርዕሰ አንቀፅ

# በድርጅታዊ ታማኝነት ብቻ ከሚደግፉ በአገራዊ ተቆርቋሪነት የሚሞግቱ ይሰሙ

«ኢትዮጵያ... ደገኛው ወደቆላ ይወርዳል፡፡ ቆለኛው ወደ ደጋ ይወጣል፡፡ ሕዝቡ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ውስጣዊ ፍልሰትንና ውሕደትን ማለትም የሕዝቦችን መስተጋብርና መወራረስን ፈጥሯል፡፡» - «የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሰረቶችና መሳርያዎች» የተሰኘው የታሪክ መድብል፣ የኢትዮጵያን የሥልጣኔ ምንጭነት አስመልክቶ ካሰፈራቸው ቃላት የተወሰኑት ከላይ የተመለከተትናቸው ናቸው፡፡ ትልቅ ቁም ነገር አዝለዋል ብለን እናምናለን፡፡ ቁም ነገሮችንም ልንፈትሻቸው ይገባል፡፡ በተለይ ካለንበት የማሕበረ-ፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እያሰናሰልን እንመርምራቸው፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ አገራችን የረዥም ዘመን የመንግስትና የሕዝብ ታሪክ ያላት እድሜ ጠገብ ምድር ናት፡፡ የሕዝቧ ባሕልና ወግም እንዲሁ ብዙ ምዕራፎች ያሉት ሆኖም እርስ በርሱ የተሳሰረና የራሱን ስርዓት ጠብቆ የኖረ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ደገኛው ወደ ቆላ የሚወርድበት ቆለኛው ደግሞ ወደደጋ የሚወጣበት የሕዝቦች መወራረስ ነው፡፡ ይህን ቁም ነገር ነው አለን ከምንለው የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ማሕበራዊ ፍልስፍና ወይም አስተሳሰብ ጋር እያሰናሰልን እንፈትሸው የምንለው፡፡ ይህን እንድንል ግድ የሚሉን ጉዳዮችም በየጊዜው ይከሰታሉ፡፡

ስለ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንና ማሕበረሰብ ውስጣዊ ውሕደት የበለጠ እያወቅን መሔዳችን በማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግብይቶችን ስኬታማ ያደርገናል፡፡ «ዴሞክራያዊ ስርዓትን እንገነባለን» ከማለታችን በፊት፣ «በቀጣዮቹ አምስት አመታት ውስጥ ድህነትን ከአገራችን እናስወግዳለን» ብለን ቃል ከመግባታችን በፊት እንዲሁም «ሕዝቡ የመረጠን ስለፈለገንና ሌሎች ፀረ-ሕገ መንግስት በመሆናቸው ነው» ብለን በድፍረት ከመደምደማችን በፊት ፍተሻችንን ልናስቀድም ይገባናል ስንል ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

ዴሞክራሲያዊም ሆነ ልማታዊ ስርዓት መሰረታቸው ሕዝብ ነው፡፡ ባሕላዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች የሚበለጽጉት አሁንም የኢትዮጵያዊነትን ሁለንተናዊ እሴቶች ለመመርመር ፈቃደኞች ስንሆንና ስነ ልቦናቸውን ስንረዳው ብቻ ይሆናል፡፡ በዚህ እሳቤ ወደ ሕዝቡ እንውረድ፣ ዜጎች አሰባስበን እናደራጅ እንዲሁም ግቦቻችንን እንተልም እንላለን፡፡ ይህን መርሕ ሚዛናችን አድርገን የፖለቲካ ልሂቃኖቻችን እያደረጓቸው ያሉትን እንቅስቃሴዎች ስንገመግም እስካሁን ያልናቸውን ነገሮች እንዲያጤኑት ግድ በሚላቸው አካሄድ ላይ እንዳሉ ለመመልከት ያስችለናል፡፡

እያጠናቀቅነው ያለነው የ2002 ዓ.ም የተለያዩ አንጋፋ ክንውኖችን አስተናግዶ ያለፈ ነው፡፡ አንዱን ክንውን ብቻ ነጥለን እንመልከተው ብንል በአገር አቀፍ ደረጃ ተካሂዶ የነበረውን ምርጫና ውጤቱን እናገኛለን፡፡ ውጤቱን ተከትሎም ተፎካካሪዎቹ ወገኖች አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን እያደረጉ ነው፡፡ እንቅስቃሴዎቹ ምን ይመስላሉ? ከተነጋገርንባቸው የኢትዮጵያነት ውስጣዊ መስተጋብሮች አንፃርስ እንዴት ይመዘናሉ? ደግሞስ ምን ቢደረግ ይበጃል? በሚሉት ላይ ጥቂት ነገሮችን ማለት እንሻለን፡፡

ከክንውኑ ጋር በተያያዘ በድህረ ምርጫው ተፎካካሪዎቹ ባነሷቸው አወዛጋቢ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ ሁነቶችን ለጊዜው እንተዋቸውና የሁለቱን ወገን ተሰላፊዎች ወቅታዊ እንቅስቃሴ ስናጤን በአዲስ የትግል ስልት እየተጓዙ እንደሆነ ሁለቱም ወገኖች ከሚሰጧቸው መግለጫዎች ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከምርጫው በኋላ በሁለት አበይት ጉዳዮች ላይ የተጠመደ ይመስላል፡፡ እነዚህም በገዢ ፓርቲነቱ መቀጠሉን ተከትሎ ለቀጣዮቹ ዓመታት እደርስባቸዋለሁ ብሎ በሚያስባቸው ግቦቹ ላይ ስትራቴጂዎቹን መንደፉና «የተለያዩ» የሕብረተሰብ ክፍሎችን እያወያየ መሆኑ ናቸው፡፡ ይደረስባቸዋል የተባሉት ግቦች ምንድናቸው? የማወያየት ሂደቱ ምን ይመስል ነበር? በምርጫ ማግስት የገዢ ፓርቲ ሚና ምን መሆን አለበት? ምንስ ይጠበቅበታል? የሚሉት የማይታለፉ መጠይቆች ናቸው፡፡

በመጀመርያ ይደረስባቸዋል የተባሉ ግቦችን አስመልክቶ አዎንታዊ ሆኖ መነሳት ተገቢ ቢሆንም ይህ አቋም የመነጨው ከስሜት ሳይሆን ከሳይንሳዊ እውቀት መሆን አለበት እንላለን፡፡

ይህ እውቀት ተግባራዊ ሊሆኑ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ የስኬት ተሞክሮዎች፣ ግባቸውን ያልመቱ ዕቅዶችን ጉድለት በመፈተሽና በማረም በዋንኛነትም የተገኘውን እውቀት ከሕዝቡ ውስጣዊ መስተጋብር ጋር በማዛመድ ሲተገበር ነው፡፡ እቅዶቹ ሊተገበሩ በሚችሉ ስትራቴጂዎችና በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ይሁኑ፡፡ ለዚህም «አዎ» እና «እሺ» ብቻ ከሚሉ የድርጅት ታማኞች ይልቅ እንዴት እና ለምን? ብለው በስነ አመክንዮ የሚሞግቱ የአገር ተቆርቋሪዎች እንደሚሻሉ አምኖ መቀበል ያስፈልጋል ፤ከብዙ ውድቀትም ያድናል፡፡

ሁለተኛው የማወያየት ሂደቱ ነው፡፡ ኢህአዴግ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እያወያየ መሆኑን ገልጿል፡፡ ውይይት መቼም በማንም መካከል መካሄዱ ጥሩና ተገቢ ነው፡፡ ስኬት አለ በሚባልበት፣ አሉታዊ ውጤት በሚመዘገብበትና በሌሎች ጊዜዎችም ሁሉ ውይይት ያስፈልጋል፡፡ ወደጎን ሊደረግ የማይገባው መርሕ ግን አለው፡፡ የውይይቱ አላማ የተለያዩ ወገኖች እምነትና ሃሳብ በነፃ ተንሸራሽሮ ውጤትና ለውጥ ማጎናጸፍን ግቡ ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ተወያዮቹ ያለጫና፣ በአገራዊ ስሜትና በመግቢያችን ላይ የተመለከትናቸውን የኢትዮጵያዊነት እሴቶች በጠበቀ መልኩ መካሄድ አለባቸው፡፡ ያለበለዚያ ለመፍትሔ ያሉት ንግግራዊ መስተጋብር እውነታን ለመሸሸግ፣ በሌሎች ላይ ለማሴርና ለታይታ ብቻ የተደረገ ስልታዊ ሽፍጥ ይሆናል፡፡ ተጎጂውም እንደሁልጊዜው ሁሉ የከበሩ እሴቶቹን አክብረው ሁለንተናዊ ልዕልናውን የሚጎናፅፉት ቁርጠኞች ያጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ይህም አጥብቀን ልንጠነቀቅበት የሚገባው አሳሳቢ አካሄድ ነው፡፡

በድህረ ምርጫ ገዢው ፓርቲ እያደረጋቸው ያሉ ውይይቶችን ባሕሪ ያጤኑ አንባቢዎቻችን ሊታረሙ ይገባቸዋል በሚል ካቀረቧቸው መረጃዎች አንዱ አመራሩ ሰብስቦ ከሚያነጋግራቸው ዜጎች አብዛኞቹ የራሱ ደጋፊዎችና አባላት የመሆናቸው አሳሳቢ አካሄድ ነው፡፡ ይህ አይነቱ የፓርቲ ደጋፊና አባላትን አወያይቶ «የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን» እንዳሳተፉ አድርጎ መግለጽ ወይም ማመን፣ የአገራችን ፖለቲከኞች ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እንደተጣባባቸው የቆየና በጣም በአስቸኳይ ሊስተካከል የሚገባ አጉል ብልጠት ነው፡፡

በእርግጥ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ከተለያየ የሕብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ ደጋፊና አባላትን ማወያየት ድርጅታዊ ጥንካሬን ሊፈጥር፣ በእቅድ አፈፃፀም ላይም ድጋፍና አጋርነትን ሊያስገኝ ይችላል፡፡ እውነተኛ ስኬት የሚገኘው ግን የተለያዩ ወገኖች ችሎታቸውን፣ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን ከቸሩ ብቻ ነው፡፡ ተወያዮቹ በሙሉ በአንድ ድርጅት የፖለቲካ አስተሳሰብ የተጠመቁ ናቸው የሚል እምነት ባይኖረንም ቅኝቱ ወደዚያው የሚያደላ መሆኑ ብቻ ተቃሎ እንዳይታይ ያደርገዋል፡፡


ኢህአዴግ የውሁዳንን አስተሳሰብ ለማስተናገድ በፍርሃት የሚንቀጠቀጥ የሚሆንበት የሥነ-አመክንዮ መሰረት የለውም፡፡ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጥንካሬውን ጠብቆ የሚቀጥለው የተለያዩ አስተሳሰቦችን ተቀብሎ በመመርመርና ሥነ-አመክንዮአዊ ሆኖ እስካገኘው ድረስ ለአማራጭ ሀሳብ ክብር በመስጠቱ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪየሚገኝ ጥንካሬና የበላይነት ምንጩ ምክንያት የለሽ ፍርሀትና በራስ ያለመተማመን ነው፡፡ መጨረሻውም የለየለት አምባገነንነት ነው፡፡ የኢትዮጵያዊነት ሥነ-ልቦና እና ውስጣዊ መስተጋብር ደግሞ ለዚህ መሰሉ ሽክም አንዳች ቦታ እንደሌለው እናውቃለን፡፡ ለዚህም ነው በድርጅታዊ ታማኝነት ከሚደግፉ ታማኞች ይልቅ በአገራዊ ተቆርቋሪነት የሚሞግቱ ይሰሙ! የምንለው፡፡

በአገራችን ተጨባጭ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሉባቸውን የአቅምም ሆነ በነፃነት የመንቀሳቀስ ችግር እንረዳለን፡፡ አካሄዳቸውን ያርሙ፣ ውስጣቸውን ይፈትሹ ወይም ለጉልብትናቸው ግብአት የሆኑ ስልቶችን ይሞክሩ የምንለውም በዚህ ዕሳቤ ላይ ሆነን ነው፡፡ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ አሉም፡፡ እቅም በፈቀደ መጠን ግን መወሰድ ያለባቸው ሰላማዊ የትግል እርምጃዎች መጀመር ያለባቸው ዛሬ ነው፡፡ የተቃውሞ ትግል ያስፈለገውና አማራጭነት የማይተካ መፍትሔ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡ ሁኔታው ፈጽሞ የማያላውስ እየሆነ በሄደ ቁጥር የበለጠ ሰላማዊ ተቃውሞ፣ የበለጠ ቀድሞ መንቃት ያስፈልጋል፡፡ እውነተኛውን ስኬት የሚያስገኘውም በዚህ መንገድ መጓዙና የማንነታችንን መገለጫዎች በጽኑ መሰረት ላይ አቆይቶ ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ በመቻል ላይ የተመካ ሲሆን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## VERBATIM


# ማን ምን አለ ?????



«አልጠቀምም ብልሽ ውሸት ነው የሚሆነው፡፡ ይህንን ያመጣው የሲዲ ዋጋ ከፍ ማለት መስለኛል፡፡»

**ድምፃዊ ፋሲል አለመወርቅ**


«አንተ ኮፒ የተደረጉ ሲዲዎችን አትጠቀምም?» በሚል ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ፡፡



«የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር በኮንፌዴሬሽን መኖር እፈልጋለሁ ካለም የሕዝቡ ውሳኔ ነው የሚሆነው፡፡»

**አቶ ዳንኤል ተወልደ**
**/የኤርትራ ብሔራዊ ኮሚሽን ጉባኤ ለዴሞክራሲ ቃል አቀባይ/**

ኢትዮጵያና ኤርትራ በኮንፌዴሬሽን ይዋሃዳሉ የሚባሉው ምን ያህል እውነት ነው? በሚል ከሰንደቅ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥይቄ የሰጡት ምላሽ፡፡



«ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግስታቸው አምኖ ምርጫ ቦርድ ሕጋዊ እውቅና የሰጠውን ፓርቲ 'ሕገ መንግስቱን ለመናድ የሚንቀሳቀሱ' ማለታቸው ሕገ መንግስታዊ አካሄድ አይደለም፡፡»

**ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ**
**/የመድረክ ከፍተኛ አመራር አባል/**

አዲስ ፕሬስ ጋዜጣ «የጠ/ሚ/ሩ ፍረጃ ተቃዋሚዎችን አስቆጥቷል» በሚል ካሰፈረው ዘገባ የተወሰደ፡፡



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# አጠያያቂው የአቶ መለስ አዲስ የውጭ ፖሊሲ



*በሌላ ቋንቋ፣ ምዕራብያውያን እየተጠናከረ የሄደውን አገዛዛቸውን ለመገዳደር፣ እርዳታን እንደ ተፅዕኖ ማሳደሪያ ለመጠቀም ማለም የለባቸውም ነው:: አቶ መለስ የራሳቸውን ቁጥር አምነው ለመቀበል ራሳቸውን እስከማታለል የሚደርሱ አስተዋይ አይደሉም ብዬ አላስብም:: ለአቶ መለስ ከልክ ሳለፈ በራስ መተማመን እውነተኛው መንስዔ፣ አል-ሻባብ ከፍተኛ ስጋት እየጋረጠ ያለ በመሆኑ እና ቻይና በአፍሪካ ውስጥ ያሳት ፍላጎት እየተጠናከረ ያለ መሆኑ፣ ምዕራብያውያን ከሚፈልጓቸው በበለጠ እነርሱ እርሳቸውን ይፈልጋሉ የሚለው ግምት ነው . . .*

**በጃዋር ሲራጅ መሀመድ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ ምዕራባዊያን ለሥልጣናቸው የሚያሰጉ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ማሻሻያዎችን እንዲወስዱ ጫና ለማድረግ የተፅዕኖ ኃይላቸውን መጠቀም እንደማይችሉ ለመጠቆም በብርቱ ሲጥሩ ቆይተዋል:: አንዳንዴ፣ ይህን «ኒዮ - ሊበራል» የተሰኘ ግፊት በመፃረር የራሳቸውን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት መሰሉን «ብሔርተኝነት» ይጠቀሙታል:: አቶ መለስ በቅርቡ ከጋዜጠኞች ጋር ያደረጉት ውይይትም፣ የዚህ ፀረ-ምዕራባዊያን አቋም በድጋሚ የተደመጠበት ነበር - ምንም እንኳን በተለየ የቃላት አጠቃቀም ቢሆንም:: ፊት ለፊት ነበር የሚናገሩት፤ ከመጠን በላይም በራሳቸው የሚተማመኑ ይመስሉ ነበር::

አቶ መለስ በዚሁ የጋዜጣዊ መግለጫ ቆይታቸው ነበር በስዊድን የኢትዮጵያ ኤምባሲ መዘጋቱን ያስታወቁት፤ በመቀጠልም የአገሪቱ ኢኮኖሚ በ14.9 በመቶ የሚያድግ በመሆኑ ኢትዮጵያ በጥቂት አምስት ዓመታት ውስጥ ከእህል እርዳታ ጥገኝነት ልትገላገል እንደምትችል ይፋ ተደረገ:: ይህ የአቶ መለስ እጅግ የተቀባባ አማላይ ንግግር፣ ተዓማኒነት ያለው ሙከራ ወይም የውጭ ፖሊሲ አቅጣጫዎች ለውጥ መሆን አለመሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ ያ እወጃ በአገሪቱ ውስጥ ባለ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖዎች የሚያሳድሩ ውጤቶች የሚኖረው ያልተጤነ ጥንቃቄ የጐደለው ስህተት ብዬ ነው የማምነው::

## «ስካንድኔቪያን» አታስፈልጉም!

ኢትዮጵያ ከስካንዲኔቪያ አገራት፣ በተለይ ከቀደምት የአገሪቱ የልማት አጋሮች መካከል ከምትጠቀሰው ስዊዲን ጋር ረዥም፣ ጠንካራ እና ውጤታማ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መስርታ ቆይታለች:: ነገር ግን ይህ ግንኙነት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየቀዘቀዘ መምጣቱ ተስተውሏል:: ያም ሆኖ የአቶ መለስ በስዊዲን የኢትዮጵያ ኤምባሲ መዘጋት በምክንያትነት ያቀረቡት «... በእኛ እና በስዊዲን መካከል አንዳች ትርጉም ያለው የልማት ትብብር ፕሮግራም የለም...» የሚለው እውነት ያልሆነና ኤምባሲው ለምን ተዘጋ ለሚለው ትክክለኛ ምክንያት አይደለም::

በመጀመሪያ፣ በኢትዮጵያና በስዊዲን መካከል በነበረው ከግማሽ ክ/ዘመን በላይ በቆየው የሁለትዮሽ ግንኙነታቸው ወቅት፣ የስዊድን ሕዝብና መንግስት ውጤታማ የልማት ድጋፍ በማቅረብ ይታወቃሉ:: የኢትዮጵያን የግብርና ዘርፍ ዘመናዊ የማድረግ ግብ የነበረውና ግንባር ቀደሙን የጭላሎ የግብርና ልማት ሕብረት ምስረታ ፕሮጀክት እኤአ በ1967 እውን እንዲሆን በገንዘብ ድጋፍ ያደረገው የስዊዲን ሕዝብ ነበር:: መንግስታቸው በግብርና ልማት ስኬትን እንደተቀዳጀ አድርገው እንደማወጃቸው ጠ/ሚኒስትሩ ስዊዲንያውያን ለኢትዮጵያ ግብርና «ዘመናዊነት» ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እውቅና መስጠት ነበረባቸው:: በሥልጣን ቆይታቸው ወቅትም እንኳን የስዊዲን ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (SIDA)፣ በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ ኮሚሽን እና ዩኒቨርስቲዎች አማካኝነት ለምርምር ያደረገው ድጋፍ ላቅ ያለ ነው:: ስለዚህም በአገራቱ መካከል ያለው የንግድ ግንኙነት አመርቂ ላይሆን ቢችል እንኳን፣ ትርጉም ያለው የልማት ትብብር የለም ብሎ መደምደም መሰረት የለሽ ነው::

በተጨማሪ፣ «... በብራዚል ኤምባሲ የለንም:: ብራዚል (በኢኮኖሚ እየተጠናከረች ያለች ግዙፍ አገር ናትና በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለንን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እየገመገምን ነው...» በማለት ነበር ጠ/ሚኒስትሩ የኤምባሲው መዘጋት ዲፕሎማሲያዊ የትኩረት አቅጣጫ ወደኢኮኖሚያዊ ትብብሮች መለወጡን በምክንያትነት ያመላከቱት:: ዘርፈ-ብዙ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች የመኖራቸው እሳቤ ወሳኝ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፣ ሌላኛውን ለማስደሰት አንደኛውን መዘጋት ግድ ታአይደለም:: እርግጥ ነው ነጥቡ ከሁለቱም አገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ማካሄድ አይቻለንም የሚለው አይደለም - በእርግጠኝነት እንችላለን:: እዚህ ጋር የብራዚል ጉዳይ የቀረው እንደቀላል ምክንያት ነውና፣ ለአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅሞች ተቀባይነት ለሌላው ውሳኔ ጉልህ አምክንዮአዊ ገጽታ የሚሰጠው ነው:: በብራዚል ኤምባሲ ለመክፈት በስዊዲን ያለው ኤምባሲ የግዴታ መዘጋት አለበት የሚለው አሳማኝ ያልሆ ብቻም ሳይሆን፣ በስዊዲን ያለው ኤምባሲ ግልጋሎት የሚሰጠው ለሁሉም የስካንዲኔቪያ አገራት (ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ አይስላንድ እና ኖርዌይ) መሆኑ ሲጤን በተጨማሪ ወደተጣረሰ ድምዳሜ የሚያስከትል ነው የሚሆነው:: ስለዚህም፣ የዚህ ኤምባሲ መዘጋት ኢላማ ስዊዲን ብቻ ሳትሆን የተቀሩት የስካንዲኔቭያ አገራትም ጭምር ናቸው:: የእነዚህ አገራት ጠቅለል ያለው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦቸው የሚካድ አይደለምና የኤምባሲውን የመዘጋት ውሳኔ ሊያብራራ የሚችለው ፖለቲካዊ አለመግባባት ብቻ ነው::

አንዳንድ የስካንዲኔቭያ አገራት፣ በኢትዮጵያ እየተሸረሸረ ባለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ከረር ያለ አቋም መያዛቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፤ እናም ባለፉት አመስት ዓመታት ውስጥ አቋማቸውን ባልተሸፋፈነ መልኩ ጠበቅ አድርገውታል:: የአቶ መለስ ፓርላማ፣ በአገሪቱን ያሉ በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ የሚገታ «የሲቪል ማሕበራት አዋጅ» ካጸደቀ በኋላ ነበር በተለይ ቁጣቸውን የገለፁት:: እናም አቶ መለስ የመያዶቹን እንቅስቃሴ በዚህ መልኩ ሽባ ካደረጉ በኋላ የስካንዲኔቭያ አገራት ለኢትዮጵያ እርዳታ ለመስጠት ከፈለጉ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ከመንግስት ጋር ቁርኝት ባላቸው መያዶች አማካኝነት እንዲያቀርቡ አሳወቋቸው፣ ምንም እንኳን አገራቱ ያንን ባይቀበሉም:: በተጨማሪ፣ እንደሚታመነው፣ የአውሮፓ ሕብረት ፕሬዝዳንታዊ መቀመጫ ስዊዲን በያዘችበት ወቅት ሕብረቱ አቶ መለስ ዴሞክራሲያዊ ማሻሻያዎች እንዲያደረጉ ጫና እንዲያሳድር ጥረት አድርጋ የነበረ ሲሆን ይህም ተግበሯ አገሪቱ የአቶ መለስ ቀንደኛ ጠላቶች ዝርዝር ውስጥ እንድትሰፍር ያደረጋ ነው:: አቶ መለስ ከአቋማቸው ውልፍት እንደማይሉ ምርጫ 2002 ካረጋገጠ በኋላ፣ የአገራቱ ግንኙነቱ ለየለት፤ እናም ለዚህ ነው አሁን አቶ መለስ ፍቺውን በሰማነው መልኩ ይፋ ያደረጉት::

የስካንዲ[illegible]ን ከኢትዮጵያ ማስወጣት፣ አቶ መለስ ለማንኛውም የውጭ ጫና የማይመለሱ መሆናቸውን በተጨማሪ ለምዕራብያውያን ለመጠቆም እንደ አንድ ቀሽም መንገድ የሚያገለግላቸው ነው:: በአገራት ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት ባላቸው አቋምና በቀጠናው ውስጥም እዚህ ግባ በማይባል ወሳኝ ብሔራዊ ጥቅም ያላቸው በመሆኑ የሚታወቁት አገራት፣ በሥልጣናቸው ጣልቃ የመግባታቸው እድል ዝቅተኛ መሆኑን አቶ መለስ ያውቁታል:: ምናልባት፣ ጉዳት የማድረስ አቅሙ እምብዛም በሆነ ኢላማ ላይ መሰል ጠንካራ እርምጃዎች መውሰድ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሌሎች የበለጠ ኃይለኛ ለሆኑ ምዕራብያውያን ኃይሎች ሰብሰብ እንዲሉ መልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ ሊሆንም ይችላል:: ይህን ማስጠንቀቂያ የሚያጠናክረው፣ ኢኮኖሚው እጅግ ፈጣን በሆነ መልኩ የሚያድግ በመሆኑ፣ «ተስፋችንና የምንጠብቀው በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ራሳችንን ለመመገብ ብቻ ሳይሆን ወደውጭ ኤክስፖርት ለማድረግ የሚያስችለን በቂ ምርት እናመርታለን» የሚለው መግለጫ ነው:: በሌላ ቋንቋ፣ ምዕራብያውያን እየተጠናከረ የሄደውን አገዛዛቸውን ለመገዳደር፣ እርዳታን እንደ ተፅዕኖ ማሳደሪያ ለመጠቀም ማለም የለባቸውም ነው:: አቶ መለስ የራሳቸውን ቁጥር አምነው ለመቀበል ራሳቸውን እስከማታለል የሚደርሱ አስተዋይ አይደሉም ብዬ አላስብም:: ለአቶ መለስ ከልክ ላለፈ በራስ መተማመን እውነተኛው መንስዔ፣ አል-ሻባብ ከፍተኛ ስጋት እየጋረጠ ያለ በመሆኑ እና ቻይና በአፍሪካ ውስጥ ያላት ፍላጎት እየተጠናከረ ያለ መሆኑ፣ ምዕራብያውያን ከሚፈልጓቸው በበለጠ እነርሱ እርሳቸውን ይፈልጋሉ የሚለው ግምት ነው . . . ::

## ምስራቁን ከምዕራቡ የማስበለጥ ጨዋታ

እንደብራዚል ካሉ በኢኮኖሚ እየተጠናከሩ ካሉ አገራት ጋር ያለውን ቁርኝትን ወደማጠናከር ትኩረት በማድረግ፣ አቶ መለስ ከምዕራቡ የሚያጡት ምንም ይሁን ምን ከምስራቁ፣ በተለይ ከቻይና እንደሚያገኙት ነው እያመላከቱ ያለው:: በአንድ በኩል አቶ መለስ ትክክል ናቸው፣ ማለትም ኢኮኖሚያዊ እድገትን እበተመለከተ፣ በማደግ ላይ ካሉ ኢኮኖሚዎች ጋር ጥምረት መፍጠር የተሻለ አማራጭ ሊሆን ይችላል:: አፍሪካን በተመለከተ ምዕራቡ አሁንም ከአባታዊነቱ ያልተላቀቀ ሲሆን አንድም የምዕራቡ አገር ከኢትዮጵያ ጋር እውነተኛ የሆነ የሁለትዮሽ ጥቅም የሚያስጠብቅ ጥምረት ውስጥ ለመግባት አይፈልግም:: በተጨባጭ፣ አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ተቀዳሚ ትኩረት፣ ብቸኛው ባይሆን እንኳን፣ አገሪቱ ለእርሷ ክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ደህንነት ያላት ስትራቴጂካዊ መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ነው:: አገሪቱ ከድህነት እና አስከፊ [illegible]ንድትላቀቅ ድጋፍ በመስጠት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ከመጫወት ይልቅ፣ ሁሌም አሜሪካ የምትፈልገው በእርዳታ ጥገኛ፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተለዋጭ አገዛዞች የራሷን የደህንነት ጥቅሞች ማራመድ ነው:: ለዚያም ነው ለምሳሌ ተጨባጭ እድሎች በ1990 እና በ2005 እያሉ ለእውነተኛ ፖለቲካዊ ለውጥ ግፊት ያላደረጉት:: እናም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድህነት ለመውጣት በምዕራቡ ላይ መተማመን አይችልም፤ እናም ምርቷን ተጠቃሚ ገበያ አድርጋ አፍሪካን የመለወጥ ዓላማ ያላት እየተመነደገች ያለችው ቻይና ብቅ ማለቷ በጣም የተሻለው አማራጭ ሊሆን ይችላል::

ያም ሆኖ፣ ከምስራቅ አገራት ጋር ለመወዳጀት ኢትዮጵያ ከምዕራብያውያን ጋር መለያየት አለባትን? መሆን አለበት ብዬ አላምንም:: አቶ መለስ እያሰቡ ያሉት ሥልጣናቸውን ከዓለም አቀፍ ግፊት ለመነጠል ቻይናን በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ መቆመር እችላለሁ የሚል ነው:: ሆኖም፣ አቶ መለስ የመሰል ስትራቴጂን ውጤት ከልክ አግዝፈው ነው እያስቀመጡ ያሉት፤ በዚህም ምክንያት የአገሪቱን ጥቅም እና ሲከፋም ምናልባት በራሳቸው ሥልጣንም ላይ ነው አደጋ እየጋረጡበት ያለው::

መጀመሪያ፣ ኢንቨስትመንት ለኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ ቢሆንም፣ ያ ገና መሰላሉን መውጣት ለጀመረ አንድ ኢኮኖሚ በቂ አይደለም:: ለወደፊቱ መጪ ጊዜ፣ የገንዘብና የሰብዓዊ እርዳታ የኢኮኖሚውን እድገት ቀጣይ ለማድረግ ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው:: የውጭ እርዳታ እንደቀጠለ ማቆየት፣ የኢንቨስትመንት ገቢዎች ሰብዓዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከሚውሉ ይልቅ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ተመልሰው እንዲውሉ ለማድረግ ይረዳል:: በተጨማሪ፣ ካለ እርዳታ፣ በኢኮኖሚው ላይ ሊደርስ የሚችል ያልተጠበቀ የውጭ ንዝረት ወደከፍተኛ ቀውስ ሊያመራ ይችላል:: ከምዕራቡ የሚደረግባት ግፊት ኢትዮጵያ አንደኛውን ወገን እንድትመርጥ የሚያስገድዳት ጥንካሬ መቼም ይኖረዋል ብዬ አላምንም::

ሁለተኛ፣ የተወሰኑ የአቶ መለስ ደጋፊዎች፣ ከማንኛውም የአሜሪካ ጥቃት ቻይና የአገዛዙ አስተማማኝ ጠባቂ (ወይም ተከላካይ) ልትሆን ትችላለች ብለው ይገምታሉ:: ይህንንም ግምታቸውን ለማጠናከር፣ ከምዕራብያውያን ጋር የለየለት ተቃርኖሽ ቢኖረውም፣ ለአስርት ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት የቻለውን የበርማን (በአሁኑ መጠሪያዋ መየንማር) አገዛዝ ይጠቀማሉ:: ሆኖም ይህ የለየለት የተጣረሰ ግንዛቤ ነው:: የቻይና የውጭ ፖሊሲ እጅግ በተጨባጭነት ላይ እንጂ በርዕዮተ-ዓለም ላይ አይደለም የተመሰረተው:: ኢኮኖሚያዊ ትርፍ ዋነኛ ግባቸው ነው፤እ ናም የፖሊሲ ውሳኔዎቻቸው በትርፍ-ኪሳራ ቀመር ላይ የተመሰረተ ነው::

የቻይና ኢኮኖሚ ከየትኛውም አገር በበለጠ ከአሜሪካ ኢኮኖሚ ጋር የተሰናሰለ ነው:: የምዕራብያውያን ጥቅሞች አደጋ በተጋረጠባቸው በአንድ ጉዳይ ላይ፣ ድሃዋን ኢትዮጵያ ቻይና እንድትታደጋት መጠበቅ የለየለት የምኞት አስተሳሰብ ነው የሚሆነው:: የመየንማር አገዛዝ እስከአሁን ለመቀጠሉ ምክንያቱ የቻይና ጥበቃ ሳይሆን አገዛዙን በተመለከተ ከአሜሪካ ጠንካራ አቋም ባለመኖሩ ነው፤ ለዚያም ምክንያቱ በአገሪቱ ላይ ያላቸው ኢኮኖሚያዊም ሆነ የደህንነት ጥቅሞች እዚህ ግቡ የሚባሉ ባለመሆናቸው ነው:: በሌላ በኩል፣ አሜሪካ ኢትዮጵያን እንደ አንዷ ዋነኛ የብሔራዊ ደህንነት አጋርቿ አድርጋ ነው የምትመለከታት:: አሁን ድረስ አሜሪካ የአቶ መለስን የተራውን ሕዝብ ጥቅም ጠባቂነት ንግግር ትኩረት ሰጥታ አትወስድም:: ሆኖም አቶ መለስ፣ ምናልባት በሌሎች አገራት መሪዎች ሊደረግ የሚችልን የእርሳቸውን ዱካ የመከተል እድል ለመከላከል፣ የሆነ አካል ለጣልቃ ገብነት አንድ ምክንያት ለማቅረብ የመቻሉን ሰፊ እድል አሳንሰው ሊመለከቱት አይገባም:: መሰል እርምጃ ለመውሰድ እርሳቸውን ድምፅ መስተካከል መጠበቅ ላይኖርባቸው ይችላል:: ያም ሆኖ ከምንም በላይ ቻይናም ሆነች አሜሪካ ኢትዮጵያን ማን ይመራታል የሚለው ያን ያህል አያስጨንቃቸውም:: ስጋታቸው በቤተ-መንግስት የሚውለው የትኛውም አካል አጋራቸው የመሆኑ ጉዳይ ነው፤ እናም በእነዚህ ወቅቶች ያን እድል የሚያገኝ እያንዳንዱ ሰው ከተባለው በስተቀር ትንሽ ምክንያታዊ ድጋፍ ነው የሚኖረው::


የእኔ ፍርሀት አቶ መለስ በ«እሺ ጌታዬ» የተከበቡ አምባገነኖች የራሳቸውን ፕሮፓጋንዳ ማመን በሚጀምሩበት ደረጃ እየደረሱ ሊሆን ይችላል የሚለው ነው:: እውነታው እንደዛ ከሆነ፣ የእርሳቸው የቅርብ ጊዜ እርምጃዎቻቸው ለውድቀት ሊዳርጋቸው የሚችል ነውና አገሪቱንም ከተመሳሳይ ውድቀት ፈጣሪ ይጠብቃት::

*/ጃዋር ሲራጅ መሀመድ፣ የፖለቲካ ተንታኝ ሲሆኑ በዋሽንተን ዲ.ሲ በግል የምርምር ስራ ላይ ይገኛሉ/*

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# እየከሰመ ያለው



በውብሸት ታዬ ◆




«በርካታ ዴሞክራቲክ መንግስታት የቅድመ ህትመት ምርመራን ሲያስቀሩ የፕሬስ ሥራ ፈቃድ» ሰነድን ያሳስፈላጊነትን በማጎናፀፍ ጭምር ነው:: በእነዚህ አገራት ያለውን አሰራር ስንፈትሽ የፕሬስ ተቋማትን በኃላፊነት የመስራት አቅም የሚያጎለብትና ሙያዊ ተልዕኳቸውን እንዲወጡ የሚያበረታታ ቢያንስ እንቅፋት የማይሆን አካሄድ ይታያል::»

**የብሮድካስት ሚዲያን በተመለከተ እስካሁን ያለው ሁኔታ የመንግስትን ሞኖፖሊ የሚያመለክት እንደሆነ የሚገልፁት የሕግ ባለሙያው በቅርብ ጊዜያት ይህን ዘርፍ በከፊልም ቢሆን «ፕራይቬታይዝ» አድርጎ ለመቆጣጠር ሕጎች ቢወጡም በተጨባጭ «የግል ብሮድካስት ሚዲያ በኢትዮጵያ አልተጀመረም» የሚያሰኝ ነው ይሉታል::**

የስነ መንግስት አጥኚዎች በአንድ አገር ውስጥ ስላለው የፖለቲካ ስርዓት፣ ሕገ መንግስታዊ ስርዓትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመዘን ከሚረዱት ግብአቶች ዋንኛው የመገናኛ ብዙኃኑ ያላቸው ነጻነትና ከአንድ ክበብ አልፈው የማሕበረሰባዊ ተደራሽነታቸው ደረጃ ነው ይላሉ:: «ኢንቪዥን » የተሰኘ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በቅድመ ምርጫ 97 አዘጋጅቶት በነበረው የውይይት መድረክ ላይ አንድ የሚዲያ ባለሙያ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገሩ «የማሕበረሰብ ሁለንተናዊ ፍላጎቶች በወግ እንዲመሩ ነፃ ፕሬስ የማዕከላዊነት ሚና መጫወት አለበት:: ይህን ሚናውን እንዲወጣ የሚደረጉት እንቅስቀሴዎች በእርግጥም ምን አይነት የፖለቲካ፣ የሕገ መንግስትና የዴሞክራሲ ስርዓት ደረጃ ላይ እንዳለን ያመለክታሉ::» ብለው ነበር::

በአገራችን የመገናኛ ብዙኃን ስርዓታማ በሆነ ሂደት ውስጥ ነፃው ፕሬስ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮችን በጎለበተ የመረጃ ፍሰት እንዳይመራ የነበሩበትና ያሉበት የቁጥጥር ዘዴዎች ግን ተልዕከውን እንዳይወጣ ማነቆ እንደሆኑበት ይገለጻል:: ቀደም ሲል በተጠቀሰው የውይይት መድረክ ላይ በአገራችን የነፃ ፕሬስ እድገት «መሰናክል የሆኑ» በሚል ባለሙያው በአጽንኦት የገለፁት ለዚህ ተግባር ሲባል የተቋቋሙ አካላት ባደረጉት ርብርብ ዘርፉ ሊጫወት የሚችለውን አይነተኛ ሚና እንዳመከነውና ያለበትን ታሪካዊ የዕድገት ደረጃም በእንጭጩ እንዳስቀረው ነው::

ለዚህ ፊቸር ሲባል ያነጋገርናቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን መምህር የሆኑት ረዳት ፕ/ር መኩሪያ መካሻ በዓለም አቀፍ ደረጃ የፃው ፕሬስ የእድገት ሂደት ተመሳሳይ ባሕሪ እንዳለው ይገልፃሉ:: «በየትኛወም ዓለም ያሉ የነፃ ፕሬስ አጀማመር ክስተቶችን ስንመረምር የየራሳቸው መገለጫዎች ያላቸው ችግሮችን እናገኛለን:: ለግጭት መንስኤ ከሆኑ የጠራ መስመር የሌላቸው አሰራሮች አንስቶ በሂደት የሰከነ የጋዜጠኝነት ፍሬ እስከሚገኝበት የጉዞ ምዕራፍ ውስጥ ተመሳሳይ አካሄዶች ይስተዋላሉ:: በዚህ ሂደት ውስጥ ሙያዊ ብቃቱን ለመጠበቅ ተገቢውን እገዛና ክትትል ይሻል::» ካሉ በኋላ በዚህ ሂደት ውስጥ የነፃ ፕሬስ ተቋማቱ ሙያዊ ብቃታቸው በእድገት ጎዳና ላይ የሚጓዝ እስከሆነ ድረስ የተመሳሳይ ሃሳብ ወይም ፖለቲካዊ አመለካከት ደጋፊ ይሁኑ ብሎ መጠበቅ እንደማይገባ ያስጠነቅቃሉ:: ወደአገራችን የነጻ ፕሬስ ፈተናዎችና ተያያዥ ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት ታሪካዊ እድገቱን አስመልክቶ የተደረጉ ጥናታዊ ዳሰሳዎችን እንመልከት::

## ጅማሬው...

በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነትና የሶሽዮሎጂ ፕሮፌሰር የሆኑት ጀሹዋ አላን የመገናኛ ብዙኃንን በተለይም የሕትመት ሚዲያዎችን አስመልክቶ ባደረጉት ጥናት «በረዥም የክ/ዘመናት ፍሰት ውስጥ ሳያቋርጥ እድገት ያሳየ መስክ ነው::» ሲሉ ገልጸውታል:: በማሕበረሰብ እድገት ጥናት ውስጥ እጅግ ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱም ይናገራሉ:: አውሮፓውያን ደግሞ በመካከለኛው ዘመን ኪነ ጥበብ፣ አርክቴክቸር፣ ስነ ፅሁፍና ባሕላቸው እንዲበለፅግ ተጠቅመውበታል:: የዓለም ጋዜጦች ማሕበር (WAN) ይፋ ያደረገውና ለህትመት ሚዲያው እንደመሰረት ድንጋይ የሚቆጠረው በ59 ዓ.ዓ. የጁሊየስ ቄሳር የሕዝብ ግንኙነት ባሕሪ ያለው ተግባር የተመዘገበ ጥንታዊ «ጋዜጣ» ተብሏል:: ይህ «አክታ ዲዩርና» ተብሎ የሚታወቀው የመረጃ መለዋወጫ በትልልቅ ነጭ ሰሌዳዎች ላይ የተፃፉ መልዕክቶችን በዋና ዋና ከተማዎች አደባባይ ላይ በመስቀል የሚከናወን ነበር:: ማሕበሩ የመልዕክቶቹ ይዘት የተለያዩ አላማዎችን የሚያካትት እንደሆነ በመረጃው አስፍሯል:: ከእነዚህም ውስጥ በቄሳሩ ግዛት ወሳኝ የሆኑ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች፣ አዋጆችንና ቀጣይ ክንውኖችን ያካትታል ብሏል:: የፍርድ ሂደቶችና አፈፃፀሞች፣ እንዲሁም ወታደራዊ ዘመቻዎች በዚህ ከሁለት ሺህ አመት በላይ እንዳስመዘገበ የሚነገርለት «ጋዜጣ» ላይ በአምድነት ይሰፍሩ ነበር::

በ8ኛው መቶ ክ/ዘመን በእጅ ተፅፎ ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ይቀርብ የነበረው «ካዩና» ጋዜጣ በቻይና (ቤጂንግ) ለንባብ የበቃው የመጀመርያው የዘመናዊነት ይዘት ያለው የጋዜጣ ሥራ ተደርጎ ተመዝግቧል:: እንዲህ እያለ የቀጠለው የጋዜጣ እድገት በ1447ቱ የጆሃን ጉተንበርግ የጽህፈት መሳርያ መፈልሰፍ ወደ ልዩ ምዕራፍ ተሸጋገረ::

ፕ/ር ጀሹዋ የጉተንበርግ አዲስ ፈጠራ የዓለምን የምልከታ አቅጣጫ ከመወሰኑም በተጨማሪ ከ14ኛው መቶ ክ/ዘመን እስከ 17ኛው መቶ ክ/ዘመን ለተካሄደው የአውሮፓውያን የ«ህዳሴ» (Renaisance) እንቅስቃሴ ፈጣን መልስ አስገኝቷል ይላሉ:: የማሽኑን ሥራ መጀመር ተከትሎ በአውሮፓ ለንባብ ይበቁ የነበሩት ጋዜጦች በንግድና ኢንቨስትመንት ለተሰማሩት ወገኖች አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ አህጉራዊ ሚናቸውን ይወጡ እንደነበር ያስታወሱት እኒህ ምሁር አገሮቻቸው በጦርነት ላይ በሆኑበት ወቅት ደግሞ የፕሮፓጋንዳ እና ስሜት ቀስቃሽ ዘገባዎችን ያሰራጩ ነበር ሲሉ በጥናታቸው አመልክተዋል::

«ጋዜጣ» የሚለው ስያሜ በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን አጋማሽ የቬኔሽያን መንግስት (ኢጣሊያ) ያሳትመው የነበረው ጋዜጣ ይሸጥበት የነበረው የገንዘብ አይነት /ሳንቲም/ ሲሆን ከመቶ አመት በኋላ የመጀመያው የፈረንሳይ ጋዜጣ ለንባብ ሲበቃ ይህን ስያሜ በርዕስነት/Flag/ ለመጠቀም ችሏል::

## ወርቃማው የህትመት ዘመን እና ኢትዮጵያ

በዓለም የጋዜጦች እድገት ታሪክ ውስጥ «ወርቃማው ዘመን» ተብሎ የሚታወቀው ከ1890-1920 ያለው ጊዜ ሲሆን ይህ ወቅት በአገራችን የጋዜጣ አጀማመር ላይም የራሱን አሻራ እንዳሳረፈ ጥናቶች ያመለክታሉ:: ከዚህ ወቅት ጥቂት ቀደም ብሎ (በ1880) በጋዜጦች ላይ ፎቶ ግራፍን መጠቀም መጀመሩ በመስኩ እድገት ላይ ተጨማሪ እርምጃ ተደርጎ የተወሰደ ከመሆኑም በላይ ጆሴፍ ፑሊትዘር፣ ዊሊያም ራዶልፍና ሎርድ ኖርክሊፍ «የጋዜጣ ኢምፓየር» የፈጠሩበት ምዕራፍ ተደርጎ ይጠቀሳል:: ኢትዮጵያና ጋዜጣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁትም በዚህ ወቅት እንደሆነ ይገመታል::

ደራሲና ጋዜጣኛ ጳውሎስ ኞኞ በ1984 ዓ.ም የካቲት ወር ባሳተመው «ዳግማዊ አጤ ምኒልክ» መጽሐፍ ላይ እንዳሰፈረው ንጉሰ ነገስቱ ስለ ጋዜጣ ምንነት ቢያውቁም ስራውን የሚያከናውንላቸው ሁነኛ ሰው በማጣታቸው ምኞታቸው ሳይሳካ ብዙ ጊዜ ቆይተዋል:: በ1888 ዓ.ም ሰኔ ወር የሐማሴን ተወላጅ የሆኑት ገ/እግዚአብሔር ጣለያኖችን ከድተው ሐረር ልዑል ራስ መኮንን ዘንድ መግባታቸው ሁኔታዎች በራሳቸው ጊዜ መስመር መያዝ እንደጀመሩ መመልከት ይቻላል:: «ሰውየው» ለኢትዮጵያ ስላላቸው ፍቅር ይገልጹ እንደነበር የተዘገበ ሲሆን ዘመናዊ አስተሳሰቦችንም ያራምዱ የነበረ ሲሆን አጤ ምኒልክ የራስ መኮንንን ሳይጠበቅ መሞት አስታከው እኒህን ዜጋ በክብር ወደራሳቸው ወሰዷቸው:: በሐረር እያሉ ይናገሯቸው የነበሩትን ሳይንሳዊ ድጋፍ ያላቸው ፍልስፍናዎች በስፋት የሚያስተዋውቁበት ዕድልም ተፈጠረላቸው::

ንጉሰ ነገስቱ አቶ ገ/እግዚአብሔር ዕውቀታቸውን በወረቀት እየፃፉ ለመኳንንቱ እንዲያድሉ ትዕዛዝ ሰጧቸው:: በእጅ የተፃፈ ጽሁፍ በመደበኛነትም ልክ እንደ ጋዜጣ በምኒልክ ግብር ላይ ይታደል ነበር:: ንጉሰ ነገስቱ በስራው ቢደሰቱም በቁጥሩ ማነስ ይበሳጩ እንደነበር ጳውሎስ ኞኞ በታሪካዊ መድብሉ አስፍረታል:: ካባዲአስ የተባለ ግሪካዊ ባቀረበላቸወ ምክር በመታገዝ «የጋዜጣ መልክ ያለው»፣ በእጅ የሚፃፍ 24 ገጽ ለመኳንንቱ ይደርስ የነበረ ሲሆን ይህ ለፕሬሱ እድገት አይነተኛ ሚና የነበረው እንቅስቃሴ በመኳንንቱ እንዳልተወደደ ይነገራል:: አጤ ምኒልክ ግን የህሊናን ልዕልና በሚያለክት አገላለጽ ለጋዜጣው «አእምሮ» የሚል ስያሜ ሰጡት::

## በ100 አመት «ዳዬ»

ኮፒ ማድረጊያ መሳሪያ ተገኝና የ«አዕምሮ» ሳምንታዊ ቅጅ ብዛት 200 ሆነ:: አጤ ምኒልክ ደስ አላቸው:: ግሪካዊውን አበረታቱት:: የማተሚያ ማሽንም ለማምጣት ተስፋ ሰጡ:: የእጅ ፅሁፉን የማባዛቱ ስራ በ1895 ዓ.ም ቆመ:: አጤ ምኒልክ በ1898 ኢ.ዴ.ልቢ. የማተሚያ መኪና እስኪያመጣላቸው ድረስ ቃላቸው ተግባራዊ አልሆነም ነበር:: «ጉህ» በማተሚያ ማሽኑ በመጠቀም በ1900 ዓ.ም ሐምሌ 17 ታትሞ የወጣ የመጀመሪያ ጋዜጣ ለመሆን በቃ::

«ዳግማዊ አጤ ምኒልክ» መጽሐፍ እንደሚያስረዳው ከሆነ በ1905 ዓ.ም «አእምሮ» ጋዜጣ በማተማያ ቤት እየታተመ ስራውን ዳግመኛ ጀምሮ ነበር:: እንዲህ እንዲህ እያለ ነው ... ከመቶ ዓመት በኋላም ዛሬም «ዳዬ» የሚለው የጋዜጣ ህትመት የጀመረው::

ማርገሪ ፐርሐም የተባለ ጸሃፊ «...በዘመናዊው

### ማረሚያ

አል-ሸባብ በአርማነት የሚጠቀምበት ምስል በባለፈው ሳምንት ፊቸር ላይ መስተናገዱ ይታወሳል:: ሆኖም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን «አርማው የቅዱስ ቁርዓንን ታላቅ መልእክት የያዘ በመሆኑ አል-ሸባብ ለአሉታዊ ተልእኮው ቢጠቀምበትም እናንተ ግን ያንን ማስተናገድ አልነበረባችሁም» ሲሉ ምክር አዘል ግሳጼ ሰንዝረውብናል:: እኛም ግሳጼውን ከታላቅ አክብሮት ጋር መቀበላችንን እየገለጽን በተፈጠረው አጋጣሚ የተከፉ ሙስሊም ወገኖቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን::

*ረመዳን ከሪም*

የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል

**ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ**

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ፕሬስ መጻኢ ዕጣ

*በእርግጥ በሽብርተኝነት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ወንጀሎች ማበረታታት እራሱ እንደወንጀል የሚቆጠርባቸው ሁኔታዎች አሉ:: የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁም የሽብርተኝነት ድርጊትን ስለማበረታታት የሚለው አለው:: ሆኖም በአንቀጽ 6 የሰፈረው ከሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ለይቶ የፕሬስ (የህትመት) ውጤቶችን በቀጥታ ይመለከታል::*

ዓለም አእምሮው ክፍት ነው::» ሲል በአክብሮት ያወደሳቸው ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የስርዓቱ ባለሟሎችና የኃይማኖት መሪዎቹ/ቀሳውስቱ/ «ጥበብ ሁሉ የሰይጣን ስራ» እየተባለ ቅቡልነት ሊያገኝ ባይችልም የነበሩበትን ተግዳሮቶች ሁሉ እየተጋፈጡ በማስተማርና በማሳመን ቀስ በቀስም ቢሆን ግን ያሰቡትን ከመፈፀም ግን ወደኋላ አላሉም ነበር:: ፕ/ር መኩርያ መካሻ የአገራችን የህትመት ሚዲያ 100 አመት ያህል ያስቆጠረ ቢሆንም ተጋኖ የሚነገርለት ፍሬ አላፈራም ሲሉ በቅሬታ ይገልጻሉ::

ከኢጣሊያ ወረራ በፊት፣በወረራው ወቅት ወራሪዎቹ የራሳቸውን ፕሮፓጋንዳ ሲያካሂዱበት የነበረው ፕሬስና ከነጻነት መልስ የታየው ያን ያህል የጎላ አልነበረም ይላሉ:: በደርግ ዘመን የነበረውን ሲያስታውሱም በመንግስት ስር ይታተሙ ከነበሩ ጋዜጦችና የተለያዩ መ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት መጽሄቶች ውጨ፲ርፉን የሚያሳድግ እንቅስቃሴ እንዳልነበር ከዚያ ወዲህም ከወገንተኝነት እስከ ልሳንነት የዘለቀ አካሄድ መስፈኑ በብዙ አመታት ውስጥ ጥቂት ብቻ እንድንጓዝ አስገድዶናል ብለዋል::

## «ሞኖፖሊ» እና ነፃው ፕሬስ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ ለረዥም አመታት ያስተማሩት ረዳት ፕ/ር ዘካርያስ ቀነዓ የአገራችንን ሚዲያ አስመልክቶ ከቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስካሁን ባለው ሂደት የነበረውን እውነታ በዳሰሱበት ጥናታዊ ጽሁፋቸው የህትመት ውጤቶች ለሕዝብ መድረሳቸው ብቻውን የፕሬስ ነፃነትና የሕትመት ሚዲያ አለ ለማለት አያስደፍርም ሲሉ ይከራከራሉ:: ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ ሁለቱ ዋና ዋና የሚዲያ አይነቶች /የብሮድካስትና የሕትመት / ነበሩ የሚሉት ፕ/ር ዘካሪያስ ሁለቱንም ዘርፎች ለመታደግ በአግባቡ መፈተሽ ያለባቸው ነጥቦች እንዳሉ ያሰምሩበታል::

የብሮድካስት ሚዲያን በተመለከተ እስካሁን ያለው ሁኔታ የመንግስትን ሞኖፖሊ የሚያመለክት እንደሆነ የሚገልፁት የሕግ ባለሙያው በቅርብ ጊዜያት ይህን ዘርፍ በከፊልም ቢሆን «ፕራይቬታይዝ» አድርጎ ለመቆጣጠር ሕጎች ቢወጡም በተጨባጭ «የግል ብሮድካስት ሚዲያ በኢትዮጵያ አልተጀመረም» የሚያሰኝ ነው ይሉታል:: «ተጀምሯል» ቢባል እንኳ በአድማጮችና ተመልካቾች ፍላጎት ላይ ያተኮር ስለመሆኑ ጥያቄ እንደሚፈጥር አስምረውበታል ::

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ደስታ ተስፋው ግን የብሮድካስት ሚዲያ ጠበቅ ያለ የሕግ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልገው ይገልፃሉ:: በተለይ ካለው ተደራሽነት አኳያ ፕሮግራሞቹ ሲተላለፉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለሚከታተሉትና ይህም ተገቢ ያልሆኑ ሃሳቦች ቢተላለፉ ሊከተል ከሚችለው ጉዳት አንፃር ተሰልቶ መሆኑን ተናግረዋል:: ይህንን ለመከላከልም ባለስልጣን መ/ቤቱ የዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ስልት እንዳለ አምነዋል::

ዋና ዳይሬክተሩ ለአንድ ለመስተዳድሩ የህትመት ውጤት ከሰጡት ገለፃ ለመረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ስልቱ በብሮድካስት አማካይነት በተላለፈ ፕሮግራም የሆነ አይነት ጉዳይ እንደደረሰ ከሚቀርቡ ቅሬታዎች በመነሳት የማጣራትና ፈቃድ እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ የሚወሰድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በተቋሙ ባለሙያዎች ፕሮግራሞቹ ከተሰራጩ በኋላ የሞኒተሪንግ ሥራ የሚሰራ መሆኑ ነው::

ምንም እንኳ አቶ ደስታ የሚወስዱት እርምጃዎች በሙሉ በሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መሰረት የተቃኙ ናቸው ቢሉም ይህ አገላለጽ ከፕሬስ ነፃነት ምንነት አንጻር መገምገም አለበት የሚሉ ወገኖች አሉ::

## ለትርጉም የተጋለጡ አዋጆች ጦስ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ ፕሬዝዳንት የሆኑት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በሰፈነባቸው አገራት ከነፃ ፕሬስ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ «ፈቃድ መሰረዝ» የሚለው ነገር ስፍራ እንደሌለው ይገልፃሉ:: «በርካታ ዴሞክራቲክ መንግስታት የቅድመ ህትመት ምርመራን ሲያስቀሩ የፕሬስ ሥራ ፈቃድ» ሰነድን ያላስፈላጊነትን በማጎናፀፍ ጭምር ነው:: በእነዚህ አገራት ያለውን አሰራር ስንፈትሽ የፕሬስ ተቋማትን በኃላፊነት የመስራት አቅም የሚያጎለብትና ሙያዊ ተልዕኳቸውን እንዲወጡ የሚያበረታታ ቢያንስ እንቅፋት የማይሆን አካሄድ ይታያል::»

አቶ ዘሪሁን የሚያነሱት ሌላው ነጥብ የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የሚወጡ ሕጎች አገሪቱ ፊርማ የተቀበለችቻቸውን ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች የጠበቁ ከመሆን በተጨማሪ የመናገርና የመፃፍ ተፈጥሯዊ ነፃነቶችን ታሳቢ ያደረጉ የመሆናቸው ጉዳይ ነው:: በሌላ በኩል ወንጀልን ለመከላከል በሚል የሚወጡ ማንኛውም አይነት የሕግ ድንጋጌዎች በሕግ መንግስቱ በግልጽ ከተደነገገው ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ጋር በምንም መልኩ የሚጣረስ ከሆነ ዘርፉ በአደጋ ጎዳና ላይ ለመሆኑ አመላካች ይሆናል::» በማለት በአሁኑ ወቅት በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ የሚታየውን በነፃው ፕሬስ ላይ እየደረሰ ያለ ሁለንተናዊ ጫና የሕጋዊነት ሽፋን የሚታይበት ሆኖም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለውን ዘርፍ ወደ መቃብሩ ሊከት የሚችል ሲሉ ይገልፁታል:: የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ለፕሬስን አስመልክቶ ያሰፈራቸው ሃሳቦች በእጅጉ ለትርጉም የተጋለጡ መሆንም በመስኩ ላይ እንዳነጣጠሩ ጥቃቶች ይታያሉ ብለዋል::

ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት በሰፈረው አንቀጽ ዙርያ ቀደም ሲል በሕግ የበላይነት አምዳችን አስፍረነው የነበረው አቶ ዘሪሁን ካነሱት ሃሳብ ጋር ይስማማል:: በእርግጥ በሽብርተኝነት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ወንጀሎች ማበረታታት እራሱ እንደወንጀል የሚቆጠርባቸው ሁኔታዎች አሉ:: የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁም የሽብርተኝነት ድርጊትን ስለማበረታታት የሚለው አለው:: ሆኖም በአንቀጽ 6 የሰፈረው ከሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ለይቶ የፕሬስ (የህትመት) ውጤቶችን በቀጥታ ይመለከታል::

«ማንኛውም ሰው መልዕክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የሕብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይ በሙሉ በዚህ አዋጅ [አንቀጽ 3] የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይ በማንኛ ውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ እንደሆነ ከ10 እስከ 20 ዓመት በሚያደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል::» ይላል::

ይህ ድንጋጌ «ያተመ ወይም ያሳተመ» በሚልበት ሰዓት በተለይ የህትመት ውጤቶችን እንደሚመለከት ግልጽ ነው:: «መልዕክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የሕብረተሰቡ አባላት» የሚለውም የጋዜጣው ወይ የህትመት ውጤቱ አንባቢዎችን ሊያመለክት ይችላል:: እናም ድንጋጌው እነዚህ አንባቢዎች ዛቻን ጨምሮ ከላይ በአንቀጽ 3 ስር

ወደ ገፅ 11 ዞሯል


ማስታወቂያ

# አዲስ ኮሌጅ

- **አራት የቴክኖጂ ሙያዎችን በመጀመሪያ ድግሪ ደረጃ** - ለእያንዳንዳቸው ዋና እና ደጋፊ ትምህርቶች የተጠናከሩ ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖችን አደራጅቶ፣
- **ከ14 በላይ የቴክኒክና የቢዝነስ ሙያዎችን በአዲሱ የTVET መመሪያ መሠረት ከደረጃ I እስከ ደረጃ IV** - ለያንዳንዳቸው ዋና እና ደጋፊ ኮርሶች ዎርክሾፖችን አደራጅቶ በድምሩ በ33 ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች እና በ31 ክፍሎች የሚያስለጥን፤ ከክልልና ከአጎራባች አህገሮች ጭምር በምርጫ እየመጡ የሚሰለጥኑበት ለአለፉት 18 ዓመታት ተማሪውን ሥራ ፈጣሪና ተቀጣሪ ያደረገ ኮሌጅ ነው:: በመሆኑም ከየትኛውም የኒቨርስቲ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በዝውውር የሚመጡ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሰልጠን ለገበያው የሚያበቃ መሆኑን እየገለጸ፤ በአዳማ ከተማ አዲስ በከፈተው ቅርንጫፍ ተማሪዎች የሚቀበል መሆኑን በደስታ ያስታውቃል

## የቴክኒክ ሙያዎች

| Occupations | Level |
|---|---|
| • Automotive electricity - Electronics | I - IV |
| • Automotive Service & Engine Overhauling | III |
| • Industrial Electrical Machine & Drive Technology | I - III |
| • Audio-Video Equipment Technology | IV |
| • Electronics office Equipment Technology | IV |
| • Electrical House Hold Appliances Technology | III |
| • General Drafting Technology | II - IV |
| • Surveying Technology | I -IV |
| • Masonry | I -IV |
| • Building Electrical Installation | I -IV |
| • Concrete work | I -IV |
| • Plumbing | I -IV |
| • Plastering | I -IV |
| • Tiling | I -IV |
| • Painting and Decorating | I -IV |
| • Building Metal work | I -IV |
| • Coble Stone Road Construction | I - III |

## የቢዝነስ ሙያዎች

| Occupations | Level |
|---|---|
| • Accounting | II - IV |
| • Office Administration and Secretarial Technology | IV |
| • Purchasing | IV |
| • Insurance | IV |
| • Marketing | IV |
| • Hardware and network Technology | III |
| • ICT Support system Service | III |
| • Web and Multimedia Technology | IV |
| • ICT Assistance | IV |

## በቴክኖሎጂ የዲግሪ ሙያዎች

| Programs | Level |
|---|---|
| • Architecture and Urban Planning | 1st Degree |
| • Automotive Technology & Vehicle Management | 1st Degree |
| • Construction Technology and Management | 1st Degree |
| • Electrical - Electronics Technology | 1st Degree |

አድራሻ:- 0116 63 56 93/94 0116 63 12 77 0911 22 18 10




PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# «ረመዳን የጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦ እና የጥሞና ወቅት ነው»

## በባራክ ሁሴን ኦባማ



**ይህ የረመዳን [ፃምን] በማስመልከት ፕሬዘዳንት ኦባማ በዓለም ዙርያ ለሚገኙ ሙስሊሞች ረመዳን የበረከት ወር እንዲሆንላቸው መልካም ምኞታቸውን ያስተላለፉበት መልእክት ነው::**

እኔና [ባለቤቴ ] ሚሸል፣ በአሜሪካ እና በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ሙስሊሞች፣ በአሜሪካ ሕዝብ ስም መልካም ምኞታችንን ለማስተላለፍ እንወዳለን:: ረመዳን ከሪም::

ረመዳን ሙስሊሞች ከእምነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ጥበብ እና መመሪት፣ እንዲሁም የሰው ልጆች አንዱ ለሌላው እና ለፈጣሪ ያለባቸውን ኃላፊነት በጥሞና የሚያጤኑበት ወቅት ነው:: ይህ ወቅት ቤተሰቦች የሚሰባሰቡበት፣ ወዳጆች «ኢፍጣር» (የዕለታዊ ፃም መግደፍያ) የሚያስተናግዱበት እና ከማዕዳቸው የሚያጋሩበት [ወቅት] ነው:: ከዚህም ባሻገር ረመዳን የጥልቅ መንፈሳዊ ተመስጦ እና የጥሞና ወቅት ነው - መስሊሞች ቀን ሙሉ ሲፆሙ ውለው ማታ በፀሎት የሚያሳልፉበት፣ በየትኛውም ሥፍራ ላሉ ሕዝቦች መልካም ዕድልን እና ብልፅግናን በመሻት ለሌሎች ድጋፍ የሚያደርጉበት ወቅት ነው:: ልንገነባ የምንሻው ዓለም፣ እውን ልናደርግ የምንሻቸውም ለውጦች - መጀመሪያ በየልቦቻችን እና በየማኅበረሰቦቻችን ውስጥ ማቆጥቆጥ እንደሚገባቸው ሁላችንም ማስታወስ ይኖርብናል::

እኒህ ሃይማኖታዊ ተግባራት፣ ሁላችንም የምንጋራቸውን መርሆች፣ እንዲሁም ፍትኅን፣ እድገትን፣ መቻቻልን እና የመላ የሰው ልጆች ክብርን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ረገድ ኢስላም የሚጫወተውን ሚና ያስታውሱናል:: ረመዳን የታላቅ ኅብር ባለቤት እና ለሰው ዘሮች እኩልነት የቆመ እምነት አውደ-ክብር ነው:: ረመዳን እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥም ኢስላም ሁሌም የአሜሪካ አካል እንደሆነ እና አሜሪካውያን ሙስሊሞችም ለአገራችን እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ያስታውሰናል:: እናም ወርኃ ረመዳንን በደስታ በምትቀበሉበት በዛሬው ወቅት፣ በዓለም ዙሪያ ለምትገኙት 1.5 ቢሊዮን ሙስሊሞች - ብሎም ለቤተሰቦቻችሁ እና ለወዳጆቻችሁ - ልባዊ የሆነ መልካም ምኞቴን ላስተላልፍላችሁ እወዳለሁ::

በዚህ ሳምንት መጨረሻ፣ ለወርኃ ረመዳን ክብር እዚህ ዋይት ሐውስ ውስጥ የኢፍጣር እራት ለመጋበዝ ተስፋ እያደረግሁ፣ [በድጋሚ] የተባረከ ወር እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ::

የፈጣሪ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን::

*/ይህ የፕሬዝዳንት ኦባማ መልእክት በአዲስ አበባ ካለው የአሜሪካ ኤምባሲ ለአውራምባ ታይምስ የተላከ ነው::/*

“

**መስሊሞች ቀን ሙሉ ሲፆሙ ውለው ማታ በፀሎት የሚያሳልፉበት፣ በየትኛውም ሥፍራ ላሉ ሕዝቦች መልካም ዕድልን እና ብልፅግናን በመሻት ለሌሎች ድጋፍ የሚያደርጉበት ወቅት ነው:: ልንገነባ የምንሻው ዓለም፣ እውን ልናደርግ የምንሻቸውም ለውጦች - መጀመሪያ በየልቦቻችን እና በየማኅበረሰቦቻችን ውስጥ ማቆጥቆጥ እንደሚገባቸው ሁላችንም ማስታወስ ይኖርብናል::**

# «ያናቆረ» የአባት ወንጀል፣ ክስና ውሳኔ

የእናቷ ነገር ተሸፋፍኖ እንደቀረና ልጆች በሙሉ «አባታችን ይለቀቅልን» ብለው እንደጠየቁ መስማታቸውን ይነግሯታል::

የእናቷ ዘመዶችም በአባቷ ላይ የ15 ዓመት ፍርድ መወሰኑን ይገልፁላታል:: ወ/ሮ ሰብለም ሀምሌ 22/2002 ዓ.ም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሄድ የፍርድ ግልባጩን ጠይቃ በማግኘት የክስ ዝርዝሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታነብ ትልቅ ድንጋጤ ይፈጠርባታል::

በክሱ ላይ ስለእናቷ የተገለፀውን ነገር በትክክል እንደማትቀበለው የምትናገረው ወ/ሮ ሰብለ፣ እናቷ ምን እንደምትሰራና ምን እንደነበረች ጠንቅቃ እንደምታውቅ በመጠቆም፣ «በክሱ ላይ ለወንጀል ድርጊቱ መንስዔ ሆኖ የተገለጸው የእናቴ ስራ አይደለም» በማለት ቅሬታዋን በአካል በመሄድ ከሳሽ አቃቤ ሕግ ለነበሩት አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው ታስረዳለች::

አቶ ቴዎድሮስም «ፖሊስ ለኛ አጣርቶ ያመጣልን ይህንን ጉዳይ በትክክል በፍርድ ቤት ታይቶ አግባብ የሆነ ፍርድ ተሰጥቶታል» ሲሏት «በክሱ ላይ ቅሬታ ስላለኝ ይግባኝ ማለት እፈልጋሁ» ላለችው የይግባኝ ጊዜ ማለፉ በአቃቤ ሕጉ ስለተነገራት ወደ 3ኛ ወንጀል ምርመራ ማዕከል በማምራት ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን ኮማንደር ተስፋዬ መንገሻን ታነጋግራቸዋለች:: ኮማንደሩም ጉዳዩን እንደሚያውቁት ይገልጹላታል:: ወ/ሮ ሰብለም «እናቴ እንደ መጥፎ ሰው የክስ ቻርጅ ላይ ተጽፋለች:: በህዝብ ሚዲያም ጉዳዩ ተዘግቧል:: እናቴ መ/ቤቷ ውስጥና በመኖሪያ ቤቷ በር ላይ «አንድ ወንድ ሳመች» ተብሏል:: ያ ከእናቴ ጋር የተሳሳመው ወንድ ማነው? የት ነው ያለው? የዚህ እውነተኝነት የታለ? ስለዚህ ይህንን ጉዳይ ያጣራው ፖሊስ መረጃውን ከየት ነው ያመጣው?» የሚል ጥያቄ ታቀርባለች:: በማከልም እሷ ከዱባይ ለእናቷ ቀብር መጥታ 15 ቀን ያህል ልቅሶ በተቀመጠችበት ወቅት ማንም የፖሊስ አካል መጥቶ ቤተሰብ፣ እህቶቿን፣ ጎረቤት እና የመ/ቤቷን የስራ ባልደረቦች አለማነጋገሩንም ትጠቅሳለች:: ኮማንደር ተስፋዬ «አንቺ የምታውቂውን ነገር ደብቀሽ ሄደሽ፣ እኛ ምን እናድርግ:: ፖሊስ ማለት ነብይ አይደለም:: የጉዳይሽን እይታ ወደራስሽ እንጂ ወደፖሊስ አታድርጊ» በማለት ተቆጥተው ከአክስቷ ጋር እንደሸኟት ወ/ሮ ሰብለ ገልፃለች::

**«በክሱ ላይ በተገለጸው መሰረት በሚዲያ የተዘገበው የእናቴ ስም ፍፁም ትክክል አይደለም:: እናቴ ብትሞትም ስሜ ናት:: እኔም የ«ዘማዊ» ልጅም አይደለሁም:: እናታችን ለዓመታት በጭስ ውስጥ ሆና እንጀራ እየጋገረች እኛን ለማሳግ በችግር የኖረች ናት» የምትለው ወ/ሮ ሰብለ፣ መንግስት በክስ ላይ እናቷ የተገለፀችበትን «ትክክለኛ ያልሆነ ጉዳይ በማስረጃ ቢያጣራ» ደስ እንደሚላትና ሆኖም የሷ ዋነኛ ዓላማ በክሱ ላይ የተጻፈው «በትክክል ወላጅ እናቴን ስለማይገልጽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይረዳልኝ» የሚለው መልዕክቷ መሆኑን አስረድታናለች::**

## «አባታችን ይፈታልን»

ቅሬታ አቅራቢዋ ወደ ፍትሕ ሚ/ር መ/ቤት በመሄድ ስትጠይቅ ሚ/ር መ/ቤቱ የተከሳሽ ልጆች መጥተው «አባታችን ለኛ ይጠቅመናል፤ ይለቀቅልን» በማለት አምስት ልጆች የፈረሙበት ማመልከቻ ገብቶ እንደነበረና በዚህም ምክንያት መንግስት ለተከሻሹ የቅጣት ማቅለያ ማድረጉ እንደተገለፀላት ተናግራለች::

ወ/ሮ ሰብለ በድጋሚ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሄድ አቃቤ ሕጉን ስታነጋግረው «ስለጉዳዩ የዘገቡ ሚዲያዎችን አነጋግሪ» በማለት ያቀረቡላትን ሃሳብ በመያዝ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ በመምጣት አጠቃላይ ቅሬታዋን ዘርዝራ አስረድታናለች:: «በክሱ ላይ በተገለጸው መሰረት በሚዲያ የተዘገበው የእናቴ ስም ፍፁም ትክክል አይደለም:: እናቴ ብትሞትም ስሜ ናት:: እኔም የ«ዘማዊ» ልጅም አይደለሁም:: እናታችን ለዓመታት በጭስ ውስጥ ሆና እንጀራ እየጋገረች እኛን ለማሳግ በችግር የኖረች ናት» የምትለው ወ/ሮ ሰብለ፣ መንግስት በክስ ላይ እናቷ የተገለፀችበትን «ትክክለኛ ያልሆነ ጉዳይ በማስረጃ ቢያጣራ» ደስ እንደሚላትና ሆኖም የሷ ዋነኛ ዓላማ በክሱ ላይ የተጻፈው «በትክክል ወላጅ እናቴን ስለማይገልጽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይረዳልኝ» የሚለው መልዕክቷ መሆኑን አስረድታናለች::

## የጠፋው ልጅና የዓመታት ጥርጣሬ

ወ/ሮ ሰብለ ለእናቴ መሞት ምክንያት ከዚህ በታች የተገለጸው ታሪክ መሆኑን ትናገራች:: ታህሳስ 29/1981 ዓ.ም በገና ዕለት ዘውዲቱ ሆስፒታል አካባቢ ባለው መኖሪያ ቤት ውስጥ በወቅቱ ሰብለ ህፃን ወንድሟን ነብዩን አቅፋለች:: እናቷም አቧሬ አክስቷ ጋር ነበረች:: አባቷ አቶ ደሳለኝ ፍፁም የተባለው የስድስት ዓመቱ ልጃቸው ጥፍሩን ሲቆርጥ እጁን በማድማቱ ምክንያት ሰብለን «ህፃኑን አልጋ ላይ አስተኝተሽው ሀኪም ቤት እንውሰደው» ብለው በማቻኮል በአቅራቢያቸው ወዳለ የግል ሀኪም ቤት በመሄድ ትንሽ ይቆያሉ:: ተመልሰው እቤት ሲገቡ ህፃኑ ልጅ የተኛበት ቦታ ላይ የለም:: ሰብለ ግራ በመጋባት ስታለቅስ «አታልቅሺ፤ እናቱ ወስዳው ይሆናል» የሚል መልስ አባቷ ቢሰጡም ህጻኑ ባለመገኘቱ እናቷ ይጠራሉ፤ የሰፈሩ ሰው ይሰበሰባል፤ ፖሊስ ለነሰብለ ጥያቄ በማቅረብ በጉዳዩ ላይ ምርመራ ቢያደርግም ለውጥ አልመጣም::

ወ/ሮ ሸዋነሽ በጣም ሀዘን ውስጥ ይገባሉ:: ነገር ግን ባለቤታቸው አቶ ደሳለኝ ህፃኑ ሲወለድ «ልጁ የኔ አይደለም» የሚለው ተደጋጋሚ ቅሬታ በሃሳባቸው ይመጣል:: «እናቴ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በህጻኑ መጥፋት አባቴን በጣም ትጠረጥረው ነበር» የምትለው ወ/ሮ ሰብለ «አባቴ በተፈጥሮው ቅናት ያለበትና ጥርጣሬ የሚያበዛ ሰው ነው» ካለች በኋላ ከ18 ዓመት በኋላ፣ የዛሬ ሁለት ዓመት በፖሊስ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ላይ ልጅ የጠፋባቸው የሚል የ«አፋልጉኝ ማስታወቂያ» እየተላለፈ ሳለ «ቴሌቭዥን እየተመለከትሽ ነው? የጠፋው ልጅሽን ይመስላል» የሚል ፈጣን መልእክት ከዘመድ ለወ/ሮ ሸዋነሽ ይነገራል::

ወ/ሮ ሸዋነሽም ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ዋና ጽ/ቤት ሲደርሱ ሌሎች «እናት ነን ባዩች» በቦታው ተገኝተዋል:: በወቅቱም የልጁን ምልክት በመናገርና የቤተሰብ ፎቶ በማሳየት ልጁ ለወ/ሮ ሸዋነሽ ይሰጣል:: በሁኔታውም ትልቅ ደስታ ይሰማቸዋል:: ልጁንም አንደኛው ወንድሙ እቤት ይዞት ይመጣል:: በወቅቱ አዲሱ ጉዳይ ከተከሰተ በኋላ ለእረፍት ከዱባይ መጥታ እንደነበረ የምትናገረው ወ/ሮ ሰብለ አባቷ በነገሩ አለመደሰታቸውን ገልጻለች:: ነገር ግን እናቷ በልጁ መገኘት ደስ ቢላትም «ለዓመታት ከልጄ የነጠለኝ ባለቤቴ አቶ ደሳለኝ ነው» በማለት የማጉረምረም ነገር ስለነበረ ጉዳዩን ለሕግ በማቅረብ «እውነቱ ወጥቶ አስፈርድበታለሁ» የሚል ተደጋጋሚ ንግግር ከእናቷ አንደበት ይደመጥ እንደነበረ ጠቅሳለች::

ወ/ሮ ሰብለ ጉዳዩን በማስመልከት አባቷን ለብቻ ስትጠይቅ ስለልጁ ምንም እንደማያነሳ ጠቁማ «ይሄ ልጅ የኛ አይመስለኝም:: እናትሽ እንዲሁ የሰፈርና የመንደር ጉረምሳ ልጇ ብላ ነው ያመጣችው» እንዳሏትና ከዛን ጊዜ ጀምሮም አባቷ እናቷን «ቀበሌ ስራ እየሰራሽ ታመሺያለሽ» በማለት መወንጀል እንደጀመረ፣ እናቷም በጠፋው ልጅ ጉዳይ ክስ እንደምትመሰርት በተደጋጋሚ በመናገሯ ምክንያት አባቷ «በሕግ እጠየቃለሁ» በሚል ፍራቻ «ሳልቀደም ልቅደም» ብሎ እናቷን ለመግደል እንደወሰነ ትልቅ ጥርጣሬ እንዳላትና የወንጀል ድርጊቱ መንስዔ ከዚህ እንደማይወጣ ብትናገርም ፍቅሯ በተወሰነ ደረጃ ከእናቷ ይልቅ ለአባቷ ያመዝን እንደነበረ ግን አልሸሸገችም:: [አሁን ነብዩ ደሳለኝ የሚገኘው ውጪ አገር ነው]::

## «እድሜ ልክ ቢፈረድበት ይሻል ነበር»

ለወ/ሮ ሰብለ ፍርድ ቤት በአባቷ ላይ የወሰነውን አሁን ትልቁ ጥያቄዋ ባይሆንም ከአባቷ ድርጊት አኳያ «እድሜ ልክ ዕኑ እስራት ቢፈረድበት የተሻለ ነበር» ስትል አስተያየቷን አክላለች:: ሄና ደሳለኝ የተባለችው ስምንተኛ ልጅም «አባታችን በጣም ኩሩና ቀብራራ ሰው ነው:: ለኛ ብሎ እንደተባለው ተጉድቶና ተሰቃይቶ አልኖረም:: እናታችን ግን በተቃራኒው ነበረች» ካለች በኋላ እሷም እንደታላቅ እህቷ በክስ ቻርጁ ላይ ስለእናቷ የተገለጸውን በመቃወም «ስሟ ተዛብቷል:: እናቴ እንደዚህ አይነት ሴት አይደለችም:: ማንነቷን አይገልጽም» ስትል በአዘኔታ ተናግራለች:: እንዲሁም እናቴ «ለሳምንት ያህል እቤት አላደራችም» የተባለው ከ«እኔ ጋር የታመሙ አባቷን ልትጠይቅ ሄዳ ነው» ብላለች::

«'አባታችን ጥሩ ሰው ስለሆነ ይፈታልን' በማለት ለፍትሕ ሚ/ር ካመለከታችሁት ልጆች ውስጥ አንዷ አንቺ ነሽ:: ያ ጥያቄ አሁን ከምታቀርቢው ቅሬታ ጋር አይቃረንም?» በማለት ለሄና ላቀረብንላት ጥያቄ ፍፁም ደሳለኝ የተባለው ታላቅ ወንድሟ አንድ ወረቀት አምጥቶ ፈርሚ እንዳላት፣ በወረቀቱ ላይ የተፃፈውን ለማንበብ ስትሞክር ተቆጥቶ እንዳስፈረማትና ትክክለኛ ጉዳዩን ብታውቀው ኖሮ እንደማትፈርም በመግለጽ መሳሳቷን ነእንደተሳሳተች ነግራናለች:: በቀጣዩ ዓመት ወደከፍተኛ የትምህርት ተቋም እንደምትገባ የምትናገረው ሄና፣ አያይዛም «በአባቴ ላይ መንግስት ተገቢ ነው ያለውን ቢወስንም፣ አባቴ እናቴ ላይ ከባድ ውሳኔ ወስኗል:: ነገር ግን በሱ ላይ የተበየነው ውሳኔ ያንሰዋል» ስትል ተናግራለች::

## «ወንድሞቼ በእናታቸው ላይ ከፈረዱ ስራሴ ፈራሁ»

በመጨረሻ፣ «በጉዳዩ ላይ የአቃቤ ሕግ ምስክር ከነበሩት ወንድሞቻቸው ጋር አልተነጋገራችሁም? ካልተነጋገራችሁስ ለምን?» በማለት እህትማማቾቹን ለጠየቅናቸው ጥያቄ፣ በአጋጣሚ የክሱን ጉዳይ ካወቁት በኋላ ወንድሞቻቸው ለስራ ጉዳይ ጅጅጋና ወደሌላ ክ/አገር ስለሄዱ በአካል ለመገናኘት አለመቻላቸውን [ሆኖም አንድ ምሽት ለጥቂት ደቂቃ ቢገናኙም ሁኔታው አመቺ አልነበረም]፣ በአሁኑ ወቅት ስልካቸው እንደማይሰራ፣ ጉዳዩ የእናት ሞት ስለሆነ ሰፊ ጊዜ ሰጥቶ መነጋገር እንደሚያስፈልግ፣ የተደበቀ ነገር ሳይኖር እውነቱ መውጣት እንዳለበትና የፍርድ ውሳኔው ቢስተካከል እንደሚመርጡ በመግለጽ ምላሽ ሰጥተዋል::

የእናታቸው የቀብር ስነ-ስርዓት ሊፈጸም አንድ ሰዓት ገደማ ሲቀረው አንዱ ወንድማቸው መርዝ በመጠጣት ራሱን ለማጥፋት ሞክሮ በሰዎች እርዳታ ሀኪም ቤት ሄዶ እንደዳነ ሄና በመጥቀስ ይህንን ያደረገው ለእናቱ ካለው ፍቅር የተነሳ ቢሆንም አሁን ነገሮች ወደ አባታቸው እንደተቀየረ ጠቁማለች:: በመጨረሻ፣ «ወንድሞቼ ብዙ ነገር የሆነችላቸውን እናታቸውን ወስነው፣ ጨክነው ከፈረዱባት እኔ ራሴ ለራሴ ስለፈራሁ እናቴ ታሳድግልኝ የነበረውን ልጄን ይዤ ከቤት በመውጣት አክስቴ ጋር ገባሁ» ያሉን ወ/ሮ ሰብለ ናቸው::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



በደረጀ ሀብተወልድ
ሆላንድ

# «እዛ ማዶ - ሆ! ይታያል መኪና እማማ ዘነቡ - ሆ! የኛ ማዶና??»

ቀኑ ዐይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር የቡሄ ጭፈራችንን በኮሎኔል አሰፋ ቤት ለማሟሸት ወስነን ወደዚያው አመራን:: ጡረተኛው ኮሎኔል እንደወትሮው ከረዥሙ ጢማቸው ጋር የሚመሳሰለውን ነጭ ጭራቸውን እያወዛወዙ ግቢያቸው ውስጥ ቁጭ ብለው ቪኖ ይጎነጫሉ:: አሹ ማወራረዱን ጀመረ:-

«ቡሄ ና ቡሄ በሉ...» እኛም በስሜት ውስጥ ሆነን ተሰጥኦውን እየመለስን ነው - «ሆ!» በማለት::

አሹ ቀጠለ:-

«እዛ ማዶ - ሆ! ነጭ ኬሻ ሆ!
እዚህ ማዶ - ሆ! ነጭ ኬሻ ሆ!
የኔማ ኮሎኔል - ሆ! ሻምበል ባሻ ሆ!»

ምን ልበላችሁ? ኮሎኔል አሰፋ እሳት ለብሰውና እሳት ጎርሰው በመነሳት ወደ ቤታቸው በፍጥነት ከገቡ በኋላ ከዘራ ይዘው በመውጣት:- «ቀጥል! ጥፋ! ወሮበላ ዱርዬ ሁሉ!!! ኃይለስላሴ የሰጡኝን ማዕረግ እንኩዋን እናንተ ደርግም አልገፈፈኝ? ቀጥል!» እያሉ አንከሳከሱን:: በወቅቱ ስህተታችን ባይገባንም፤ ውሎ አድሮ ግን ሳንረዳው አልቀረንም:: ለዚያ ስህተት የተዳረግነው «የሻምበል ባሻነት ማእረግ - ከኮሎኔልነት እንደሚበልጥ አስበን» የሙገሳ ስንኝ በማዘጋጀታችን ነው:: ለካ አሞገስን ብለን ብዙ ደረጃ ዝቅ አድርገናቸው ኖሯል:: ሆኖም ልጅነት ነውና ባለማወቅ እንጂ ሆን ብሎ የተደረገ አልነበረም::

***ነሀሴ በባተ በ13ኛው ቀን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህኦ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ «ደብረ-ታቦር» ተብሎ ይከበራል - የታቦር ተራራ ማለት ነው:: ይህ ተራራ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ወቅት ድንቅ ተአምራት ከገለፀባቸው ስፍራዎች አንዱ ነው::***

***«... ከስድስት ቀናትም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሀንስን ይዘው ወደረዥሙ ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው:: በፊታቸውም ተለወጠ፤ ፊቱም እንደ ፀሀይ በራ፤ ልብሱም እንደ ብርሀን ነጭ ሆነ:: እነሆ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው:: ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን:- «ጌታሆይ! በዚህ መሆን ለኛም መልካም ነው፤ ብትወድስ በዚህ ሶሰት ዳስ፤ አንዱን ለአንተ፣ አንዱንም ለሙሴ፣ አንዱንም ለኤልያስ እንስራ» አለ:: እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፣ እነሆም ከደመናው - «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት» የሚል ድምጽ መጣ»***

***ማቴ 17፤ 1-5***

አባቶቻችን እንዳስተማሩን ባህላዊው የቡሄ በአላችን መነሻ መሰረቱ ይህ በደብረ-ታቦር የሆነው ድንቅ ነገር ነው::

ጎንጉነን የምናጮኸው ጅራፍ የነጎድጉዋድ ድምጽ ምሳሌ ሲሆን፤ የምንቀልሳቸው የቡሄ ዳሶች ደግሞ የጴጥሮስን ንግግር የሚያስታውሱን ናቸው - «ጌታ ሆይ! በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነው፤ አንድ ላንተ፤ አንድ ለሙሴ፤ አንድ ለኤልያስ ዳስ እንስራ» ማለቱን:: **(እዚህ ላይ ጴጥሮስ ለኔ ወይም ለኛ እንስራ አለማለቱ፤ በክርስትና «እኔነት» ስፍራ እንደሌለው አመላካች ይሆን?)**

> “ኢትዮጵያዊነት እንደ ነፋስ የሚጋባ የአውሲያ መንፈስ አይደለም፤ ምንጮች አሉት:: ብዙዎቻችን ከነዛ ምንጮች ስለጠጣን ነው በመፈቃቀድ ገመድ በአንድነት ተሳስረን የምንገኘው:: እነዛም ምንጮች: - የሰርግ ድንኩዋኖቻችን፣ የሀዘን ዳሶቻችን፣ የቡሄ ቤታቻችን ወዘተ ናቸው

ይሁን እንጅ በአሉ ከጥንት ጀምሮ ከኃይማኖታዊነቱ ይልቅ ባህላዊ መልኩ የጎላ እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያመለክታሉ:: ስለዚህም በክርስቲያኖችም ሆነ በሙስሊሞችም ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ ሁሉንም ለረዥም ዘመናት አፋቅሮና አስተሳስሮ ያሳደገና ያኖረ ልዩ በአል ነው - ቡሄ::

ቡሄ መጣ
ያ መላጣ
ቅቤ ቀቡት
እንዳይቆጣ:
የቡሄ ለት
አለው ለከት
እንደ ጋሻ የሚመከት ... እያለ

በቡሄ ሙልሙል ያላደገ ማነው?

አዎ! ባንድ ዳስ ተሰባስበን በፍቅር በልተናል/ ጠጥተናል፤ ተቃቅፈን እና ተቀባብለን ጨፍረናል:: በሚጣፍጠው የልጅነት አንደበት «የእማምዬ ቤት ወርቅ ይፍሰስበት!» እያልን መባረክን፤ መመረቅን ተለማምደንበታል:: ከሁሉም በላይ የአገራዊ ፍቅር መሰረቱን አግኝተንበታል:: ኢትዮጵያዊነት እንደ ነፋስ የሚጋባ የአውሊያ መንፈስ አይደለም፤ ምንጮች አሉት:: ብዙዎቻችን ከነዛ ምንጮች ስለጠጣን ነው በመፈቃቀድ ገመድ በአንድነት ተሳስረን የምንገኘው:: እነዛም ምንጮች: - የሰርግ ድንኩዋኖቻችን፣ የሀዘን ዳሶቻችን፣ የቡሄ ቤታቻችን ወዘተ ናቸው::

ከመለኮታዊ ጥበቃ ባሻገር ለተሳሰርንበት የፍቅር እትብት ዘላቂነት ዋስትና የሆኑትን እነዚህን እሴቶች ታዲያ ልንጠብቃቸውና ልንንከባከባቸው ይገባል::

ይህን ያለኩት አሁን አሁን ባህሉም እየደበዘዘ፤ ጭፈራውም መልኩን እየቀየረ የመጣ ስለመሰለኝ ነው::

ለምሳሌ እኔ:- የዋንዛው ቲማቲም

«ሊሰጠኝ ነው ሳንቲም»

እያልኩ ስጨፍር የማደጌን ያህል፤ የሁለት ጊዜ ታናሽ ወንድሜ ደግሞ ሰሞኑን የቡሄ ጭፈራው እንደሚከተለው በኢሜል አድሶኛል::

«እዛ ማዶ ቀይ ዶሮ - እዚህ ማዶ ቀይ ዶሮ
የኔማ ደረጀ - ሊልክልኝ ነው - መቶ ዩሮ»

---



በግርማ ካሳ
(ከቺካጎ)

# መንፈሳዊ አባቶች አሉን፤ ግን የሉንም!

> ጦርነት መከፈቱን እንደሰሙ፣ የኢራን መንፈሳዊ አባት አያቶላ አሊ አልሲስታኒ፣ ለሕክምና ከሄዱበት ከለንደን፣ ወዲያው ተመለሱ:: የኢራቅ ጊዜያዊ መንግስት ባለሥልጣናትን እንዲሁም የአልሳዳርን ቡድን እንደ አባት አነጋገሩ:: በእኝህ መንፈሳዊ አባት መሪ ምክርና ቁጣ ጦርነቱ ቆመ:: ተኩስ አቁም ታወጀ:: ናጃፍ ተረፈች:: አያቶላ አል ሲስታኒ ዝም ብለው ሊቀመጡ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን እንደ ሃይማኖት መሪነታቸው ማስታረቅ፣ በተቃራኒ ወገን ያሉትን ወደ አንድ ማምጣት እንዳለባቸው የተረዱ ታላቅ ሰው ነበሩ::

እሁድ እለተ ሰንበት ቀን ነበር:: አምላካቸውንና ፈጣሪያቸውን ሊያመሰግኑ ምእመናን የቤተ ክርስቲያኒቱን አዳራሽ አጣበውታል:: በአዳራሽ የነበረው ምእመን ፊቱን ወደ መንበረ ታቦቱ አዙሯል:: መንበረ ታቦቱ በቀኝና በግራ በኩል ነጭ የለበሱ ዲያቆናት ቆመዋል:: በዲያቆናቱ መካከል ከመንበረ ታቦቱ በኋላ ምእመኑን ፊት ለፊት የሚያዩ አንድ የእግዚአብሄር ሰው ይታያሉ:: እኝህ ሰው በመንበረ ታቦቱ ላይ የነበረውን ሕብስት በሁለት እጃቸው አነሱ:: ወደ ሰማይ ዘርግተው ሕብስቱን መባረክ ጀመሩ:: በእጆቻቸው ወደ ላይ ከፍ ያደረጉትን ህብስት ወደ ቦታው ሳይመልሱት፣ ድንገት ሕብስቱም እሳቸውም መሬት ላይ ወደቁ::

እኝህ ሰው ቅዳሴ እየቀደሱ ነበር:: ሕብስቱም የጌታ ሥጋ (ቅዱስ ቁርባን) ነበር:: ከቤተ-ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከሚገኝ የከፍታ ቦታ የተተኮሰ ጥይት የእኝህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ደረት ላይ አረፈ:: የተኮሱት ታጣቂዎች ወዲያው ስፍራውን ለቀው ጠፉ:: ህዝቡ ተደናገጠ:: ለቅሶና ዋይታ አዳራሹን አቀለጠው::

ቅዳሴ ሲያስቀድሱ በጥይት የተገደሉት እኝህ የእግዚአብሄር ሰው የኤልሳልቫዶር (ላቲን አሜሪካ ውስጥ ያለች አገር ናት) ሊቀ ጳጳስ ኦስካር ሮሚሮ ነበሩ:: ኦስካር ሮሚሮ በኤልሳልቫዶር የተስፋፋውን ኢ-ፍትሃዊነት፣ በመንግስት የሚደረገውን ሽብርና ግድያ፣ በአገሪቱም የነበረውን የከፋ ድህነት አጥብቀው የሚያወግዙ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነበሩ:: የሚመሩበትና የሚሰብኩት ወንጌል የፍትህ መጽሃፍ፣ የሚከተሉትና የሚያመልኩት ጌታ ፍትህ አምላክ መሆኑን በመረዳታቸው፣ ይሉኝታ፣ ፍርሃት ሳይዛቸው፣ ጥቅምና ምቾት ሳያታልላቸው ለፍትህ የቆሙ ነበሩ::

በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ይደገፍ የነበረው፣ የወቅቱ ኤልሳልቫዶር ወታደራዊ ጁንታ፣ እኝህን ሰው በመግደል ዝም ለማሰኘት የመረጠው፣ የሊቀ ጳጳስ ኦስካር ጠንካራ የፍትህ አቋም ስላልተመቸውና ስላሰጋው ነበር::

ኦስካር ሮሜሮ ለእውነት፣ ለፍትህ፣ ለድሆች በመቆማቸው በወቅቱ ጉልበተኞች በተተኮሰ ጥይት የወደቁት እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1981 ነበር:: ኦስካር ሮሜሮ እንደ ሌሎች አድርባይ የሃይማኖት መሪዎች ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር ተሻርከው፣ የሕሊናቸውንና የአምላካቸውን ድምጽ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው መኖር ይችሉ ነበር:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰው ምን መሆን እንዳለበት ሕይወታቸውን በመስጠት ያሳዩ ታላቅና የተከበሩ የዘመናችን ሰው ነበሩ::

በሩሲያ በምትገኝ፣ ነዋሪዎቿ 91 ፐርሰንት ሙስሊሞች በሆኑባት፣ ዳጊስታን በምትባል ክፍለ ሃገር ብዙ አባላትን ያቀፈች አንዲት «ሆሳእና» የምትባል የፔንቴኮስታል ቤተ-ክርስቲያን አለች:: የቤተክርስቲያኒቱ አባላት፣ በቤተ ክርስቲያናቸው አዳራሽ ከመዘመርና ከማምለክ በተጨማሪ፣ በሥራቸውም እምነታቸውን የሚገልጹ ክርስቲያኖች ነበሩ:: በእሥር ቤት የሚገኙ በርካታ የዳጊስታን ነዋሪዎች እየጎበኙ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ አገልግሎት ይሰጡ ነበር:: ክርስትና መስቀል ወይንም መጽሃፍ ቅዱስ ይዞ መዞር፣ ጠዋትና ማታ ቤተ ክርስቲያን መዋል፣ መስቀል ይዞ እያማተቡ በስመ አብ ወይንም ደግሞ መጽሃፍ ቅዱስ ወደ ላይ እያነሱ «በኢየሱስ ስም» ማለት ብቻ ሳይሆን፣ «ታምሜ አልጎበኛችሁኝም፤ ታስሬ አልጠየቃችሁኝም፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፣ ተርቤ አላበላችሁኝም» እንደሚለው መጽሃፉ፣ የተጠቁትን፣ የተገፉትን፣ የወደቁትን መመልከትና ማንሳት፣ ለመበለቲቱ መሟገት፣ ለድሃ አደጉ መፍረድ እንደሆነ የገባቸው ክርስቲያኖች ነበሩ::

የሆሳዕና ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ይህን መሰል የተከበረ ሰብዓዊ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር፣ የቤተ ክርስቲያኒቷ መጋቢና ፓስተር፣ በክልሉ ባለሥልጣናት የሚደረጉ ግፎችንና ወከባዎችን በግልጽና በድፍረት ይቃወሙና ያወግዙ ነበር:: ፍትህ ሲዛባና ፍትህ ሲረገጥ ማየት የክርስትና እምነትን የሚጻረር በመሆኑ፣ ለፍትህ ያልቆመ ክርስቲያን ክርስቲያን ሊባል ስለማይችል፣ ፓስተሩ ለጥቅምና ለጊዜያዊ ከበሬታ ሲሉ እምነታቸውን አመቻምቸው ከመኖር፣ እውነትን ተናግረው የሚመጣው ለመቀበል ወሰኑ::

ከአራት ሳምንት በፊት ነው፣ ጁላይ 15 ቀን እኝህ የሆሳእና ፔንቴኮስታ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ፓስተር አርተር ሱሌማኖቭ ከመኪናቸው ሲወጡ በታጣቂዎች የተገደሉት:: የክልሉ ባለሥልጣናት በድርጊቱ እንደሌሉበት ይናገሉ:: ነገር ግን ከእኝህ ፓስተር አንደበት የሚወጡት የተከበሩ ቃላት እንደጦር ስላስፈራቸው፣ እርሳቸውን ዝም ለማሰኘት ያደረጉት ሰይጣናዊ ድርጊት እንደሆነ ይታመንበታል:: ፓስተር ሱሌማኖቭ ገና አርባ ዘጠኝ አመታቸው ነበር::

ሳዳም ሁሴን በአሜሪካኖች ወረራ ከስልጣን ተወግዷል:: የሳዳም ሁሴንን መውደቅ ተከትሎ በኢራቅ አንዳንድ ኃይሎች ብቅ ማለት ጀመሩ:: ከተለያዩ ቡድኖች የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግስት ተቋቋመ:: ኢያድ አላዊ የመጀመሪያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ:: እንደተጠበቀው ግን ሁኔታዎች ሊረጋጉ አልቻሉም:: በአል ሳዳር የሚመሩት የሺያ ቡድኖች በአሜሪካኖች የሚደገፈው ጊዜያዊ መንግስት ላይ አመጹ:: አሜሪካኖች ከአልቃይዳና ከሱኒ ተዋጊዎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሺዓዎች ጋርም ፍጥጫ ገጠማቸው:: ብዙ ጥረቶች ተደረጉ ሊሳካ አልቻለም:: በመጨረሻ በናጃፍ ከፍተኛ ውጊያ ተከፈተ::

ጦርነት መከፈቱን እንደሰሙ፣ የኢራን መንፈሳዊ አባት አያቶላ አሊ አልሲስታኒ፣ ለሕክምና ከሄዱበት ከለንደን፣ ወዲያው ተመለሱ:: የኢራቅ ጊዜያዊ መንግስት ባለሥልጣናትን እንዲሁም የአልሳዳርን ቡድን እንደ አባት አነጋገሩ:: በእኝህ መንፈሳዊ አባት መሪ ምክርና ቁጣ ጦርነቱ ቆመ:: ተኩስ አቁም ታወጀ:: ናጃፍ ተረፈች:: አያቶላ አል ሲስታኒ ዝም ብለው ሊቀመጡ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን እንደ ሃይማኖት መሪነታቸው ማስታረቅ፣ በተቃራኒ ወገን ያሉትን ወደ አንድ ማምጣት እንዳለባቸው የተረዱ ታላቅ ሰው ነበሩ::

ኢትዮጵያ ውስጥ ኦስካር ሮሜሮዎች፣ አርተር ሱማሌኖቮች፣ አያቶላ አሊ ሲስታኒዎች አሉን? በሰው ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፣ ለጥቅማቸው ያላደሩ፣ ለፍትህ የቆሙ፣ እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ወይንም ባለሥልጣናትን የሚያገለግሉ የእግዚአብሔር ሰዎች አሉን? አዎ የኃይማኖት መሪዎች አሉን:: ነገር ግን የሉንም!

ምርጫ 2002 ሊደረግ ጥቂት ቀናት ሲቀሩ፣ በቴሌቪዥን እንዳየነው፣ ካባ የለበሱ፣ መስቀል የያዙ፣ አንገታቸው ላይ ነጭ መቀነት ያደረጉ፣ የኃይኖት መሪዎች ነን የሚሉ ብዙ ነበሩ:: ነገር ግን እንደ ሊቀ ጳጳስ ሮሜሮና ፓስተር ሱሌማኖቭ ለፍትህ፣ ለተጠቃው፣ ለተገፋው ሲቆሙ አላየንም:: በኢራቅ አያቶላ አል ሲስታኒ እንዳደረጉት በአገራችን የሰፈነው የፖለቲካ ቀውስ ይወገድ ዘንድ፣ ኢትዮጵያውያን እንደ ወንድማማቾች ይቀባበሉ ዘንድ፣ አንዳቸው በሌላቸው ላይ ከመጨከን ይቆጠቡ ዘንድ፣ ፍቅር በምድራችን ይሰፍን ዘንድ ለእርቅ ሲሰሩ አላየናቸውም:: በወንጌል እንደተጻፈው ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «የሚያስታርቁ ብጹዓን ናቸው» ነበር ያለው:: ነገር ግን እነዚህ መሪዎች እንኳን ሌሎችን ሊያስታርቁ ከራሳቸው ጋር መታረቅ ያልቻሉ የመንፈስ ደካሞች እንደሆኑ ነው እያየን ያለነው::

በአገራችን ዜጎት ህይወታቸውን ያጣሉ:: የኢህአዴግ አባል ስላልሆኑ ከሥራ ይባረራሉ:: ያለ ምንም ወንጀል ፍርድ እየተጣመመ ይታሰራሉ:: ሙስናና ሌብነት ከላይ እስከታች ተንሰራፍቷል:: ካልሰረቁ፣ ጉቦ ካልበሉ፣ የኢህአዴግ አባል ካልሆኑ፣ ከባለሥልጣናት ጋር ዝምድና ከሌላቸው፣ ወይንም ውጭ አገር ዘመድ ከሌላቸው በስተቀር ኢትዮጵያውያን በንጹህ መንገድ ሰርተው ትልቅ ደረጃ መድረስ የሚችሉበት ሁኔታ የለም:: የ99.6 በመቶ የምርጫ ውጤት እንደሚያመለክተው ሰላሳ አመታት ወደኋላ እየሄድን ነው:: በዚህ ሁኔታ ሞራል ድምጽ ሆነው፣ «የሚደረገው ነገር ትክክል አይደለም» የሚሉ የሃይማኖት አባቶችን ግን አናይም::

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ በምሳሌነት መጥቀስ ብቻ ይበቃል:: የአሜሪካና የአውሮፓ መንግስታት፣ በርካታ ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግስታት፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሕሊናና የፖለቲካ እስረኛ እንጂ የሕግ እሥረኛ እንዳልሆነች እየገለጹ፣ ያለ አንዳች ቅድመ

ወደ ገፅ 23 ዞሯል



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



## የእቤት ወግ

አቤ ቶኪቻው abeto2007@yahoo.com

# «እምዬ ቀበሌ» ቻው ቻው…

ከቀበሌ ጋር ትዝታ የሌለው ማን አለ? የዛሬን አያድርገውና ስኳር በኩፖን እየተቀበልን የተራጨንባት እምዬ ቀበሌ ናት:: የዛሬን አያድርገውና ያኔ በደርጉ ዘመን ችግር ከዳር ዳር አዳርሶን አላላውስ አላንቀሳቅስ ባለን በዛ በርሀቡ ዘመን «ተወዷል ጤፍና ስንዴ ሩዙን ብላ በዘዴ» በተባለበት ሰአት ሩዝ ከየት ይመጣ ነበር? ያው ከቀበሌ አነበር?

ጉዞ ሲያደርጉ በደረሱበት አካባቢ የሚያጋጥምዎት ዋርዲያ፣ አልያም በሆነ ጉዳይ «መታወቂያ!» ያልዎት ያገባኛል ባይ መታወቂያ ሲጠይቅዎ አብዛኛውን ጊዜ የሚሻው የቀበሌ መታወቂያዎን ነው:: ምክንያቱም ቀበሌ ዋና ነዋ! የቀበሌ መታወቂያ የሌለው ነዋሪ ዘዋሪ እንጂ ነዋሪ ለማለት አያስደፍርማ!

ድሮ ድሮ ከወዳጆቻችን ጋር ስንቀያየም «ሂድ ቀበሌ ክሰሰኝ» ይባል ነበር:: ምክንያቱም ቀበሌ ቀበሌ ብቻ ሳትሆን ፍርድ ቤትም ነበረቻ!

ቀበሌ አካባቢ የዋለ ሰው ለጉሮሮው ምግብ ቢያጣ ለጆሮው ወሬ አያጣም:: ከሬድዮ ቀጥሎ የወሬ ዋና ምንጭ ቀበሌ ናት:: መዝናኛዋስ ቢሉ… ቀበሌ መዝናኛዋ እንደሌሎች መዝናኛ ዎች በርካታ ገንዘብ ካልመዘዙ አይዝናኑም አትልም:: ዋጋዋ ኪስ አይጎዳም:: (በርግጥ ዋጋዋ ኪስ ባይጎዳም የሚሰናዱት ምግባ ምግቦች ጤናን የሚጎዱበት ጊዜ እንዳለ አንዳንዶች ሲያወጉ ይሰማል) ቢሆንም ግን ቀበሌ «እምዬ» መባል የሚያንሳት ነበረች:: ዛሬ ግን ቀበሌ ስሟ የለም:: ቀበሌ ከቀበሌ ጠፍታለች:: እኛም የዘመናት ወዳጃችን ቀበሌን «እምዬ ቀበሌ ቻው ቻው…» ብለናታል:: ለመሆኑ ቀበሌ ምን አጥፍታ ነው እንድትጠፋ የተፈረደባት? ከዚህ በኋላ የቀበሌ መታወቂያ፣ የቀበሌ መዝናኛ፣ ቀበሌ ወጣቶች፣ የቀበሌ ሴቶች፣ እና የቀበሌ ሊቀመንበር ሳይቀር ተረት ሊሆኑ ነው ማለት ነው? ምክንያቱም ድሮ ቀበሌ ሲባል የነበረው ዛሬ በወረዳ ተተክቷል:: በኮምፒውተር ባለሞያዎች አባባል እንጠቀም ብንል «ቀበሌ ዴሊት ተደርጎ ወረዳ ከሪሳይክል ቢን ሪከቨር ተደርጓል» ማለት ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ በርካቶች ሀዘናቸውን እየገለፁ እንደሚገኙት ሁሉ ፈንጠዝያ ላይ የሚገኙም አሉ ከወደ ማብቂያችን ጭማሪ ይኖረናል:: ከዛ በፊት ሰላምታ:-

ወዳጄ እንዴት ሰነበቱ? እኔ ከእርስዎ ሀሳብና ናፍቆት በስተቀረ ደህና ነኝ:: ልልዎት ፈለግሁኝና ለካስ ሳምንት ተገናኝተናል:: እናም ባለፈው ሳምንት ተገናኝተን ሳለ «ከርስዎ ሀሳብና ናፍቆት በስተቀር» ብዬ ብልዎ ሽርደዳ እንዳይመስልብኝ በማሰብ እንደው በስሱ «አለውልዎ!» ማለቱን መርጫለሁ::

እኔ የምለው ወዳጄ ይሔ «ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም!» የሚባለው አባባል እውነት ነው ማለት ነው? ወይስ አንዳንድ ግለሰቦች ሆን ብለው (የሀገራችን ተረት ዋጋ እንዳያጣ በማሰብም ሊሆን ይችላል) ብቻ ግን በመስከረም ዋዜማ ላይ ጉድ ለማሰማት ጉድ ጉድ ይላሉ ልበል? «እንዴት?» ካሉኝ እንዴት ማለት ጥሩ ጥያቄ ነው ብዬ እቀጥላለሁ፤

እንዴት ማለት ጥሩ ጥያቄ ነው:: (ቢያንስ ቢያንስ ጨዋታው ረዘም እንዲል አድርጎ ወሬው እንኳ እርባና ባይኖረው ለጊዜ መፍጃ ይሆናል::) እናም እንዴት ማለት ጥሩ ጥያቄ ነው:: ሰሞኑን አውራምባ ታይምስ ቢሮ ላይ የደረሰውን ጉድ ሰምተዋል? «ጉድ ሳትሰሙ መስከረም አይጠባትም!» ያሉ ሰዎች በቢሮው ላይ የድንጋይ ናዳ አወረዱበት አይደለም እንዴ? አንዳንድ የአውራምባ ቤተሰቦች ይሔ ነገር «አንደርቢ ይሆንን!?» እያሉ እስኪደመሙ ድረስ የመስኮት መስታወት ተሰብሮ ድንጋይ ቢሮው እስኪገባ ድረስ… (እናጋን ካልን ለሚያብቃቃ ጥንቁቅ ግንበኛ አንድ ቤት መስራት የሚችል ደንጋይ በቢሮ ውስጥ ተገኝቷል) እውነትም ሲታሰብ በህግ ሀገር፣ በመንግስት ሀገር በጥቅሉ ህገመንግስት ባለበት ሀገር እንዲህ አይነት ነገር ይፈፀማል ብሎ ለማመን ስለሚከብድ የለም ይሔ የደብተራ ስራ «አንደርቢ» ነው:: ብሎ ማመኑ ነው የሚሻለው::

### መግለጫ

«አንደርቢ» ማለት በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች አንዳንድ «ድብትርናን» ጠንቀቀው ያጠኑ ተማሪዎች የሚሰሩት ጥበባዊ ስራ ነው:: (በነገራችን ላይ ድብትርና የሚባለው እውቀት ዱክትርና ከሚባለውም በላይ መሆኑን የሚያስረዱ ወገኖች አሉ) እና አንዳንድ ደብተራዎች ሆዬ የተማሩትን ቀና ትምህርት ወደተንኮል በመለወጥ በተለይ በገጠር አካባቢ የሰው ማሳ በረዶ በማስመታት፣ እና በባዶ ሜዳ የድንጋይ ናዳ ወደሰው ቤት በመልቀቅ የተንኮል ጥማቸውን የሚወጡበት የ«አስማት» አይነት ነው:: ልብ ብለዋል…? በሀገር ሰላም ምናልባትም በትንሽዬ ካፍያ የእርስዎ ማሳ ለብቻው ተለይቶ በረዶ ይደበድበዋል:: አሁንም ልብ ብለዋል…? በሀገር ሰላም አንድም ድንጋይ የሚወረውር «ነውጠኛ» በሰፈርዎ በሌለበት የእርስዎ ቤት ብቻ ተለይቶ ደንጋይ ይደበድበዋል:: ከዚህ የበለጠ አስማት አለ? ኧረ የለም ይበሉ ወዳጄ

እና ሰሞኑን የአውራምባ ታይምስ ቢሮ በአንደርቢ ጥበበኞች ይሁን፤ ወይ ደግሞ በድንጋይ ውርወራ «አንቱ» የተባሉ ባለሞያዎች እንጃ … ብቻ ግን የደንጋይ ናዳ ቢዘንብበት «በህግ አገር በመንግስት ሀገር ባጠቃላይ በህገ መንግስት ሀገር እንዴት እንዲህ ደረጋል?» ብለው የአውራምባ ወዳጆቻችን በቅድሚያ ወደ ፖሊስ ሄዱ:: ጉዳዩን ለማጣራት ከመጡት ውስጥ አንዱ «የእኛ ሰው» እንዲህ ተናገረ አሉ «አይ ትንሽ ነው ብዙ አልተጎዳችሁም!» አለ አሉ በዚህ ጊዜ አንዱ ጋዜጠኛ በሆዱ ምን እንደተናገረ ያውቃሉ? «ምነው ከዚህም በላይ ነበር እንዴ የታዘዘልን?» አለ:: ይህ ንግግር እንኳንም በሆድ ሆነ እንጂ «የእኛን ሰዎች» በአንደበት እንዲህ የተናገሩ ብዙዎች በአሁኑ ሰዓት ጤናቸው ተቃውሶ ይገኛሉ::

የሆነ ሆኖ የአውራምባ ወዳጆቻችን ጉዳዩን ለፖሊስ ብቻ አመልክተው ዝም አላሉምና ለጋዜጠኞች እና ለየ ዌብ ሳይቱ አደረሱት ታድያልዎ የአሜሪካ ድምጽ ራድዮን ሆዬ ጉዳዩ ይመለከተዋል ያለውን የህግ አካል በስልክ ደውሎ «እንዴት ነው ነገሩ?» ብሎ መጠየቅ… የህግ አካሉ ዋና የስራ ሂደት ባለቤት ምን መለሱ… «ነገሩ ምንም ፖለቲካዊ አንድምታ የለውም!» አሉዋ! ይህንን የሰማ አንድ «ወዳጃችን» ለማለት የማያስደፍር ግለሰብ ታድያ ምን አለ መሰልዎ… «ይሄ ነገር ምርመራው ሳይጣራ እከሌ ነው እንቶኔ አይደለም… አላማው ይሔ ነው ይሔ አይደለም ማለት አግባብ ነውን?» ሲል መጠየቅ… ማንን? እኛን… እኛም ለህግ አካሉ ተወካይ ያለንን ተቆርቋሪነት በሚያሳብቅ ድምፅ «ምርመራው በቅልጥፍና ተጠናቆ ይሆናል ምን ታውቃለህ?» ብለን መለስንለት:: ወዳጃችን ግን አንዴ ከአንደበቱ መልካም እንዳይወጣ «ፕሮግራምድ» ሆኗልና «እኔ የምለው…» ሲል ጀመረ… እርሱ የሚለው «የዘንድሮ ምርመራ ለጋዜጣዊ መግለጫ ሲሆን ማኛ ጤፍና ሰርገኛን በሚመረመርበት ፍጥነት ያልቃል:: ባለጉዳዩ የፍትህ ያለ ሲል ደግሞ የጠፈር ምርምርን ያኽል ይርቃል ኧረ ጎበዝ እንዴት ነው ነገሩ?» አለን እኛም ይህ አይነቱ ንግግር በሚቀጥሉት አምስት አመታት «በእድገት እና ትራስፎርሜሽኑ» ዕቅድ ከድህነት ጋር እንደሚጠፋ ተስፋ አድርገን እና ታግሰን ዝም አልነው::

ውይ ወዳጄ ቅድም ከሰላምታዬ በታች እንደው ዘልዬ ወደነገር ገባሁኝ እንጂ እንኳን ለደብረታቦር ክብረ በዓል ወይም ቡሄ ወይም ሆያሆዬ በሰላም አደረሳችሁ ለማለት በዕቅድ ደረጃ ይዤው ነበር:: ይቺ በዓል ግን ግርም አትልዎትም? ስሟ አበዛዙ…ደግነቱ እንደስሟ ወጪ ያን ያኽል የበዛ አይደለም:: ዶሮ እረዱልኝ አትል… ሙክት ጎትቱልኝ አትል… ቅርጫ ግቡልኝ አትል ጥሩ የደሀ አመት ባል ማለት ቡሔ ነች! (እረዱልኝ ጥበሱልን ብትልስ ከየት ይመጣል? ብሎ አለቅጥ ማማረር የሀገር መልካም ገፅታን ያበላሻልና አደራ እላለሁ) ለማንኛውም አነሰችም በዛች በዓሏ አመት ጠብቃ የምትመጣ በዓል ነችና ስትመጣ እንኳን አደረስዎ… ስታልፍም አመት አመቱ ያድርሰን መባባል የአባት ነው እና ይኸው አድርሻለሁ:: በነገራችን ላይ ክረምትን በቃ አለፍናት ማለት ነው? «ቡሔ ካለፈ የለም ክረምት ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት» ይባል የለ? እንግዲህ ተረቶቻችን ሁሉ ሃቀ ሃቁን መልዕክት እያስተላለፉ ስለሆነ ከአሁን በኋላ ክረምት የለም ማለት ነው:: ሌላ በነገራችን ላይ አንድ ወዳጄ «ቡሔ ካለፈ… ዶሮ ከጮኸ…» የሚለውን ተረት እንዴት እንዳሻሻለው ሰምተውልኛል «ሮኬት ከጮኸ የለም ክረምት ዶሮ ከጮኸ የለም ለሊት» እውነትም ለቡሔ ክብረ በዓል ተብሎ አዲሳባችን ሰሞኑን የዛኔውን «ባድመእና ሽራሮ» መስላ ሰነበተች አይደለም እንዴ? «ግርግር ለሌባ ያመቻል» ይላሉ ተረት አዋቂዎች በቡሔ ሮኬት ሰበብ ሌሎች ፍንዳታዎች እንዳይመጡ ጠባቂው ይጠብቀን! አያምጣውና ጉዳቱም ከመጣ «ይቺማ ምን አላት?» ብሎ የሚያፅናናውን ይላክልን! አሜን! በዚሁ ከላይ ጀምረን ወዳቋረጥነው ጉዳ እናምራ…

እንኳን ለደብረታቦር ክብረ በዓል ወይም ቡሄ ወይም ሆያሆዬ በሰላም አደረሳችሁ ለማለት በዕቅድ ደረጃ ይዤው ነበር:: ይቺ በዓል ግን ግርም አትልዎትም? ስሟ አበዛዙ…ደግነቱ እንደስሟ ወጪዋ ያን ያኽል የበዛ አይደለም:: ዶሮ እረዱልኝ አትል… ሙክት ጎትቱልኝ አትል… ቅርጫ ግቡልኝ አትል ጥሩ የደሀ አመት ባል ማለት ቡሔ ነች! (እረዱልኝ ጥበሱልን ብትልስ ከየት ይመጣል? ብሎ አለቅጥ ማማረር የሀገር መልካም ገፅታን ያበላሻልና አደራ እላለሁ) ለማንኛውም አነሰችም በዛች በዓሏ አመት ጠብቃ የምትመጣ በዓል ነችና ስትመጣ እንኳን አደረስዎ… ስታልፍም አመት አመቱ ያድርሰን መባባል የአባት ነው እና ይኸው አድርሻለሁ::

«እምዬ ቀበሌን» ከዚህ በኋላ ላንጠራት ተሰነባብተናል:: በርካቶች በሀዘን የተቆራመዱትን ያኽል አንዳንዶችም በደስታ ጮቤ ረግጠዋል:: ብዬዎትም አልነበር? ደስታው ከምን የመጣ እንደሆነ በጠየቅሁኝ ጊዜ በቀበሌ ውስጥ የነበረው ዝርክርክ አሰራር ከስሙ ጋር አብሮ ይጠፋ ይሆናል… በሚል ተስፋ የመጣ እንደሆነ ሰማሁኝ:: ይህንን የሰማ አንደ ወዳጃችን ምን አለ መሰልዎ… «እባካችሁን ስም ሳይሆን ስራ ይቀየር!» አለን:: እኛስ ምን አልን መሰልዎ «ስራማ ከተቀየረ ሰነበተ እኮ!»

የሆነ ሆኖ ቀበሌ አሁን በወረዳ ተተክቷል:: እናም የቀበሌ መታወቂያ፣ የቀበሌ መዝናኛ፣ የቀበሌ ወጣቶች፣ የቀበሌ ወዘተዎች… የወረዳ እየተባሉ ሊጠሩ ነው:: ምንም እንኳ አንዳንዶች «በሚቀጥሉት አምስት አመታት ድህነትን ለማጥፋት ድህነታችንን የሚያስታውሱንን እንደ ቀበሌ የመሳሰሉ ስሞችን ማጥፋት ተገቢ እርምጃ ነው!» እያሉ ሽሙጥ አዘል አስተያየት ቢሰጡም እኛ ከቀበሌያችን ጋር ብዙ ክፉ እና ደግ ያሳለፍን ሰዎች ግን በሀዘን «እምዬ ቀበሌ» ቻው ቻው ብለናታል:: በነካ አንደበታችንም ቀርቶ የነበረው ወረዳን «ወረዳ ሆይ እንኳን ደኽና መጣህ!» ብለነዋል::

<u>በመጨረሻም</u>

### ብሔራዊ ቡድናችን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሁን ለታ ከኬኒያ አቻው ጋር የእግር ኳስ ግጥሚያ አድርጎ ነበር:: በውጤቱም ብሔራዊ ቡድናችን ሶስት ለባዶ በሆነ ውጤት ተሸንፏል:: እኛም ለብሔራዊ ቡድናችን መልካም ከማሰብ የማንቦዝን ሰዎች «በጠባብ ውጤት በመሸነፋችን ተስፋ ሰጪ ቡድን አለን!» ስንል ተኩራርተናል ከእኛ በተቃራኒ የቆሙ ሌሎችም የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል የሚከተለውን ይመስላል:-

አንዱ ወዳጃችን በብሔራዊ ቡድኑ ውጤት በጣም አዝኖ «ድሮውንም እኛ ሀገር የቡድን ስራ አይሆንልንም:: ያንኑ ሩጫችንን መንከባከብ ነው::» ሲል ተናገረ:: እኛም አልን «ሩጫም ቡድን ስራ አለው:: የቡድን ስራ የሌለው ገበጣ ወይም ቼዝ ነው::» ወዳጃችን ላለመሸነፍ ምን እንዳለን ያውቃሉ? «ሩጫ ላይ የቡድን ስራ ያለው ካሸነፉ በኋላ ባንዲራውን በጋራ ሲለብሱት ካልሆነ በስተቀር ሲሮጡ ያየሁት በየግላቸው ነው» አለና!

ሌላው አስተያየት ሰጪበኩሉ «ለሽንፈቱ ተጠያቂ የማደርገው አዲሱን ሜዳ ነው::» አለን:: «እንዴት?» አልነው:: ተጫወቱበት ሜዳ ዘመናዊ አርቴፊሻል ሳር በቅርቡ የለበሰው አበበ ቢቂላ ስቴድም ነው:: እናም ተጫዎቻችን ሜዳውን ስላልለመዱት በኬኒያዎች ሜዳ ላይ የሚጫወቱ መስሏቸው ነው:: አለን:: በዚህ ጊዜስ በበኩሌ ብልጭ ብሎብኝ ሌላ ሌላ ልናገር ነበር::

ወዳጄ ከተናግሮ አናጋሪ ይሰውርዎ! አሜን በሉኝና አማን ያሰንብተን ልበልዎ!

*አማን ያሰንብተን!*


ማስታወቂያ

C enima



ወደ ገፅ 23 ዞሯል

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



# እንደ ኖርዌይ ብናድግ አይሻልም?

በፍስሐ ያዜ

> በጣም ትዕግስቴ አልቆ የእድገት ምኞት አቅጣጫዬን ልለውጥ አልኩና አንድ ዕድል መስጠት እንዳለብኝ ተሰምቶኝ እዚያው ኖርዌይ ቆሜ መጠበቅ ጀመርኩ:: የእድገት ጀት እድገቱን ጭኖ የት ይሄድላችኋል ጃፓን:: አሁን ተስፋ ቆረጥኩ:: ወይኔ አልኩ:: ማንም ተነስቶ እንደህንድ፣ ቻይና፣ ብራዚል፣ ጃፓን ሲያድግ እኔ በኖርዌይ ሰማይ ላይ ተንሳፍፌ ልቅር?

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በየጊዜው በወሬና በቁጥር ደረጃ ፈጣን እድገት እያሳየ መምጣቱን ማንም የማያስተባብለው ሀቅ ነው:: ዴሞክራሲው በየእለቱ እየጎለበተ መሔድም አይካድም:: ለምሳሌ የኢኮኖሚ እድገታችን በማመለከት የታየውን እመርታ በንጽጽር ስናይ:- ኢትዮጵያ እንደ ቻይና አድጋለች:: ባለፉት አመታት ደግሞ እንደ ህንድ አድጋ ነበር:: ከዚያም እንደ ብራዚል አደገች:: ወደ አፍሪካ ስንመጣ ደግሞ እንደ ደቡብ አፍሪካ አድጋ እንደነበር የሚታወስ ነው:: ከጥቂት ወራት በፊት ደግሞ በፖለቲካው እንደ ጃፓንና እንደ ስዊዲን ማደግ መቻሏ በይፋ ተገልጿል::

እንግዲህ የሰዎች አመለካከትና ፍላጎት በግለሰብ ደረጃ ይለያያል:: አንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደቻይና ማደግ ይፈልጋል፤ ሌላው እንደህንድ ማደግ ይፈልጋል፤ የተቀረው እንደብራዚል:: በአፍሪካዊነቱ የሚኮራው ደግሞ እንደደቡብ አፍሪካ ማደግ ይመርጣል:: የመምረጥ መብትም አለው:: ነገር ግን 80 ሚሊዮን ህዝብ ባለበት አገር የሁሉንም የእድገት አይነት ምርጫና ፍላጎት ባንዴ ማሟላት አይቻልም:: ስለዚህ ከሁሉም አገራት እድገት ለኮፍ፣ ለኮፍ እያደረጉ በፍጥነት ለማደግ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ይገኛል::

እንደ ህንድ ብናድግ፣ እንደ ብራዚል ብናድግ፣ እንደቻይና ብናድግ፣ እንደምንም ብናድግ እስካላደግን ድረስ በየትኛውም አይነት እድገት አልረካም:: ይሄን ምኞቴን በተስፋ ስጠባበቅ ረጅም ዓመታት ተቆጥረዋል:: እድገቱ ከቻይና ተነስቶ ካሁን አሁን ወደኖርዌይ ይመጣል ስል፣ በዚያው ወደ ብራዚል ሔደ:: ከብራዚል ወደአውሮፓ ይመጣል ስል በዚያው ወደ ህንድ ሔደ:: አይ ... ከህንድ ተነስቶ እንኳ መምጣቱ አይቀርም፤ ሌላ ወደየት ይሄዳል? እያልኩ በናፍቆት ስጠባበቅ ጭራሽ ወደ ደበቡብ አፍሪካ በረረልኝ::

በጣም ትዕግስቴ አልቆ የእድገት ምኞት አቅጣጫዬን ልለውጥ አልኩና አንድ ዕድል መስጠት እንዳለብኝ ተሰምቶኝ እዚያው ኖርዌይ ቆሜ መጠበቅ ጀመርኩ:: የእድገት ጀት እድገቱን ጭኖ የት ይሄድላችኋል ጃፓን:: አሁን ተስፋ ቆረጥኩ:: ወይኔ አልኩ:: ማንም ተነስቶ እንደህንድ፣ ቻይና፣ ብራዚል፣ ጃፓን ሲያድግ እኔ በኖርዌይ ሰማይ ላይ ተንሳፍፌ ልቅር? በማለት በቅድመ ምርጫዬ ተበሳጨሁ::

ምኞቴ መቸም እንደማይሳካ ስለገባኝ ከኖርዌይ ወደአገሬ መገስገስ ስጀምር እድገት ሆዬ «መጣሁ ደረስኩ» እያለ እየፎከረ እያስገመገመ ስዊዲን አልደረሰ መሰላችሁ? እንዴ? አልኩ:: ስዊዲን ከደረሰማ ከስዊዲን ኖርዌይ በባቡር የጥቂት ሰዓታት መንገድ ነው:: ባለቀ ሰዓት መድረሱ ደስ አሰኘኝ:: ግን ደግሞ የሚሆነው አይታወቅም:: የእድገትን ወፈፌነት ከኔ በላይ ማን ያውቀዋል? አሁንም ዘሎ ወደአርጀንቲና ሊሄድ ይችላል እያልኩ ተጠራጠርኩ:: ግን ማየት አለብኝና መታገስን መረጥኩ:: እንደኖርዌይ እስክናድግ ድረስ እንደምንም ውሸንፍሩን ችዬ ከመጠበቅ በቀር አማራጭ አልነበረኝም::

ስለዚህ የኔ ምርጫ እስኪወራ መጠበቅ አለብኝ:: የታገሰ ሰው የምኞቱን አያጣም:: ይሄው ስዊዲን ደረሰኮ::

ትዕግስት አጣሁ:: ቅርብ አይደል እንዴ ለምን ሔጄ አላየውም፣ በዚያውም «እንኳን ደህና መጣህ» እለዋለሁ አልኩና በፈጣን ባቡር ከኖርዌይ ወደስዊዲን አመራሁ:: እዚያ ስደርስ ለካ ጀቱ የጫነው ፖለቲካዊ እድገት ኖሯል:: እኔ መቸ ይሄን ፈለግሁ? ፖለቲካዊ እድገትማ አገሬ ላይ መቸ አጣሁ? እኔ የፈለግሁት ኢኮኖሚያዊ እድገት እንጂ አልኩና በብስጭት ተመለስኩ:: ይሄን ያህል የጠበቀ ሰው መቸም ... ጥሎ መምጣት ይከብደዋልና ይሄው ኖርዌይን የሙጥኝ እንዳልኩ አለሁ::

ኖርዌይን የመረጥኩበትን ምክንያት ወደ ኋላ እመለስበታለሁ:: አሁን ግን ተጎልቼ ከምጠብቅ ለምን ከእናንተ እንደቻይና፣ እንደብራዚል፣ እንደህንድ፣ እንደሁሉም ካደጋችሁት ጋር የልምድ ልውውጥ ሳደርግ አልቆይም? ብዬ ነው ለጭውውት የመጣሁት::

«አዲስ ራዕይ» የተባለው የኢህአዴግ ልሳን የሆነው መፅሄት በነሀሴ 2002 እትሙ፣ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትራችን «...የምርጫ 2002 አስደናቂና አመርቂ ውጤት በአገራችን እንደ ጃፓንና ስዊዲን ሁሉ የአውራ መድብለ ፓርቲ ሥርዓት መከሰቱን በግልጽ የሚያመለክት ነው...» በማለት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዴሞክራሲው እጅግ ከማደጉ የተነሳ ያለ ጊዜው የዴሞክራሲ ጣራ ላይ ወጥቶ ፍፁምነቱን ማወጁን ያረጋግጣሉ::

ፈጣኑ የፖለቲካ ጀት አንድ ክንፉን ሩቅ ምስራቅ፣ አንድ ክንፉን አውሮፓ ላይ ዘርግቶ ድምፁ በዓለም ላይ እያስተጋባ፣ ጭሱ ወደኢትዮጵያ እየተጎለጎለ ነው:: በቀጣይነት ወደየት እንደሚበር አብራሪው ብቻ ነው የሚያውቀው::

የኢኮኖሚው ጀትማ ተዉት:: አርፎ አያውቅም፤ መብረር ነው ሁሌ:: ማንዣበብ ነው::

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚ/ሩ አቶ ሶፍያን አህመድ በቅርቡ የቀጣዩን 5 ዓመት የልማት እቅድ ይፋ ባደረጉበት ጊዜ ባለፉት ዓመታት የተገኙትን ባለሁለት ዲጂት /አንዳንዱ ከነጥቡ ጋር ባለ ሶስት ዲጂት ነው/ እድገቶች በአሃዝ እየተነተኑ ከገለፁ በኋላ «በቀጣዮቹ 5 ዓመታት አሁን ያለው አገራዊ ምርት በእጥፍ ይጨምራል፤ በዚህም ድህነት ታሪክ ይሆናል» ማለታቸው ይታወሳል:: ይሄ ቃል ለሚሊዮኖች ጆሮ ደርሷል:: ጠቅላይ ሚ/ሩም ይሄንኑ ሃሳብ (እቅድ) ተጋርተውታል::

5 ዓመት በእርግጥ ብዙነው:: ከተሰራበት:: ተስፋም ጥሩ ነው:: ለኔ ግን የሚ/ሩ ቃል ድንጋጤና ፍርሃት አሳድሮብኛል:: ኧረ እንዲያው የሚ/ሩ ቃል 5 ዓመት ስለሆነ ረዥም ጊዜ ነውና እስከዚያ ችግሩን ለመቋቋም በቂ ዝግጅት ማድረግ ይቻላል:: ረሃቡንም ከወዲሁ ለመለማመድ ዕድል ይሰጣል:: የ«ዘ ኢኮኖሚስት» አለላችሁ አይደል እንዴ ለአጣዳፊ ስጋት የሚዳርግ ትንበያ እንዲህ ይላል «... ኢትዮጵያ በቀጣዩ ዓመት ማለትም በ2003 ዓ.ም በዓለም ላይ ከሚገኙ አገራት ፈጣን እድገት በማስመዝገብ 5ኛ ደረጃ ላይ ትቀመጣለች...» ከ12 ወራት በኋላ ማለት ነው:: ታዲያ ያን ጊዜ የት ሊገባ ነው?

ተመልከቱ:- አሁን ባለው ሁኔታ ግብርናው 8.5 በመቶ፣ ኢንዱስትሪው 14 በመቶ፣ የአገልግሎት ዘርፉ 31 በመቶ እድገት አሳይቶ ይገኛል:: የኢትዮጵያን የነፍስ ወከፍ ገቢ 7.2 እድገት ያሳዬ ሲሆን ከ164 ዶላር ወደ 271 ዶላር ከፍ ብሏል:: ባለፉት 4 ዓመታት ይሄን ያህል ግዙፍ ለውጥ በኢትዮጵያ ምድር ተከስቷል:: ባለፉት ዓመታት አጠቃላይ እድገቱ 11.1 በመቶ የነበረ ሲሆን በቀጣዩ 5 ዓመት ደግሞ ወደ 15 በመቶ ለማሳደግ እቅድ ተይዟል:

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር መግለጫ እንደሚያሳው ደግሞ በ2000 ዓ.ም 78.2 በመቶ ደርሶ የነበረው የምግብ ዋጋ ግሽበት በ2001 ዓ.ም ከዜሮ በታች ሆኖ 3.4 በመቶ ወርዷል:: በቀጣዩ 5 ዓመት እነዚህ ቁርጥራጭ ቁጥሮች ወይም ብጥስጣሽ ቁጥሮች ሊወገዱ መሆኑ ነው:: ይሄ ሁሉ ስለኢትዮጵያ ኮ ነው! ስለኢትዮጵያ ምግብ!

እንግዲህ እንደ ኢኮኖሚ ባለሙያ በጂ.ዲ.ፒ 35 ቢሊዬን ዶላር ሊደርስ ነው:: የኔ ጨዋታ ከጂ.ዲ.ፒ ጋር ሳይሆን ከራሱ ከኑሮ ጋር ነው: ሕይወት የሚለካው በመሠረታዊ ፍላጎት መሟላትና በልቶ በማደር እንጂ በቁጥርና በምህፃረ ቃል ነው የሚለው ፍልስፍና አልገባ ብሎኛል:: አንድ አገር ልጆቿን ጥላ ብቻዋን ካደገች ራሷ ዘንጣ ልጆቿን የምታስርብ እናት መሆኗ ነው::

እድገት ተሸክሞ ባየር ላይ የሚንንሳፈፍ ጀት! የማያርፍ:: ባለፉት 4 ዓመታት የዜጎች ገቢ /የብዙሃኑ/ አሁን ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: /በመጪ ዓመት አጋማሽ ይጨመራል ተብሏል/ ባለፉት 4 ዓመታት ከላይ የተዘረዘሩት ዘርፎ ብዙ እድገቶች ታይተዋል:: ልክ በዚያው መጠን ኑሮው በየዓመቱ በእጥፍ እየተወደደ ቀጥሏል:: እድገቱ ሁሉ ከእንጀራ በወጥ ጋር ንክኪነት የለውም:: ምናምን በመቶ እድገት በተመዘገበ ቁጥር ምናምን በመቶ የእንጀራ ዋጋ እየጨመረ እዚህ ደረሷል::

በዚህ መሰሉ ሂደት ፈጣን እድገት፣ ፈጣን ድህነት እየተከተለ እንጂ ምንም እየሆነ እንዳልሆነ ስረዳ ፈራሁ:: ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል እንዲሉ በቀን ሶስቴ ወደበቀን ሁለቴ፣ እንደገና አንዴ ... እየባለ በቀጣዩ 5 ዓመት በቀን ዜሮ ጊዜ ሊሆን ቢችልስ?

ሒደቱ ይሄን ብቻ እንድገምት ያስገድደኛል:: «ያለፈው ተሞክሯችን» እንዳሉት ሚ/ሩ እኔም «ያለፈው ተሞክሮዬ» እላለሁ:: ስለዚህ እፈራለሁ::

ከላይ እንዳየነው የምግብ ዋጋ ግሽበት በአንድ ዓመት ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወርዷል:: ይሄ እውነት ነው? የትኛው ምግብ ነው የቀነሰው? ባለፉት 4 ዓመታት እንጀራ 60 ሳንቲም ነበር:: አሁን 3 ብር ነው:: «የምግብ ዋጋ» ተብሎ በግልጽ ተጠቅሷል:: «በልተው ስለማያድሩ አያውቁትም» ተብሎ ከሆነ ቢያንስ ዋጋውን መጠየቅ የሚያቅተው የለም::

የፈጣን እድገቱ ጥቅምና ውጤት ይሄ ሆኖ ሳለ በቀጣዮቹ 5 ዓመታት «ድህነት ታሪክ ሊሆን ነው» ከተባለ በልቶ ማደርም በተመሳሳይ ታሪክ ይሆናል ወደሚል ትርጓሜ ያመጣናል:: ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ የዘርፉ እድገት መርዶ እንጂ የምስራች የሚሆንበት ምክንያት አይኖርም ብዬ ነው እንደ ኖርዌይ እንድናድግ የፈለግሁት::

ምክንያቱም እንደቻይና፣ ብራዚል፣ ህንድ ወዘተ ማደጉ በልቶ ለማደር ካላስቻለ የግድ ፊታችንን ወደ ኖርዌይ ማዞር ይኖርብናል:: ከተመኙና ከጎመጁ አይቀር የኖርዌይ አይነቱ እድገት ይሻላል:: ምክንያቱም ባሁኑ ሰዓት ከዓለም 1ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች ለኑሮ ምቹ የሆነች፣ ምግብ የተትረፈረፈባት፣ አንድም ስራ አጥ ዜጋ፣ አንድም ችግረኛ፣ ፈጽሞ ምንም አይነት ጥያቄ የሌለባት አገር የምትባለው ኖርዌይ ስለሆነች ነው::

ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ እንደሁሉም አገር በየዘርፉ ማደጓ በንጽጽር ሲገለጽ ኖሮ ኖርዌይ ብቻ ተጠቅሳ አታውቅም:: ለምን? ይሄ ፍትሃዊ አይደለም:: ከተወራ የሁሉም እድገት መወራት አለበት:: ከዚህም በላይ ሲያወሩት ደስ የሚለው የኖርዌይ እድገት ነው::

ደሞ ምን ይባላል መሰላችሁ? «የኢትዮጵያን እድገት ከሌሎች አገራት እድገት ለየት የሚያደርገው የነዳጅ ዘይት ኃብትና የአልማዝ ኃብት ሳይኖራት መገኘቱ ነው»:: ምኑ? ይሄ አይነቱ ፈጣን እድገት:: ጉድኮ ነው::

እስቲ አስቡት፤ እንደኖርዌይ ብናድግ ደግሞ «የኢትዮጵያን እድገት ከሌሎች አገራት እድገት ለየት የሚያደርገው አንድ የታሸገ ምግብ በ5 ብር ተገዝቶ እቃው 6 ብር መሸጡ ነው» ይባል ነበር:: ታዲያ ሲወራ ደስ የሚለው የትኛው ነው? የኖርዌይ አይደል? ስለዚህ እንደኖርዌይ ያሳድገን::

አሜን::

▷ ማስታወቂያ ◁




ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# እየከሰመ ያለው. . .

የተዘረዘሩትን የሽብርተኝነት ድርጊት (አንዱ ወይም የተወሰኑት ወይም ሁሉንም) «እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይ በተዘዋዋሪ መንገድ የማያበረታታቸው ወይም በማንኛወም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት» የሚል ሐረግ በውስጡ ይዟል:: አንባቢዎቹ የሚያበረተታቸው ወይ የሚገፋፋቸው «እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት» የሚለው እጅግ የተለጠጠና ከቀጥታ ውጤቱ ይልቅ ፕሬሱን ለአፈና አሳልፎ የሚሰጥ የሚል ትችት ይቀርብበታል:: ጦሱም ዜጎች ወደ ዘርፉ እንዳይገቡ ተፅዕኖ እንደፈጠረባቸው ያለውን የተቀዛቀዘ እንቅስቃሴ ዋቢ ማድረግ ይቻላል::

## የአንፀባራቂው ጅምር ጥላዎች

ለነፃው ፕሬስ ዕድገት ወሳኝ ናቸው ከሚባሉ ግብአቶች አንዱ የተለያዩ አስተሳሰቦችን ያለገደብ ለማራመድ ያላቸው ብቃት መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ:: በነጻው ፕሬስ የህትመት ሚዲያ የጎለበተ ልምድ ያላቸውና በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማሕበር ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ደርበው ተመስገን «ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እውን የሚሆነው በአዋጅ አንቀጾች ላይ ስለሰፈረ ብቻ አይደለም::» ይላሉ:: አቶ ተመስገን በንጉሱ ዘመን ተሻሽሎ በወጣው ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ድንጋጌ ላይ «በመላው ንጉሰ ነገስት ውስጥ የንግግርና የጋዜጣ ነጻነት የተፈቀደ ነው::» ቢባልም ሃሳቡን በጥቅል ከማስቀመጥ በዘለለ ራሱን የቻለ ሕግ ሊወጣለት አልቻለም፤ፈቃዱም አልነበረም በማለት የአገራችን መንግስታት ለተግባራዊ እርምጃ ያላቸውን ዘገምተኝነት ተችተዋል:: በደርግ ጊዜም ይኸው አካሄድ በመደገሙ ከታሪክ ድግግሞሽ የዘለለ እርምጃ አልታየም ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ ገልጸዋል::

«የ1984ቱን የፕሬስ አዋጅ ተከትሎ በርካታ የጋዜጣና መጽሄት ህትመቶች ለንባብ መብቃታቸው በጎ ጅምር ነበር::» የሚሉት የሳምንታዊው ነጋድራስ ጋዜጣ ስራ አስኪያጅ አቶ አያሌው አስረስ ናቸው:: አንጸባራቂው ጅምር በመጨረሻ የደረሰበትን ውድቀት ግን መንግስት ለተቋማቱ ካለው የተዛባ አመለካከት ጋር በማያያዝ ነው:: «የተለያዩ እምነቶችንና አመለካከቶችን ሲያንሸራሽሩ የነበሩት የፖለቲካ መጽሄቶች ዛሬ በኪነጥበባዊ፣ማሕበራዊና የፋሽን መጽሄቶች የተተኩ ይመስላሉ:: ለነገሩ አንዳቸውም ሌላቸውን መተካት አይችሉም፤እየሄድንበት ያለነውን አሳሳቢ አካሄድ ያመለክቱ ካልሆነ::» ብለዋል::

«እስከማስታውሰው ድረስ ንጉሱ ጊዜ የነበረችው ብቸኛዋ የነጻ ፕሬስ ውጤት «ጸደይ» ስትሆን በደርግ ጊዜ ደግሞ «ቁም ነገር» መጽሄት ብቻ ነበረች:: እሷም በኋላ ላይ እንድትቆም የተደረገች ይመስለኛል:: በመቶዎች የሚቆጠሩ መጽሄቶችን ጀምረን ወደምንም እየሄድን ነው::» ሲሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ:: አንድ አሳታሚ በአንድ ስያሜ ጋዜጣና መጽሄት እንዳያሳትም በሕግ መታገዱ ፋይዳም ግልጽ አይደለም ሲሉ ይተቹታል::

በደርግ ጊዜ ትታተም የነበረችው «ቁም ነገር» የቆመችበትን ምክንያት አስመልክቶ የጠየቅነው የመጽሄቷ ባለቤት የሆነው አንጋፋ አርቲስት ደበበ እሸቱ «ጉዳዩ ሰፊ ነው::...»ካለ በኋላ የመጽሄቷ አጀማመር አዝናኝነትን የተላበሰ ቢሆንም በሂደት ወደ ሌሎች ማሕበራዊና ጠንከር ያሉ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ስትገባ ችግሮች መከሰት ጀመሩ::» በማለት የአሁኑ ፕሬስም መሰል ዕታ እንደገጠመው ገልጿል::

## የሚያዩትን ሳይሆን የሚያስቡትን

ፕ/ር መኩሪያ የተለያለ አስተሳሰቦች ማሕበረሰባዊ እድገትን ለማምጣት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በማጣቀስ ያሳያሉ:: «ለምሳሌ ነጻ ፕሬስ በልጽጎባታል በምትባለው በእንግሊዝ ያሉ ጋዜጦች የኮንሰርቫቲቭ፣ ወይም የሌበር ፓርቲዎችን አመለካከት ደጋፊ ሆነው ይጽፋሉ:: ሌሎቹም እንዲሁ የተለያዩ የፖለቲካ ፍልስፍናዎችን ያራምዳሉ:: ይህ ሁሉ የሙያውን ስነ ምግባር እስከጠበቀ ድረስ የሚፈለግና ትክክለኛ ነገር ነው:: የ1984ቱን የፕሬስ አዋጅ ተከትሎ ብዙ የሕትመት ውጤቶችን ማየታችን ከአማራጭ ሚዲያዎች ለሚጠበቀው የሃሳብ መንሸራሸር የማይተካ ሚና ነበረው::» ቢሉም የራሱ ችግሮች የነበሩበት እንደነበር ግን ይጠቅሳሉ::

«የመንግስት ጋዜጦች የመንግስትን የግሉ ደግሞ የተወሰኑ ፓርቲዎችን የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ አጫፋሪዎች ሆነው ተከሰቱ:: የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ወደ ዘርፉ የሚገቡት ወገኖች ሙያውን የማያውቁ የስነ ምግባር ደንቦቹን እንዳሻቸው የሚጥሱ መሆናቸው ነው::» ሲሉ ያስታውሳሉ:: ከቀድመው ማስታወቂያ ሚ/ር ያገኘናቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የ1984ቱ የፕሬስ ሕግ ከወጣ በኋላ በነበሩት አምስት ተከታታይ አመታት ብቻ ለ385 ጋዜጦችና መጽሔቶች የሕትመት ፈቃድ የተሰጠ ቢሆንም እድገቱ ወቅቱን ጠብቆ ከመጓዝ ይልቅ ማሽቆልቆሉ ይታወሳል::

የፕሬስ ሕጉ እንደወጣ ለንባብ ከበቁትና በአገሪቱ ነፃ ፕሬስ ወሰጥ ጥንካሬያቸውን ጠብቀው ከዘለቁት የሕትመት ውጤቶች በአጥበያ ኮከብየማስታወቂያ ስራ ኃላ/የተ/የግል ማሕበር ስር ትታተም የነበረችው ጦቢያ ዋና አዘጋጅ የነበሩት አቶ ብሩ ፀጋዬ ወቅቱን አንፀባራቂው ጅምር» ሲሉ ይጠሩታል:: «በየዕለቱ አዳዲስ የሕትመት ውጤቶችን ለማየት ችለን ነበር:: ነፃ ፕሬሶች በየትኛውም የዓለም ክፍል ማሕበረሰቡን የመምራት ሚና በመጫወት ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን ተጫውተዋል::» በማለት በአገራችን ያጋጠመው ግን እድገቱን ጠብቆ ከመጓዝ ይልቅ ወድቀቱን ያፋጠነ እንደነበር በቅሬታ ይገልፃሉ::

«ያን ያህል የህትመት ፈቃድ ተሰጥቷል በተባለባቸው አመታት ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ከጨዋታ ውጪነዋል:: ከነበሩት ውስጥም ሚዛናዊና ሀቀኛ መረጃዎችን ለሕዝቡ የሚያቀርቡ፣ በዘርፉ ባለሙያዎች የሚመሩና በሂደት የጠራ ሙያዊ መስመር እየያዙ የነበሩ ቢታዩም የብዙዎቹ የማንነት ፍሬ አንፀባራቂውን ጅምር አምክኖታል:: እንዲያውም ዛሬ ላይ ሆነው በወቅቱ የነበረውን አካሄድ አምርረው የሚተቹ ሆኖም በጊዜው የሕትመት ፈቃድ አውጥተው የሌለ ጦር ፈጥረው ስለዘመቻቸው የሚዘግቡ ሁሉ ነበሩ::...» እንደ አቶ ብሩ ፀጋዬ እምነት የሚያዩትን ሳይሆን የሚያስቡትን የመዘገብ ጋዜጠኝነት በመንግስት በኩል ከሚደረገው ጫና ጋር ተደራርቦ በአሁኑ ወቅት የሚያውን መቀዛቀዝ ፈጥሮታል::

«ይሁንና ግን ...» ይላሉ አቶ ብሩ «... ጋዜጠኞቹ እንማን ናቸው? ማን ነበሩ? ከማለታችን በፊት የተከተሉትን መስመር ለምን መረጡ? የሕብረተሰቡ አስተዋጽኦስ ምንድነው? ማለት አለብን::» በማለት አሁን ባሉት የነጻ ፕሬሶች ውስጥም በድፍረት የገቡ ወገኖች ኢ-ስነ ምግባራዊ በሆነ መንገድ እውነታውን ሳይሆን ምኞታቸውን የሚጽፉ እንዳሉ ጠቁመዋል::

ፕ/ር ዘካሪያስ ቀነዓ በበኩላቸው በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ:: «የእስካሁን የሚዲያዎቻችን ታሪክ፣ አጠቃቀማችንና ያመጡት ውጤት መገምገም ያለበት ይመስለኛል» ይላሉ::

## ከአመርታዎቹ ጀርባ

የዓለም ጋዜጦች ማሕበር ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያመለክተው በዓለም ላይ ከፍተኛ የስርጭት መጠን ካላቸው 10 ምርጥ ጋዜጦች ውስጥ ሰባቱ በጃፓን ይገኛሉ:: የስርጭት መጠኑ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኘው «ዮሚዩሪ ሺምቡን» በአንድ ህትመት ከ14 ሚሊዮን በላይ ቅጅዎችን ለአንባቢዎቹ ያቀርባል:: በከፍተኛ ስርጭታቸው በሚታወቁ ጋዜጦች ዙርያ የተደረጉ ጥናቶች ለስኬቶቹ በምክንያትነት የሚያቀርቡት ሚዲያዎቹ በጊዜ ሂደት ውስጥ በአንባቢዎቻቸው እምነት የሚጣልባቸው ሆነው መገኘታቸው ሲሆን ስኬታቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ ያስቻላቸው ደግሞ በብሔራዊ ጉዳዮችና በኤዲቶሪያል ፓሊሲያቸው የማይናወጥ አቋማቸውና መሰል ዝርዝሮችን ነው::

ወደአገራችን ሚዲያዎች ስንመለስ የጋዜጦች ቅጅ የመዋዠቅ ሁኔታ ቢያሳይም ተጠቃሽ የጊዜ ምዕራፎችን እናገኛለን:: ከእነዚህ የታወሰኑት የቀድሞውን ፕ/ት ወታደራዊ ዝግጅቶችና የግል ጉዳዮች፣ የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩት የአቶ ታምራት ላይኔ መታሰር፣ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት፣ የ1993ቱ የሕወኃት ክፍፍልና በመጨረሻም የ1997ቱ አጠቃላይ ምርጫ ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ታሪካዊ ክስተቶች ከፍተኛ ትኩረት ስለሳቡበት ሁኔታ የተለያዩ ምክንያቶች ይቀርባሉ::

## ስሱዎቹ ክስተቶች

ከላይ በተጠቀሱት ሁነቶች ወቅት የህትመት ቅጅ የማሻቀቡ ምስጢር ከጉዳዮቹ ስሱነት/sensitivity/ አንፃር የሚመለከቱት ወገኖች አሉ:: ማንነታቸው እንዲለገጽ ያልፈለጉና ቀደም ሲል በአንድ ወርሃዊ መጽሔት ላይ በዋና አዘጋጅነት ሲሰሩ የነበሩ ጋዜጠኛ ያላቸውን እምነት ሲገልፁ «ክንውኖቹ የነበራቸው ማሕበራዊ ፋይዳ እያንዳንዱን ዜጋ በግለሰብ ደረጃ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚነኩ ነበሩ:: የአቶ ታምራት የሙስና ቅሌት የድርጅቱን አመራር ገመና ለመጀመርያ ጊዜ የገለጠ ነበር:: የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ልጆቹን ሲገብር የቆየበትንና መክኖ የቀረውን ታሪካዊ የባለቤትነት ጥያቄ ሊመልስ ይችላል የሚል ተስፋ መፈንጠቁ አልረም::» ካሉ በኋላ የሕወኃት መሰንጠቅ ስለነበረው አንድምታ ሲገልፁ

«ይህ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት ትርጉም ነበረው:: የመጀመያው እንደፈላጭ ቆራጭ የሚቆጥረው ድርጅት መከፋፈል በራሱ ጊዜ ነፃነቱን እንዳጎናፀፈው የሚሰማው ሲሆን የውዝግቡን ትክክለኛ ምንጭ በአንፃራዊ ሁኔታም ቢሆን ሊያገኝ የሚችለው ከነፃው ፕሬስ እንደሆነ ያውቀዋል:: በሌላ በኩል በገዢው ፓርቲ ውስጥ የአንጋፋው ድርጅት በዚያ መንገድ መሰንጠቅ ወላፈኑ ለአገሪቱ ይተርፋል የሚል ስጋት ነበር::» በማለት ማሕበረሰቡ አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት የነበረው ተነሳሽነት በሕትመት ሚዲያው ላይ የፈጠረውን ለውጥ ያስታውሳሉ:: አያይዘውም «ጥልቀት ያላቸው ዳሰሳዎችን የሚያቀርቡ፣ ቀጥተኛና ደፋሮች እንዲሁም አንባቢው ማወቅ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ፈልፍለው የሚያወጡ» ሲሉ በወቅቱ የነበሩትን የሕትመት ውጤቶች ያወድሷቸዋል::

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት መፈንዳት ያልተጠበቀ ይመስላል:: በተለይ በሁለቱ አገር መንግስታት መካከል ጠንካራ የወዳጅነት ግንኙነቶችና ውሎች ነበሩ:: አንድ የምጣኔ ኃብት ባለሙያ እንዳሉት ባልተለመደ ሁኔታ ለሰባት አመታት ያህል በአንድ ገንዘብ በመገልገል አገራችን የማታውቀው እዳ ከፋይ ሆና ቆይታለች:: ይህን ኢ-ፍትሃዊ አካሄድ አበክረው የሚቃወሙ ጽሁፎች በነጻው ፕሬስ ላይ ሲስተናገዱ ቆይተዋል:: «እንደችግር የተቆተረው ይህ ሊሆን ይችላል::...»ይላሉ እኚህ ባለሙያ ከምርጫ 97 በኋላ ጠንካራ አቋም ባላቸው ጋዜጦች ላይ የሚደረገው ጫናም ይህንኑ ያስታውሳል::

## የውዝግቡ መንስኤዎች

በምርጫ 97ትና በነፃው ፕሬስ እንቅስቃሴዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ለታሪካዊው ውዝግብ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግብአቶች አሉ:: የመጀመሪያው የገዢው ፓርቲ ሕዝባዊ ቅቡልነትን ማጣት ሲሆን ገዢው ፓርቲ በበኩሉ ውስጡን ከመፈተሽ ይልቅ ተቋማቱን በባላንጣነት ፈረጃቸው:: የኢኒሽየቲቭ አፍሪካ የፕግርራም ማኔጀር የነበሩት ዶ/ር ታደሰ ብሩ በወቅቱ አቅርበውት በነበረ አንድ ጥናታዊ ጽሁፋቸው ኢህአዴግ የሕጋዊ ተቀባይነት ችግር እንዳለበት ሲገልፁ በምርጫ ሽፋን የሚያስመዘግባቸው «ውጤቶች» ወደ መቶ በመቶ እየተጠጉበት «ተቸግሯል» ብለውታል:: ሕዝቡ ለዘመናት በምርጫ የመወሰን መብቱን በእጁ ያለማስገባቱ፣ የምርጫ ተዋናዮቹ ለምርጫ ስነ ምግባር ተገዢ ሳይሆኑ መቆየታቸውና ይህም በፈጠረው ጫና የነበረው የለውጥ ተነሳሽነት የመሩት የነጻው ሚዲያ ቤተሰቦች ነበሩ::

«በእርግጥ...» ይላሉ የጦቢያ መጽሔት ዋና አዘጋጅ የነበሩት አቶ ብሩ ፀጋዬ:: «... አንድ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያ በየትኛውም ወቅት ቢሆን ስሱ እና ስሜት ቀስቃሽ ጉዳዮችን ከሕዝቡ ውስጥ እያወጣ መልሶ ከማቅረብ ይልቅ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመመርመር ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃዎችን በሰከነ መንገድ በማቅረብ ይህን የመሪነት ሚናውን ቢወጣ ዘርፉ እንዲያድግና ሙሉ ኃይሉን በሂደት ለመጎናጸፍ ያስችለው ነበር::»

መኩሪያ መካሻ በበኩላቸው «በአፍሪካ ደረጃ መንግስታት መተቸትና መወቀስ አይሹም:: ወደተቃዋሚዎች ስንመጣ ደግሞ የመንግስት ሚዲያዎችን መጠቀም ስለማይችሉ የግሉን ሚዲያ እስከመግዛት ይደርሳሉ:: ሕበረተሰቡ በበኩሉ የማሚደርሱበትን ችግሮች በሚዲያዎች በኩል እንዲገለፁለት ይፈልጋል::» በማለት የሁኔታዎቹን ወስብስብነት በማስታወስ «እነዚህ ስሱ ሁኔታዎች ያለመቻቻልን ሊያመጡ ይችላሉ:: በዚህ ወሳኝ ወቅት የሚዲያ ባለሙያው ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይጠበቅበታል:: » ሲሉ ያስጠነቅቃሉ::

## እየከሰመ ያለው ፕሬስ መጻኢ ዕጣ

ምርጫ 97ትን ተከትሎ ከሃያ በላይ ጋዜጦች በሕጋዊ እገዳና በፖለቲካዊ ጫናዎች ህትመታቸውን ያቋረጡ ሲሆን በርካታ የነፃው ፕሬስ አባላትም ለእስር መዳረጋቸው ይታወሳል:: ይህን ወቅት ብዙዎች «የጨለማው ዘመን» ሲሉ ይጠሩታል:: ምርጫውን ተከትሎ ያጋጠመው የብዙ ዜጎች ሕይወት መቀጠፍና ማሕበራዊ ምስቅልቅል እንዳለ ሆኖ ከዚያ በኋላ የተወሰዱት እርምጃዎች እየከሰመ የመጣውን ነፃ ፕሬስ ከጨለማው ዘመን የሚያላቅቁት አይመስሉም::

የዓለም ጋዜጦች ማሕበር ይፋ ባደረገው መረጃ በየዕለቱ አንድ ቢሊዮን ያሕል ሰዎች ጋዜጣ የሚያነቡ ሲሆን ይህም ከዓለማችን ስድስት ሰዎች አንዱ ማለት ነው:: እንደ አሜሪካ ባሉ አገራት የጋዜጦቹና አንባቢዎቹ ቁጥር የሚመጣጠን ሲሆን በአራችን በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በመንግስት ይዞታ ስር ሆነው የሚታተሙትን ጨምሮ 80 ሚሊዮን ሕዝብ ባላቱ አገር የቅጅ መጠናቸው ከ50 ሺህ አይበልጥም:: ይህም ለአንድ ጋዜጣ ከ1400 በላይ አንባቢ ይደርሳል ማለት ነው:: «መጀመሪያውኑም የአገራችን የንባብ ባሕል ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ጋር ሲነፃፀር እንኳ በጣም ደካማ ነው:: አሁን ደግሞ ሁኔታው የባሰ ሆኗል::» ሲሉ ፕ/ር መኩሪያ በመጻኢ ሁኔታው ያላቸውን ስጋት ይገልፃሉ:: ሌሎች ደግሞ ከምርጫው በኋላ የወጣው የፕሬስ ሕግ ነጻው ፕሬስ የተደቀነበትን አደጋ የበለጠ የሚያባብስ ነው ይላሉ:: በተዘዋዋሪ የሚደረጉት ፖለቲካዊ ጫናዎችም አንዳንዶች ሕትመታቸውን እንዲያቋርጡ አስገድዷቸዋል::

ጥቅምት 7 ቀን 2002 ዓ.ም ለንባብ የበቃቸው «አዲስ ነገር» ጋዜጣ በርዕሰ አንቀጽ አምዷ ይፋ ያደረገችው ነጥብ ችግሩን ከመጠቆም አልፎ መወሰድ የነበረባቸውን አዎንታዊ እርምጃዎች ያመላከተ ነበር የሚል መከራከርያ ሲቀርብ ቆይቷል:: በርዕሰ አንቀጽ ላይ ከሰፈሩት መልዕክቶች ዋንኛው «አዲስ ነገርን እና ባልደረቦቿን ቢቻል ከሕዝብ ለማቃቀር ባይቻል ደግሞ መፃፋቸውን እንዲያቆሙ ጥረት እየተደረገ ነው::» የሚለው ሲሆን አዘጋጆቹ የዜጎችን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ለመጠበቅ የተመሰረቱ ተቋማት በተቃራኒው ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ማፈኛ እንዳይሆኑ ሲሉ አሳስበው ነበር:: በመጨረሻ ከምርጫ 97 በኋላ ከፍተኛ ተነባቢነትን አትርፋ የነበረችው ጋዜጣ ባልደረቦች ደረሰብን ባሉት ጫና ሕትመታቸውን ሲያቆሙና አብዛኞቹም ሲሰደዱ በመንግስት በኩል ይታይ የነበረው ምላሽ ለሌሎቹ የፕሬስ ተቋማትም እንደመልዕክት ተቆጥሯል::

## «ሰዎች የሚተባበሩት ትብብሩ...

እድልን ያጐናፅፋል::

ሪፐብሊኮች ከንጉሳዊ ሥርዓቶች በበለጠ የተረጋጉ ይሆናል፤ ይበልጥ እራሳቸውን መከላከል የሚችሉና ግዛታቸውን በጦርነት በማስፋፋት ረገድ ይበልጥ ስኬታማ ይሆናሉ:: በተወሰነ መልኩ የሰውን ልጅ ግለኝነት በማዝቀጣቸው ወይም በመመከታቸው ምክንያት ሳይሆን፣ ይልቁንም ይበልጥ የሰፋ ነፃነት በመስጠታቸውና በዚህም ጀግና፣ መጨቆንን የማይሻ፣ በራሱ ሚተማመን ግለሰቦችን በመፍጠራቸው ምክንያት እንጂ::

### ስሪፐብሊኩ ዘለቄታ

የሰው ልጅ ተፈጥሮ ምንም ሆነ ምን፣ ሪፐብሊኩ ላይ የተጋረጠው ችግር ወደ ጨቋኝ ሥርዓት (tyranny) አለመለወጡን ማረጋገጡ ወይም የመፈረካከስ (የመውደቅ) ሂደቱን በተቻለ መጠን ማራዘሙ ላይ ነው:: ሪፐብሊኮች የተረጋጉ እንደሆኑ መቀጠል የሚችሉት ሰዎች ማንም ቢሆን የተቀሩትን ሁሉ በቀላሉ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን መጠን ያለፈ ሥልጣን እንዲኖረው ባለመፍቀድ እርስ በርሳቸው ፈጠራ በተሞላበት መንገድ እንዲፎካከሩ ባስቻሉ ጊዜ ብቻ ነው::

ማኪያቬሊ ተግባራዊ የመንግስት ዓይነቶች እንደየሕዝባቸው ሁኔታ እንደሚለያዩ ተረድቷል፤ ነገር ግን እሱ እንደሚያስበው፣ ከሁሉም የተሻለው የመንግስት ዓይነት ቅይጥ ሕገ-መንግስት ያለው ሪፐብሊክ ነው:: ሕዝቡ በመንግስት ላይ ትርጉም ያለው ድርሻ ሲኖረው ሁሉም በክብራቸው፣ በንብረታቸው እና በሰውነታቸው የዋስትና ስሜት እንዲኖራቸው ያስችላል:: ሕጐቹ ግልፅ እና በሕዝብ የሚታወቁ ሊሆኑ ይገባል፡- ዜጐቹ በከፍተኛ የእርግጠኛነት መጠን ሳይቀጡ መስራት የሚችሉትንና የማይችሉትን ሊያውቁ ይገባል::

ጥቅል ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና መበረታታት ያለበት ሲሆን፣ ከመጠን ያለፈ የግለሰብ ሀብት እና ቅንጦት በሕጐች መገደብ ይኖርበታል:: ለዜጐች ጥቅሞች ጉልህ እውቅና ሊሰጥ ይገባል፤ እንዲሁም ክብር እና ዝና ለሚሹ ሁሉ በመንግስታዊ አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት::

ሕዝባዊ ሞራልን ለመገንባት እና ለመጠበቅ መንግስታዊ ሃይማኖት መኖር አለበት:: ሆኖም ይህ ሃይማኖት ደካማነትንና ተገዢነትን የሚያበረታታው ክርስትና መሆን የለበትም::

ሪፐብሊኩን ለመጠበቅም ሆነ በወረራ ጦርነቶች ይዞታውን ለማስፋፋት በዜጐች የተዋቀረ ሠራዊት ሊኖር ይገባል:: ሠራዊቱ ለትምህርታዊ እና ለወታደራዊ ዓላማ ይተጋል፡- በዜጐች ዘንድ ለባለስልጣን ክብር መስጠትን፣ አርበኝነትን እና ወታደራዊ ሥነ-ምግባርን ያሰርፃል:: በተጨማሪም ግለሰባዊ ህልሞች (ምኞቶች) ተፈጥሯዊ እና ጤናማ መገለጫቸውን የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል:: በሪፐብሊክ ውስጥ ያለ ህይወት እጅግ የተመቸ መሆንም የለበትም:: በችግር እና በአደጋ ጊዜ ህብረተሰባዊ ጥምረት እና ጥንካሬ ዝግጁነታቸው መረጋገጥ አለበት:: እንዲህ ያሉ ጊዜያት በህዝቡ ያለውን መልካምነት በማውጣት በአብሮነት እንዲሰሩ ብርታት ይሆኗቸዋል::...


### በአጭሩ

በአጭሩ ማኪያቬሊ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን የተለያየ ዓይነት እና መጠን ያለው ሥልጣን በመያዝና የያዙትንም ላለማጣት እና የበለጠ ለመያዝ የሚሞክሩ የግለሰቦች እንቅስቃሴ እንደሆነ አድርጐ ይወስደዋል:: ዘ ፕሪንስ እና ዘ ዲስኮርሰስ ጥብቅ በሆነ መልኩ የተለያዩ አይደሉም፤ እርስ በርስ የሚቃረኑም አይደሉም:: ሁለቱም የሰው ልጅ ተፈጥሮ ግለሰባዊ፣ ተፎካካሪ እና አስፈላጊ ሲሆንም ጨካኝ እና ሥርዓት አልበኛ የመሆኑን ምልከታ ይጋራሉ:: ዘ ፕሪንስ ልዑሉ ለራሱ በሚጠቅመው መልኩ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ ኃይሎችን እንዴት እንደሚቆጣጠር የሚያሳይ ፅሁፍ ነው፤ ዘ ዲስኮርሰስ ደግሞ እነዚህ ኃይሎች አንድነትን እና ሕዝባዊ ደህንነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ የሚጠቁም ምልከታ ነው:: ሆኖም በሁለቱም ለይ የሚገኙት ኃይሎች ተመሣሣይ ናቸው::...

ለማኪያቬሊ ሥልጣን ተግባራዊ የሚሆንባቸው የመጨረሻ ውጤቶች የቀዳሚነት ሳይሆን የሁለተኛነት ደረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ልብ ማለት አይቀርም:: ማኪያቬሊ በየትኛውም መደበኛ መመዘኛዎች ጨካኝ እና ሞራል የለሽ የሆነውን ጨቋኙን ሴዛሬ ቦርጂያን የሞራል ጠባዩን ሳይሆን ብቁነቱን ያደንቅለታል:: በጊዜው ከነበሩም ሆነ ከቀደሙት ከአብዛኞዎቹ በተቃራኒው፣ ፖለቲካ ከሞራል አኳያ ገለልተኛ የሆነ ጥበብ ስለመሆኑ ማኪያቬሊ ያምናል:: ከማንም በላይ ይህንን ፖለቲካዊ ክስተቶች እና ግንኙነቶች ሊተነተኑ የሚገባበትን ጉልህ ምልከታ የማበርከቱ እውነታ ነው፣ የእርሱ ልፋት በፖለቲካ እሳቤ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ ቦታ ሊሰጠው ያስቻለው::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com




ዳሰሳ

በእዩኤል መኮንን

# ህልም ብቻ እንዳይሆን የምፈልገው መፅሐፍ

**የመፅሐፍ ርዕስ:- ያልተፈታው ህልም**

**ደራሲ:- ሕዝቅያስ ፀጋዬ**

**የገፅ ብዛት:- 263**

**ዋጋ:- 30 ብር**




የአገራችን ሃያስያንን ብዙ ገዜ የሚያጨቃጭቅ ነገር አለ:: አዲሱ ትወልድ ምንም የፈጠራ ስራ መስራት እንደማይችል እና ስለኢትዮጵያ የስነ-ፅሁፍ እድገት ሲወራ አንድ ትውልድ ብቻ ስሙ ሲወደስ ይከርማል:: በአዲሱ ትውልድ ውስጥም የአገሪቱ የስነ - ፅሁፍ እንዲያድግ የራሳቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የአዲስ ትውልድ አባላት እየተፈጠሩ ነው:: አዳዲስ ፀሐፊዎችን ልናደንቃቸው ይገባል፤ «በርቱ» ብለን ኮፍያችንን ብድግ ልናደርግላቸውም ጭምር::

በቅርቡ ገበያ ላይ ከዋሉ መጽሐፍት አንዱ «ያልተፈታው ህልም» የሚል ልብ-ወለድ መፅሐፍ ነው:: የመጽሐፉ የሽፈን ገፅ ለየት ያለ ምስልን የያዘ ሲሆን ኢትዮጵያዊ ተወንጫፊ ሚሳዔል፣ አሜሪካዊት መሆኗን ባደረገችው ባርኔጣ የምታሳይ ሴት (በቆረጣ)፣ ኤርትራ ሳትገነጠል የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታ፣ ኮከብ አልባው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ይዟል:: መጽሐፍን በሽፋኑ ይዘቱን መገመት ባይቻልም በራሱ የሚናገረው ነገር አለ በማለት ገዝቼው ወደ ቤቴ ገባሁ::

ታሪኩ የሚጀምረው እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ መጽሐፎች በትረካ ሳይሆን በድርጊት ነው፤ ልክ እንደ ሆሊውድ ፊልም:: በኤርትራ ጦርነት ወቅት እንደተፃፈ የሚገልፀው ይህ መፅሀፍ ታሪክ በሰኔና ሰኞ ግጥጥሞሽ ይጀምራል:: እንደ ኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ሰኔ 1 1990 ሰኞ ዋሺግተን ዲሲ ነጩ ቤተ-መንግስት ውስጥ:: ፀሐፊው በድፍረት አሉ ያላቸውን ስንክሳሮች በልብ-ወለድ መልክ ጠቅሷቸዋል:: ይህንን የሚያሳይ አንቀፆች ላቅርብ:: ከገጽ 44-45 ሰፍሯል::

«ይህ የሆነበት ትልቁ ምክንያት ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ፍቅር የያዛት ከኛ ሳይሆን ከቻይናና ከሩሲያ ነው:: ቻይና በአፍሪካውያን ዘንድ ተሰሚነቱን ማግኘት ትፈልጋለች:: እቃዎችን በርካሽ ዋጋ ወደ አፍሪካ የምታስገባው ተሰሚነቷን ለማጠናከር ነው:: የቻይና የኢኮኖሚ ግስጋሴ አስፈሪ እየሆነ ነው:: ቻይና በአፍሪካ ላይ ያላትን ተሰሚነት ለማጠናከር እንደ ኢትዮጵያ ካለች በአፍሪካዊያን ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ካላት ሃገር የበለጠ እንደሌለ ስለምታወቅ የኢትዮጵያን የኒኩሌር ፕሮግራም መጀመርና ማበልፀግ «እንቢ» የምትልበት አቋም የላትም:: ባሁኑ ወቅት እና ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ትልልቅ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የቻይና ኩባንያዎች እንደሚሰሩ ጥርጥር የለውም:: ቻይናም ለሀገሯ ኩባንያዎች ሕልውና ስትል የኢትዮጲያን አቋም ትቀበላለች::

ሌላው ታሪካዊ ጠላታችን ሩሲያ ከኢትዮጵያ ጋር እያሳየች ያለችው ፍቅር እራስ ምታት ነው:: ሩሲያኖቹ የገንዘብ ችግር እንዳለባቸው የታወቀ ነው:: ገንዘብ ካገኙ የኒኩለር ፕሮግራሙን ለኢትዮጵያ የማይሰጡበት ምክንያት የለም:: ሩሲያ ለኢትዮጵያ ከገንዘብም በላይ ፍቅራቸው ከጥንት የጀመረ ነው:: ግንኙነታቸው የመንግስት ግንኙነት ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ነው:: ሐምሌ 28 ቀን 1888 ዓ.ም. የሞስኮ ንጉሠ ነገሥት በኢጣሊያን ጦርነት ጊዜ የተጎዱትን ኢትዮጵያውያንን የህክምና ዕርዳታ እንዲሰጥ ለንጉስ ሚኒልክ የህክምና ቡድን ልኳል:: ሁለቱም ሃገሮች የምስራቅ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ናቸው:: ለፍቅራቸው ሃይማኖታቸውም አስተዋጽኦ አለው:: እውቁ የሩሲያ ደራሲ አሌክሳንደር ፑሺኪን በአያቱ ኢትዮጵያው ስለሆነ ግንኙነታቸውን የበለጠ ያጠናክረዋል:: ከዚህ በተጨማሪ የኢትጵጵያ የመጨረሻ ንጉስ ከሥልጣን በወታደራዊ መንግስት ሲወርዱ ወታደራዊ መንግስት ሰዓቱን ወደ እኛ ሲያዞያ በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው ጂሚ ካርተር ከንጉሱ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ስለ ነበር ለመንግስቱ እውቅና ባመስጠቱ መንግስቱ ፊቱን ወደ ምስራቁ ዓለም በማዞሩ የዛሬው ራስ ምታት ውስጥ ገባን::

ሰዎቹ ፋብሪካውን ሊሸጡልን ያልፈለጉት የኒኩለር ባለቤት የመሆን እቅድ ስላላቸው ነው:: የኛ መንግስት ፋብሪካውን የጦር መሳሪያ ፋብሪካ ስለሆነ

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

## ኮሜዲያን ደረጄ ኃይሌ ለአዲስ ዓመት አዲስ ቪሲዲ እንደሚለቅ አስታወቀ

ኮሜዲያን ደረጃ ኃይሌ መጪውን አዲስ አመት ምክንያት በማድረግ «የሳቅ እልፍኝ» የተሰኘ አዲስ ቪሲዲ በማስተር ሳውንድ ሙዚቃ ቤት አሳታሚነት ለገበያ ለማቅረብ ቅድመ ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፀ::

ከሚች የሙያ አጋሩ ሀብቴ ምትኩ ጋር በመሆን የተለያዩ የኮሜዲ ስራዎችን ከሀያ አመታት በላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሲያቀርብ የቆየው ኮሜዲያን ደረጃ ኃይሌ፤ ጓደኛውና የሙያ አጋሩ ኮሜዲያን ሐብቴ ምትኩ በ1999 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ወዲህ የራሱን ስራዎች በቪሲዲ መልክ ሲያቅርብ ይህ የመጀመሪያ ዚዜው ነው::

በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ዘና እያደረገ ቁም ነገር እንደሚያስጨብጥ የተነገረለት የኮሜዲያን ደረጀ አዲስ ቨሲዲ ከአመት በዓሉ በፊት ለገበያ እንደሚቀርብ ኮሜዲያኑ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል::

## በአማርኛ ኖ ተጻፈ ጽሁፍ

ደሳለኝ ስዩም

desalegnseyoum@yahoo.com



# ክተፍ እንግዲህ 1

የአባታችን ሰላም በናንተም ዘንድ ይሁን!

ስለከተፋ አሁን ላውጋችሁ?!

ያው እንደነገርኳችሁ አንድ መከረኛ የሩቅ ዘመድ (ከብዙዎቹ አንድ) አለኝ:: «ከተፋ» የሚለውን ዘመነኛ ቃል ሊተረጉመው አምሮት እንዲህ አለ::

«ከተፋ የሚለው ቃል ትርጉም መምተርን፣ መሰንጠቅን፣ መቁረጥን፣ መፍለጥን እና መቸፍቸፍን ያመለክታል:: እርግጥ ነው በሀገሪቱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እጥረት አለ:: ይሁና የከተፋ ትርጉም ከዚህ እንደማይበልጥ እርግጠኛ ነኝ:: ይሄውም ቃል ለሽንኩርት፣ ለጐመን፣ ለሥጋ . . . » ብሎ ያሰበውን ሳይጨርስ በሳቅ ታጀበ::

ለመሆኑ ስለምን ተሳቀበት የሚል ቢኖር ማለፊያ ጥያቄ ማንሳቱን ይወቅ:: እነሆም ባደባባይ ለዘመነኞች ስለተረጐመ ተሳቀበት (እንዴት)? እቤቱ ለልጆቹ ቢተረጉም ኖሮ መልካም:: ሲያቀብጠው ባደባባይ በሰው ፊት ከተፋን ለመተርጐም በመሞከሩ ተሳቀበት::

ያጀቡት ሳቀኞች ሆዳቸውን አሚቸው ፀጥ ሲሉ፣ «ምነው?» ሲል ጥያቄ አቀረበ:: ሳቀኞች ባይደክሙ ኖሮ በተጨማሪ ሳቅ በታጀቡ ነበር:: ይሁንና ዝም አሉት::

በኩርፊያ የተለያቸው ዘመዴ በሌላ ግዜ የሆነውን ኹሉ ለኔ አዋየኝ:: እኔም እንዲህ ስል (ሞደርን ሌክቸር) ሰጠሁት::

«ዘመዴ ሆይ! አንተ የዋህ ነህና እንደየዋህነትህ መለሰልህ:: ግና ከዘመኑ ስለራቅህ ትምህርት ቤት ልትገባ ይገባሀል:: እርግጥ «ከተፋን» እንደብሂልህ ተርጉመሀል:: ይሁንና የኔ የአሁኑ ስራ በራሱ ከተፋ ነው::

«እንዴት?»

«ግድ የለህም እየቆየሁ በምሳሌ ስተነትንልህ ይገባሀል:: የከተፋን ትርጉም አይደል የፈለከው?»

«አው የከተፋን ትርጉም::»

«ከተፋማ . . . እንዴት መሰለህ? . . . ቆይ በፈርጅ በፈርጅ፣ በብልት በብልት ላድርገውና . . . » ሳያስጨርሰኝ ዘመዴ ጣልቃ ገባ::

«እህ . . . እኔስ እንግድያ ምን አልኩ?»

«ምን አልክ?»

«ከተፋ በፈርጅ በፈርጁ፣ በብልት በብልት . . . »

በተራዬ ጣልቃ ገባሁ፤ «የለም እንዲያ አይደለም:: እኔ እንደሱ ልተረጉም አልሞከርኩም:: ከተፋን ለምሳሌ . . . ስዕል ከተፋ ታውቃለህ?»

«እሱ ደግሞ ምንድ ነው?»

«ስዕል ከታፊዎች አሉ:: እነዚህ እንዴት መሰሉህ . . . ይሄውልህ በየአውቶብስ ፌርማታው ወይም በሲኒማ በር ላይ ሰው ሰብሰብ ሲል ብጣሽ ወረቀትና እስክርቢቶ ይዘው የሰው ወይም የመኪና ወይም ቅልል የሚላቸውን ስዕል እየሳሉ ስቱዲዮ ለማቋቋም የሚያስችል ምጽዋት የሚለማመኑ ናቸው::»

ዛዲያ በነዚህ ከተፋዎች ላይ ሙያዊ ጥያቄ አይነሳባቸውም:: ማለት «ላይን . . . ከለር . . . ፕሮፖርሽን ምናምን የሚባሉ ጥያቄዎች አይነሱም:: አንዳንድ ግዜ የሳሉትን ስዕል እያሰብክ አንድ ክፍለ ዘመን ልትስቅ ትችላለህ:: እኔ ለምሳሌ አውቶብስ ፌርማታ ላይ አንድ ከታፊ የሳለውን አስታውሳለሁ:: ጥቁር ድንጋይ የመሰለ ነገር ስሏል::

«ምንድነው?» አልኩት::

«ሳጥን» አለኝ::

«እንዲህ አይነት ሳጥን በምድረ-ገጽ ተሰርቶ አያውቅም» ስለው ምን አለኝ መሰለህ?

«'ምልህ አብስትራት ነው:: እንደፈለክ ልትተረጉመው ትችላለህ» አለኝ::

ዘመዴ ግራ በመጋባትና በተመስጦ መካከል ሆኖ እየተሰማኝ ስለመሰለኝ የበለጠ ለማብራራት ሌላ ምሳሌ አነሳሁ::

«የሙዚቀኛስ ከታፊ እንዳለ ታውቃለህ?»

«እንዴት ማለት?»

«በቃ መጠጥ ቤት ወይም ዳንስ ቤት ውስጥ ሙያ የሚላካ የለም:: በሌላ አነጋገር እንደ አይዶል ከምት፣ ከቅኝት፣ ከሪትም ወጣኽ፤ ግጥም ቀየርክ፣ አሳጠርክ፣ . . . ሳትባል የምትዘፍንበት ነው::»

በነገራችን ላይ ስለዘፈን ግጥም ከተነሳ . . . አንድ ግዜ፣

«ምናለ ቀርበሽ ብትረጅው ጉዳዬን» የሚለው የዘፈን ግጥም «ምናለ ቀልጠሽ ብትረጅው ጉዳዬን» ተብሎ ሲዘፈን ሰምቻለሁ::

በሌላ ግዜ ደግሞ «ወገኔ አለቀ በወሲብ እሳት» በሚል ዘፈን ላይ «ኡኡ ቆጣሪ መልሱ የሚል (ፊቸሪንግ) ገብቶበት ሲዘፈን አስታውሳለሁ::

ዘመዴ ከአድማጭነት ወደ ተሳታፊነት ተሸጋገረ::

«እርግጥ ነው ከተፋን እየተረጐምከው ነው:: ይሁንና ግሱን ሳይሆን ፍካሬያዊ ስድቡን ነው የተረጐምከው:: በመንገድ አናናስ እየከተፉ የሚሸጡትን ምን ትላቸዋለህ?» አለኝ::

«አይ ዘመዴ! እነሱማ 'ሻጭ' ነው የሚባሉት ወይም በንግድ ስራ የተሰማሩ ወገኖቻችን::»

«የለም፤ ከተግባራቸው አንፃር» አለኝ ያልገባኝ መስሎት::

«እሱ እንኳ ጥናት ያስፈልገዋል» አልኩት::

«እንዴት?»

«ከተግባራቸው አንፃር ለመፈረጅ መደራጀት አለመደራጀታቸውን፣ ኪራይ ሰብሳቢ መሆን አለመሆናቸውን፣ እንዲሁም ልማታዊ አስተሳሰብ ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን መገምገም ይኖርብኛል ብዬ ነው» አልኩት::

ዘመዴ የጠረኗቸውን ቃላት ስለሚፈራቸው እኔንም ፈራኝ:: እና ጥሎኝ ሄደ:: እኔ ግን ስለከተፋ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ አዘጋጅቼለት ነበር:: (ለናንተ ልንገራችሁ?)

ስለከተፋ መምህራን፤

ከታፊ መምህርን ማለትማ . . . በመደበኝነት ማስተማር አይፈልጉም:: ይልቁንም በየቤቱ እየዞሩ እናስጠና ይላሉ:: ታዲያ በዚህ ሂደት ውስጥ ሙያዊ ነገሮች ሊረሱ ይችላሉ:: ለምሳሌ የትምህርት ጥራት፣ የትምህርት ሥነ-ዘዴ በዚህ የተነሳ ከታፊዎች ብዙ ይስታሉ (በቀን 02 ቤት ለመድረስ ይሉኝታ የሌላቸው አይጠፉም)::

እና አንድ የከተፋ ሰለባ የሆነ ተማሪ «ግዑዝ» የሚል የአማርኛ ቃልን ትርጉም ጠየቀኝ:: ትርጉሙን ለምን እንደጠየቀኝ ጠየኩት:: ተማሪውም ከታፊውን ጠይቆት እንደነበርና ከታፊውም የግዑዝ ትርጉም «ከልጅ ፊት የማይወራ ፀያፍ ነገር» እንደሆነ እንደነገረው ነገረኝ (ቂቂቂቂቂቂ)::

(«ክተፍ እንግዲህ» ትቀጥል?)

ቸሩ ያሰንብተን::

## ሦስተኛው የኢትዮጵያ አመታዊ የስዕል ኤግዚቢሽን በሸራተን አዲስ ተከፈተ



ከነሐሴ 15 እስከ 18/2002 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ የስዕል ኤግዚቢሽን በሸራተን አዲስ ላሊበላ ቦልሩም አዳራሽ የተዘጋጀ ሲሆን በኤግዚቢሽኑም ላይ አርባ ታዋቂ አርቲስቶች 400 የሚጠጉ ስራዎቻቸውን ለዕይታ ቀርበዋል::

ከታዋቂ ሰዓሊያንም መካከል እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜተር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ፣ ሰዓሊ ወርቁ ማሞ፣ እሸቱ ጥሩነህ እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል::

ሸራተን አዲስም የአርቲስቶቹን ግለ-ታሪክ የያዘ የጥበብ ስራዎች በመጽሀፍ መልክ አዘጋጅቷል:: ዝግጅቱም አስደሳች እና የማይረሳ የስዕል ኤግዚቢሽን እንደሚሆን ተጠቁሟል::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# መዝናኛ

## እኔ የምለው! *ከሊዮ*

### ኮሚክ ምስክር

መቼም አለን ከተባለ አለን:: ወዳጆቼ አውራምባ ታይምሶች በምሽትና በሌሊት የድንጋይ ናዳ ወረደባቸው አሉ:: በፈገግታ የሚቀበለን አመለ ሸጋው የጥበቃ ባለሙያ ፊቱ አብጦ፣ ፕላስተር ለጥፎ ሌላ ሰው እንዲመስለን ሆኗል:: «ፊቴ ላይ ድንጋይ አሳረፉብኝ» ቢለኝ «አወይ አጨካከን» አስባለኝ:: ጠ/ሚኒስትሩ ባለፈው ሰሞን መግለጫ ሲሰጡ «ጥያቄዎች ሁሉ የሕዝብ ናቸው ማለት አይቻልም» ያሉት አባባል ትውስ አለኝና «ድንጋዮች ሁሉ የወጣቶች ናቸው ማለት አይቻልም» በሚል ለመተካት አስቤ የእሳቸውን ንግግር ቶሎ ለቀም ማድረግ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮን መምሰል ነው በሚል ተውኩት:: ለመቼ ልቦና፣ ለተመቼ ፅናት ይስጥ፤ ቤት ለፈረሰባቸውም በፈረሰ ይተካ ከማለት ሌላ ምን አማራጭ አለ?

«ሆያ ሆዬ» እንዴት ነበር? «ሆ» እያላችሁ አሳለፋችሁት? «ሆ» ያሉማ «ለካ ተመራርጠው እስኪጨርሱ ነው?» በማለት ገለል ስለመደረጋቸው በንዴት ጠረጴዛ ደብድበው እየጨረሱ ነው አሉ:: ስለ ቡሄ ከተነሳ አይቀር.... ጭፈራዎቹን አያችሁልኝ? ባሉበት የሱስ ዘሮች ጥርሱ የበለዘ አባወራ ጋር ሄደው «እዚያ ማዶ አንድ ዘንዶ.... የኔማ እከሌ ጥርሰ በረዶ» ሲሉ ብሰማ ነገርየው ማድነቅ ነው? መሸርደድ እንድል አድርጎኛል:: እድሜ ጠገብ ባለትዳር ቤት ሄደው «እዚያ ማዶ አንድ ሽምብራ (ያው እዚህ ማዶ ሌላ ሽምብራ).... የኔማ እከሌ/ሊት አዲስ ሙሽራ» ሲሏቸው ባለትዳሮቹም ተቀብለው «እውነት ነው» ሲሉ ብሰማ እውነት ሆይ አገርሽ ወዴት ነው? አስብሎኛል:: ጭፈራና ሽቀላዋ አዋጪ ሳትሆን አትቀርም:: የሚለቅ እኮ ከተገኘ [የሚለቅ ስል ስልጣን መስሏችሁ እንደሳቃችሁ እርግጠኛ ነኝ:: አይደረግም! This is Africa ብሎ ራስን መሸወድ ነው:: የሚለቅ ባራዶች ቋንቋ የሚሰጥ ማለት ነው] እናም የሚለቅ ከተገኘ እንደ አሸን ከፈሉት አክስዮን ማኅበሮች ተርታ ለመደመር የሚያስችል ገንዘብ ያስገኛል:: እኔና ጓደኞቼም ለቫራይቲ ማጋባትና ማፋታት ላይ የሚሰራ አክስዮን ማህበር ለማቋቋም አስበናል:: ሰው ሲያገባ ብቻ ነው እንዴ ምናለ ሲፋታስ በቬሎና በሙሉ ልብስ ተውቦ ቢሆን የሚል ቁጭት የወለደው ነው የኛ አክስዮን ማህበር::

እኔ የምለው! በመገናኛ ብዙሐን የአንድ ሰው ግለ-ታሪክን ማዕከል አድርገው የሚሰሩ ፕሮግራሞች ላይ ለምስክርነት የሚጋበዙ ሰዎች ሰውየውን/ ሴትዮዋን «ቸሩ መድኃኒአለም» ሊያደርጓቸው እኮ ምንም አይቀራቸውም:: «ሩህሩህ፣ የተቸገረ ረጂ፣ ሳይጐርስ የሚያጐርስ፣...» ሲሉ ማን የማናውቃቸው ይመስል እሱ/እሷ እያልን አለቅን እኮ:: አንዳንዶቹ ተገቢ ያልሆነ ምርቃት ሲወርድባቸው «ወይ ማወቅ እና ማየት» እንድንል አድርጐናል:: [ነው የሰው ማንነቱ ሚዲያ ላይ ይቀየራል?] ሰው ግን ለመደነቅ ኢቴቪ ላይ የተሞክሮ እንግዳ መሆን አሊያም መሞት አለበት እንዴ? «ለመደነቅ ብዬ አልሞትም» ያሉትን ሰው ነፍሳቸውን ይማር:: የየመስሪያ ቤቱ ህዝብ ግንኙነቶችስ (አፈ ቀላጤ የሚለው ስም ሳይሻላቸው አይቀርም) ቢሆኑ ስለ ሚሰሬበት ድርጅት ሲናገሩ ሁሌም በጕውን በመቶ አባዝተው ብቻ ከመሆኑ የተነሳ «ይሄ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ነውን?» ያስብላል:: ምስክሩ ሁሉ ኮሚክ ልማታዊ ሆነ አይደል? ይህቺ ኮሚክ አገር ያልያዘችው ስንት ኮሚክ ነገር ብላችሁ ነው? ለማንኛውም በምኞት ሩምታ መደብደብ ባትችሉ እንኳን እንደ ወዳጆቻችን ከድንጋይ ሩምታ ይጠብቃችሁ:: የምለው ካላጣሁ የሳምንት ሰው ይበለን::

## ቅንጭብጭብ

ተያይዘን ገባን:: ካፌው ደንገዝገዝ ባለ ብርሃን ነው የጠበቀን:: ሻማዎች ተለኩሰዋል:: «እንዴት ነው ኑሮ?» አልኳቸው፤ ጨዋታ ለመጀመር:: «አለን፤ ይኸው እንዳለን አለን፤ ፀሃዩ መንግስት በጨለማ እያኖረን» አሉኝ::

«እኔ ምልህ መቼ ነው ይኼ መንግስት ይቅርታ የሚጠይቀን? መቼ ነው . . . አትሰማውም እንዴ ታሪክን እየበለዘና እየከለሰኮ ነው:: ኢህአፓን አለ አቅሙ እያጀገነው ነው:: የተገደለ ሁሉ ፃዲቅና ትክክል የሚሆንበት ምክንያት ምንድነው? ሟችም ለገዛ ሞቱ ዕዳ አለበት የሚባል ነገር አለኮ! የመጀመሪያውን የከተማ ተኩስ የከፈተው ማን ነው? ኢህአፓ ነው:: ደርግ አይደለም:: ኢህአፓ ነው መንግስቱን ለመግደል ሞክሮ የሳተ:: በዚህ ጊዜ ነው መንግስቱ ተበሳጭቶ ፀረ ሕዝቦች ብሎ እርምጃ ያስወሰደባቸው:: ...

የያዙትን የሰነበተ ጦቢያ መጽሔት እየገላለጡ «ተመልከት፤ አሁን የማነብልህን . . . ከደርግ በስተጀርባ በመሆን በግፊት በለውጥ ስም የሕዝብ ንብረት ያስዘረፈ ኢህአፓ፤ የቀድሞ ባለስልጣናትን በአድሃሪ ስም ያስረሸነ ኢህአፓ፤ የእኛ ሶሻሊዝም ነው ትክክል በሎ ተማሪውን ለታንክ የዳረገ ኢህአፓ ነው:: ይህ ሁሉ ትክክል ከሆነ የደርጉ ስህተት ምን ላይ እንደነበረ ትናንት ለተወለዱ ልጆችም ይምታታባቸው አይመስለኝም::

«ለዘመናት በዘመርንበት አፋችን 'ማሪኝ አብዮቴ' ብለናል፤ 'ኢህአፓ ያቸንፋል' ባልንበት. . . 'ቀይ ሽብር ይፋፋም' ብለናል:: ይህንን ሁሉ ያልነው 'ፓርቲያችንን' ጠልተን ነበር? አልነበረም:: 'ፓርቲያችንን' ከድተን ነበር? አልነበረም::ተቃዋሚያችን 'ደርጎች' ስላስገደዱን ነበር? አልነበረም:: 'ፓርቲያችን' የምንለው ዘረክራካ ድርጅት ለቤተ-መንግስቱ ሥልጣን ለመብቃት ያህል ያነሳነው ፖሊሲ እንጂ ለክፉ ቀን የምትሆን ጥርኝ ታክል የትግል ስልት ስላልነበረው ነው...»

ኮለኔሉ መጽሔቱን ወደፊቴ እያቀረቡ «ይህን ያለው ማን እንደሆነ ታውቃህ? ኢህአፓ ትግል ውስጥ የነበረና በአሁኑ ግዜ ውጭ አገር የሚኖር አንድ ሰው:: ተመልከት፤ አንዳንዶቹ እንኳን ህዝቡን ይቅርታ ሊጠይቁት ይፈልጋሉ:: የተቀሩትስ ልባቸው ለምን ደነደነ ያልክ እንደሆነ ወያኔ የልብ ልብ ሰጣቸዋ! በደርግ እጅ የተገደሉትን ወይም ተገድለዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ወይም የተገደሉ የመሰሉትን የኢህአፓን ሰዎች የብፁዕነት ማዕረግ ሊሰጣቸው እየተጋ ነው:: ገዳዩን ለማኮሰስ፣ ደርግን ለማሳነስ፣ ሟቹን ማጀገን ነበረበት? በፍፁም! ኢህአፓ በዘመኑ እንደነበር ነው እንደማንኛችንም የፖለቲካ ፓርቲዎች የራሱ ያልሆነ፤ የተኮረጀ፤ የተቀዳና የተዳቀለ አስተሳሰብ ይዞ እኔ ነኝ እረኛ ችሁ፤ ከኔ ወዲያ መሪ ላሳር በማለት . . . ራሱ ላይ የተኮሰ ትውልድ አባል ነው:: ይህንን ፓርቲ ነው ገዢው ፓርቲ የሚያጀግነው? መኢሶንን ለምን አይጠቅሱትም? እነሱን ይቀናቀን ስለነበር? ለምን? ሟቹም ነዋሪውም እኩል ተጠያቂ ነው:: ሁላችንም ኢትዮጵያን የተሻለች ለማድረግ ብለን ነው የተጨፋጨፍነው:: ኢህአፓዎች ስለገደሉዋቸው መኢሶኖችና ደርጎች አይነገረንም? ለምን አየህ! ለዚህ ነው ኢህአዴግ ከስልጣን ከመውረዱ በፊት ሕዝቡን ታሪክ ስላፋለስኩብህ ይቅርታ! ብሎ መጠየቅ አለበት የምልህ . . . »

*«ደርሶ መልስ» እንዳለጌታ ከበደ - 2002*

---

*ሙዚቃ ከጀመረ ስድስት ዓመት ሆኖታል:: ግርማ ሞገሴ ነሽ ፣ የእኔ ደህና ድሬ-ድሬ በሚሰኙ ሶስት ነጠላ ዜማዎቹ ይታወቃል:: በቅርቡ አዲስ አልበም ለማውጣት በዝግጅት ላይ ነው:: «የጥበብ የመጀመሪያ ግቢን አግብቻለሁ» የሚለው ሚኪያስ ቸርነት አንድ አፍታ ከሰናይት ግርማ ጋር ቆይታ አድርጓል::*

## «ሴትም እኮ ወንዳ ወንድ ሲሆን ነው እንጂ እ... የሚመስል ከሆነ ምኑን የተለየ ነገር አገኘች?»

**ሚኪያስ**



***በአሁን ሰዓት ምን እየሰራህ ነው?***

በቅርቡ የሚወጣውን ካሴቴን ሰርቼ ጨርሻለሁ:: አሁን የቀረኝ ወደ ሙዚቃ ቤቶች ጋር መሄድ እነሱም ወደ እኔ መምጣት ነው:: ካሴቴ ላይ አዳዲስ ነገሮች አሉት ብዬ አስባለሁ:: ከሌሎች ሙዚቀኞች ጋር የሚመሳሰል ድምጽ የለኝም:: በራሴ ስታይል፣ ድምጽና ዜማ ራሴን ሆኜ ነው የመጣሁት:: ከዚህ በተረፈ ካሴቱ ሳይለቀቅ አይዲያ አይነገርም::

***የጥበብ ባለሙያ ነህ:: የጥበብ ዋና ግቢ ምን ይመስልሃል?***

ሙዚቃን በትክክል መስራት ከጀመርኩ ስድስት ዓመት ሆኖኛል:: የናዝሬት ልጅ ነኝ:: ወደ አዲስ አበባ ስመጣ በትክክል መስራት ጀመርኩኝ:: ናዝሬት እያለሁ በፀረ-ኤድስ ክበብ ውስጥ ታቅፌ ነበር የምሰራው:: በዚያ ላይ የምንሰራው በአስራ አምስት ቀን አንዴ ነበር:: በዚያች ትንሽ ከበሮ ስንጮህ እንውል ነበር:: በዚያን ጊዜ ከዘፈን ባለፈ ስለ ኤድስ እናስተምር ነበር:: ሰዎች ያበረታቱኝም ነበር:: የጥበብ የመጀመሪያ ግቢን አግብቻለሁ:: ሰው እንዲያውቀው የማድረግ እና ሞያዬን ከሚወዱልኝ ሰዎች ጋር መድረስ የሚሉትን ነገር አሳክቻለሁ::

***ሁሉንም ነገር አሳክቻለሁ ብለህ ታስባለህ?***

ያወጣሁት ነጠላ ዜማ መደመጡ አንድ ስኬት ነው:: ትምህርት ተምረን ማብቂያ የለውም ወይም አይጨረስም እንደሚባለው ሁሉ በሙዚቃ የመጨረሻ ስኬት ላይ አይደረስም ወይም አያልቅም:: እግዚአብሔር ይመስገን አሁን ያለሁበት ጥሩ ነው::

***በህይወትህ ኪሳራ ውስጥ ገብተህ ታውቃለህ?***

አዎ አለ:: አንድ ሰው ሲዘፍን ትክክለኛ መነሻ ወይም ሜጀሩን ሊያጣ ይችላል:: የሙዚቃ ፍቅሩ ስላለሽ ብቻ መዝፈን ትጀምሪያለሽ:: የእኔ አጀማመር በትምህርት የታገዘ አይደለም:: ሊይድል ሾው በጣም የምወደው ፕሮግራም ነው:: ቢያንስ ለአሁኑ ትውልድ የሙዚቃ ክህሎቱን እንዲያሳድግ ተፈትኖ ማለፊያ ፕሮግራም አለ:: አንደኛና ሁለተኛ ዙር ላይ ብትወድቂ እንኳን የሆነ ነገር እየተማርሽ ነው:: ለሚቀጥለውም የወደቅሽበትን ስህተትሽን እያወቅሽ ትመጫለሽ:: በኤድስ ክበብ ውስጥ በምሰራበት ወቅት መሳሪያው ጥሩ ስላልነበረ የዘፈንኩትን ዘፈን ሰምቶ «ለምን ስራህን አትቀይርም?» ብሎኝ የሚያውቅ ሰው አለ:: እንደዚያ መባሌ እንዳቆም ሳይሆን ጠንክሬ እንድሰራ አድርጎኛል:: ድምፄን ለማስተካከልም ጥረት አደረግኩኝ:: «ስራ ቀይር» ያለኝ ሰውዬ አሁን ሲያገኘኝ ስራ ቀየርክ አይደል? ይለኛል:: ተሻሽለሃል/ ተለውጠሀል ማለቱ ነው:: የዚያን ጊዜ ሞራሌ ተነክቶ ነበር:: ያን ተቋቁሜ ለዚህ ደርሻለሁ:: የገንዘብ ኪሳራ ግን ገጥሞኝ አያውቅም::

***ጥሩ ነገር ማድረግ ከባድ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ:: በዚህ ትስማማለህ?***

እንደ ጭንቅላትሽ ነው:: ጥሩ ነገር ማድረግ ወይም ለተቸገረ መስጠት ይህ ከባድ የሆነ ነገር አይመስለኝም:: ጥሩ ነገር ማድረግ ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከጊዜያዊ ልምድ አይደለም:: ስለዚህ ጥሩ ነገር ማድረግ አይከብድም:: እንደውም መጥፎ ነገር ማድረግ ይከብዳል:: ህይወት ትጨልማለች:: የወደ ፊቱን ለማሰብ እንኳን ግራ ይገባሻል:: ከሰው አትቆጠሪም፣ ትገለያለሽ:: ታዲያ የዚህ ጫና አይከብድም? ጥሩ ነገር ማድረግ ግን በየሄድሽበት ቦታ ሁሉ ጥሩ ትሆኛለሽ:: ጥሩ ነገር ማለት በቃ ጥሩ ነገር ነው::

***ድሬ ድሬ የሚለው ነጠላ ዜማህ ላይ የ«ድራጎን» (እባብ) ምስል ያለበት ንቅሳት (tattoo) ወይም ስቲከር አንገትህ ላይ ይታያል:: ትርጓሜው ምንድነው?***

እኔ ለህዝብ አዲስ ፊት ነኝ:: አዲስ ሙዚቀኛም ነኝ:: ህዝቡን ለመሳብ አዲስ ነገር መፍጠር ነበረብኝ:: ከአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ የሚገኙ አድናቂዎቼ እየደወሉ «አንገትህ ላይ ያለው ንቅሳት ነው ወይስ ስቲከር» ይሉኛል:: አንዳንዶች ንቅሳት ወይም ስቲከር ነው በማለት ይወራረዱ እንደነበርም ነግረውኛል:: አንዳንዶቹ ያምራል ሲሉኝ ሌሎቹ ደግሞ እንደሚያስጠላ ይነግሩኛል:: እኔ በዚያን ሰዓት የሰው ጭንቅላት ውስጥ እየተቀረጽኩኝ ነው:: ስቲከር ሲሆን ክሊፑን ከሰራሁ ከሦስት ቀን በኋላ ከአንገቴ ላይ ጠፍቷል::

***ለምን የድራጎንን ምስል መረጥክ?***

ምክንያት የለኝም:: ምናልባት የዲዛይነሩ ምርጫ ስለሆነ ይሆናል:: ዲዛይነሩ ይህ እንደሚሻለኝ ነገረኝ:: መስቀል ወይም ጨረቃ ብታደርግ ወደ አንድ ወገን ትወግናለህ የሚል ሀሳብ ነግሮኝ ነው:: ስለዚህ ይሄኛው ግን ጌጥ ነው:: በፊት ካራቴ እና ኳስ እጫወት ስለነበር ድራጎን የሚል ነገር በውስጤ ነበር::

## *አሁን ሙዚቃን ስንሰራ በኮምፒውተር ድምፃችንን እንዲቀይር ያደረጋል ይባላል እንጂ ጥሩ ድምፅ ለህዝቡ እንዲደርስ እያደረገም ነው::*

***ስለ መዋቢያ ካነሳን አንዳንድ ወንዶች ከሴቶች በላይ የሚኳኳሉ አሉ [ይህ አይሁን የሚል ነገር ባይኖርም]:: ይህን የሚቃወሙ ወንድ ወንድነቱ ብቻ ውበቱ ነው ይላሉ:: ከራስህ ተነስተህ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለህ?***

ወንድ ሲባል ራሱ «ወርቅ» ማለት ነው:: [ሣቅ] አዳላህ እንዳትይኝ:: ወርቅ አሁን ላሳምረው ትያለሽ? አምስት ግራም ወርቅ ዲዛይኑ ሲያምር ተብሎ ከተገዛ በኋላ በይበልጥ ላሳምረው ይባላል? ላስጨፍልቀው ቢባል እንኳን ወርቅ ቤት ወይም ሙያተኛ ጋር ተሒዶ ነው የሚሰራው:: ወንድ በራሱ የሆነ ውበት አለው:: ምናልባት በሴት ጥሩነት ወይም ማማር መሳብ ይመስለኛል ይበልጥ እንዲኳኳሉ የሚያደርጋቸው:: ሴትም እኮ ወንዳ ወንድ ሲሆን ነው እንጂ እሷን የሚመስል ከሆነ ምኑን የተለየ ነገር አገኘች?

***ታዋቂ ነኝ ብለህ ታስባለህ?***

እግዚአብሔር ይመስገን ጥሩ ነገር ላይ ነኝ ያለሁት:: ታውቂያለሁ ሳይሆን አውቀው ጥሩ ፍቅር የሚሰጡኝ አሉ:: ለሚወደኝ ህዝብ የሚመጥነውን ስራ አላቀረብኩለትም ብዬ አስባለሁ:: ብዙ ነገር ይቀረኛል:: አሁን እወድሃለው ያለኝ ህዝብ እኮ እኔን እያስጨነቀኝ ነው፤ ወደ ፊት ጥሩ ስራ እንዳቀርብለት::

***ፈልጎ መወለድ ቢቻል በየትኛው ክፍለ ዘመን መኖርን ትፈልጋለህ?***

በዚህ ዘመን መኖር እፈልጋለሁ:: የድሮውን ዘመን አላውቀውም:: ይህ ያለንበት ዘመን ቴክኖሎጂው ያደገበት፣ ሰው ከሰው በዱላና በፀብ ሳይሆን በመነጋገር የሚግባባበት ነው:: በድሮ ጊዜ እኮ የእነ እንትና ልጅ እከሌን ገደለ ሲባል ታናሽየው ተነስቶ ገዳዩን ይገላል:: አሁን ግን ነገሮች በመነጋገር ይፈታሉ:: አሁን ሙዚቃን ስንሰራ በኮምፒውተር ድምፃችንን እንዲቀይር ያደረጋል ይባላል እንጂ ጥሩ ድምፅ ለህዝቡ እንዲደርስ እያደረገም ነው:: በዚህ የተነሳ የማላውቀውን ዘመን ላወድስ አልችልም:: በዚህ ዘመን ያለን ወጣቶች ጥሩ ሰርተን የዚህ ዘመን ወጣቶች ማስባል አለብን::

***ብዙ ጊዜ የምትጠቀመው ቃል ምንድነው?***

እግዚአብሔር ይመስገን:: በሁሉም ንግግሬ ውስጥ እግዚአብሔር ይመስገን እላለሁ:: ሰውን ሰላም ስልም ጭምር::

***ከኢትዮጵያ ባህላዊ መጠጦች የቱ ይመችሃል?***

ኦያያ መሰለን መሰልክ እንዳትይኝ [ሳቅ] ዘመናዊ መጠጦችን እወዳለሁ ማለቴ ሳይሆን የባዕላት ቀን ጠላ እቀምሳለሁ:: ጠጅ ስለሚጣፍጥ ብዙም አልጠጣም::


***አረቄስ?***

የአበሻ አረቄ ተብሎ ልቀምስ እችላለሁ:: ግን ጠላ መቅመስ ይሻለኛል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ይህቺ አገር የማን ናት?



በደረጀ መላኩ

እውቁ የፖለቲካ ተጠባቢ እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች እንዲሁም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ መስራች የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 127 ነሐሴ 01/2002 እትም ላይ «የሕግ አምላክ ተሰደደ?» በሚል ርእስ ተነስተው ስለአንድ «ጥጋበኛ» ሰው ድርጊት አስነብበውናል:: ማስተዋል ለሚችል ሰው እንዲህ አይነት አዌ በጉልበቱ የሆኑ ሰዎች በመዲናችን እንደአሸን እየፈሉ ለመሆኑ መገንዘብ የሚሳነው አይመስለኝም::

ሀሳባቸውን በአደባባይ በመግለጽ የሚታወቁት ፕሮፌሰር መስፍን ያነሱት ሃሳብ የድፍን አዲስ አበባ ችግር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: የዚህች አጭር ጽሁፍ አቅራቢ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት፣ ከቤት ወደ ቤተ-መጽሀፍት ቤት ወይንም ከቤት ወደ ቤተ-መቅደስ (ቤተ-ክረሰቲያን) በአብዛኛው የሚመላለሰው በእግሩ በመሆኑ ብዙ አሳሳቢ ጉዳዮችን ያስተውላል:: በተለይ ሀብት አለን የሚሉ ሰዎች የሚፈጽሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በእኔ በኩል አሳሳቢ ደረጃ ደርሷል ባይ ነኝ::

ለዛሬው በአዲስ አበባ አውራ ጎዳናዎች ላይ ስንከራተት ያጋጠሙኝን ሁኔታዎች ላብራራ::

በሳምንት ቅዳሜና አሁድ የእኔ የእረፍት ቀናት በመሀናቸው ማለዳ ተነስቼ ረጅም የእግር መንገድ መጓዝ ልምድ ካረኩኝ ዓመታትን አስቆጠርኩ::

ነሀሴ 9 ቀን 2002 ዓ.ም ማለዳ ላይ በአዲስ አበባ ሱሉልታ መስመር እየተጓዝኩ ነበር:: ጉዞዬን ጨርሼ ስመለስ ከ30 በላይ ተሳቢ መኪናዎች የእግረኛውን መንገድ በመዝጋት ተኮልኩለው ቆመዋል:: እኔም በመሀል መኪና የሚሄድበትን መንገድ ትቼ ከቆሙት መኪናዎች ጀርባ ጥግ ጥጉን በማድረግ ጉዞዬን ቀጠልኩ:: ትንሽ እንደተራመድኩ አንድ ሮጦ ያልጠገበ ወጠምሻ፣ «ማነህ አንተ?» በማለት በንቀት መልክ ተጣራ:: ዞር ስል፣ «ና:: ምን ትዝናናለህ::» በማለት አምባረቀብኝ:: በእውነቱ ትህትና የሚባል አልፈጠረበትም:: «ጥግ ጥግ የምትሄደው ምናምን ልትፈታ ነው፣» በማለት ተወራጨ:: በዚህን ጊዜ በንዴት ደሜ ፈላ:: ኢትዮጵያዊነቴ ትምህርት እንድሰጠው አስገደደኝ:: ለማስረዳትም ሞከርኩ፤ «ስማ የእኔ ወንድም፤ ይህቺ አገር የማን ናት?» ብዬ ጠየኩት:: አሁንም በንቀት መልክ አየኝ:: «ይህ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው» ብዬ መለስኩለት:: ይህ ባለሀብት መብት እንጂ ቅንጣት ያህል ግዴታ የሌለው በመሆኑ እንደ ኳስ ወደ ሰማይ አጎነኝ:: መሬት ስደርስ በእግሩ ረጋገጠኝ:: በደመ-ነፍስ ተነስቼ በድንጋይ ጀርባውን መታሁት:: ተመልሶ ከጥቅም ውጪ ሊያደርገኝ ሲል ሶምሶማ የሚሮጡ ሰዎች ደርሰው አስጣሉኝ:: ከዚህ ጨካኝ አውሬ በትር ስላዳኑኝ ሳላመሰግናቸው አላልፍም::

ልብ በሉ! የከባድ መኪናው ባለቤት መሆኑን የአካባቢው ሰዎች የነገሩኝ ሰውና (ሮጦ ያልጠገበና በትእቢት የተወጠረው ወጣት) እኔ የቆየ ቂም ወይንም ትውውቅ የለንም:: እርሱ ባለ ገንዘብ ወይንም ከለላ ያለው ሰው ሲሆን እኔ ግን እውነተኛ ነፃ ማህበር የሌለኝ ምስኪን መምህር ነኝ:: እርግጥ ነው እኔ ሁለተኛውን ዲግሪዬን ለመጨበጥ የምዳክር ሰው ስሆን እርሱ ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት ያለው ሶታ ወጣት ነው:: ገንዘቡን እንዴት እንዳገኘው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው::

ሶስቱ ሰዎች ከገላገሉኝ በኋላ እምባዬን እየዘራሁ ወደ ቤቴ አመራሁ:: ትንሽ ከተራመድኩ በኋላ ግን ውስጤ በንዴት ስለጦፈ ቁጭ ብዬ አለቀስኩ:: ሆኖም ግን አላፊው አግዳሚው እንዳላየ ያልፋል እንጂ ምን ሆነህ ነው? ብሎ የጠየቀኝ ሰው አልነበረም:: ይሄ ደግሞ ሀዘኔን አከበደው:: በቅኝ አገዛዝ ውስጥም እንዳለሁ ተሰማኝ::

«ሸገር» በተባለው የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ላይ ዶክተር መስፍን አርአያ የተባሉ እውቅ የአእምሮ ህክምና ጠቢብ፣ «ጥንት እኛ ልጆች ሆነን በአካባቢያችን አንድ ፍትህ የተጓደለበት ሰው ስናገኝ ምክንያቱን ጠይቀነው እናጽናናው ነበር:: በዳይም ከተገኘ የፍትህ አደባባይ ሳንደረስ እንዲክስ እናደርግ ነበር::» ያሉት ትዝ አለኝና ያልታሰበ እምባ ፊቴን ሙሉ አራሰው:: ጎንበስ በማለትም እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ በማለት አምላኬን ተማፀንኩ::

ጎበዝ! እኛን ግን ምን ነካን? ትብብርና አንድነትን አሽቀንጥረን በመጣላችን ዛሬ የትናንሽ አምባገነኖች መጫወቻ ሆነናል:: ያሳዝናል:: ማሳዘን ብቻ አይደለም ህሊናን ያደማል:: ሆድንም ይበጠብጣል::

በነገራችን ላይ እኔን እንዲህ ያበሳጨኝ ነገር በጉልበተኛው መደቆሴ አልነበረም፤ የዚች አገር የሰብዓዊ መብት ሁኔታዎች አሳዛኝ ደረጃ ላይ የመድረሳቸው ጉዳይ እንጂ:: በመጨረሻም ስብሰለሰል ከቆየሁ በኋላ ሁለት ሶስት ሰዎችን የፖሊስ ጣቢያ የት እንደሚገኝ ብጠይቅ እኛ አናቅም በማለት ጥለውኝ እብስ አሉ:: በሁኔታው አዝኜ ትንሽ አለፍ እንዳልኩ ሁለት መለዮ የለበሱ የፖሊስ አባላትን በማየቴ ወደ እነርሱ አመራሁና የደረሰብኝን የመብት ረገጣ ለማስረዳት ሞከርኩ:: «እባክህ መብት መብት አትበል:: ደረሰብኝ ለምትለው ነገር ማስረጃ አለህ ወይ?» ብሎ አንደኛው ጠየቀኝ:: እኔም፣ «ጉልበተኛው ሲነርተኝ ያዩ ሰዎች እንደነበሩ፣ መንገደኞች በመሆናቸው አድራሻቸውን አላውቅም ሆኖም ግን ባለሀብቱና ጉልበተኛው ትንሽ ከፍ ብሎ መኪናው ውስጥ ይገኛል» ብዬ መልስ ብሰጥ፣ «ከፊታችን ዘወር በል» በማለት ጉዟቸውን ቀጠሉ:: እኔም «የሕግ አምላክ» እዚህ ቦታ እንደሌለ በማረጋገጤ ቀስ እያልኩ ወደ ቤቴ አዘገምኩ::

አሁን ደግሞ በሀብታቸው ብዛት ህሊናቸው መብት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያልተገነዘቡ ወይንም እነሱ ባለመብት ሌላው ባለግዴታ ብቻ እንደሆነ የተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ያደረሱትን የመብት ጥሰት ለመጠቆም እሞክራለሁ::

በነገራችን ላይ መንግስት የተባለው አካል እዚህ ላይ ተወቃሽ ሲሆን ይታያል:: ለምሳሌ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ፊት ለፊት በአንደኛ የእሳት አደጋ ብርጌድ እና በማእከላዊ የወንጀል ምርመራ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚሰሩት ግዙፍ ህንፃዎች እየተጠናቀቁ ባሉበት ሁኔታ እንኳን የእግረኛ መንገዶች በአጥር ስለታጠሩ ሰዎች ከመኪና ጋር እየተጋፉ መሄድ ግዴታ ሆኖባቸዋል:: ይሄ የሰብዓዊ መብት ገፈፋ አይሆን እንዴ? እስቲ ቆም ብለን እናስብ::

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ከሚኖሩበት አፓርትመንት ህንፃ ሻገር ብሎ ወደሲኒማ ኢትዮጵያ በሚወስደው ጠባብ መንገድ ላይ አንድ ግሩም ህንፃ ተገንብቶ ታያላችሁ፤ ወደቸርችል ጎዳና ቁልቁል ስትወርዱ ወይም አቀበቱን ስትወጡ ቀድሞ የፈርኒቸር መስሪያ ይመስለኛል ኋላ አነስተኛ የሆነ ሆቴል በነበረ ቦታ ላይ ቅልብጭ ብሎ የሚታይ ትልቅ ህንፃ አለ:: ስያሜውም ቸርችል ቪው የሚባል ሆቴል መሰለኝ:: በእውነቱ ለመናገር ደስ የሚል ህንፃ ነው:: ሆኖም ግን ከሆቴል ቤቱ ጀርባም ሆነ ፊት ለፊት አሳባቂ ነገሮችን ታያላቹ:: ህዝቡ ምን ያህል በድህነት ወለል ላይ እንደሚገኝ ለማለት ነው::

ለማንኛውም ከላይ የተጠቀሱት የሁለቱም ህንፃ አሰሪዎች (ባለሀብቶች) የእግረኛውን መንገድ ድንጋያቸውን ካስደረደሩ በኋላ እንኳን ሰብአዊ ፍጡራንን በመናቅ የእግረኛውን መንገድ ዘግተው ወደ ራሳቸው ግዛት ቀላቅለውታል:: ግዛት አዌ (kingdom) መሆኑ ይሆን? ሁኔታው ስለከነከነኝ በሆቴሉ በኩል በእግሬ ሰጓዝ አንድ ቀን በር ላይ የቆመውን ጠባቂ የእግረኛውን መንገድ ዘግታችኋል ብዬ ተናገርኩ:: እርሱም እየሳቀ ዝም አለኝ:: በሌላ ጊዜ ይሄው ሰው ተናግሮ ነው መሰል በመጠኑም ቢሆን የእግረኛው መንገድ ትንሽ ሰፋ ብሎ አየሁት:: በዚህም ደስ አለኝ::

ከአዲስ አበባ ወደ ወለጋ በር ብትጓዙ ተመሳሳይ ችግር ታስተውላላችሁ:: ለመሆኑ ይሄንን ጉዳይ እየተከታተለ እርምጃ የሚወስደው ክፍል የተኛው ይሆን? ያስተዛዝባል:: በፍትሐ-ብሔር ሕግ፣ ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚባል ፅንሰ ሀሳብ አለ:: ስንቶቹ ባለሀብቶች ይሆኑ ይሄን ጽንሰ ሀሳብ በደንብ የተረዱት? ቤት ይቁጠረው::


በመጨረሻም ወደአስገራሚው የህንፃ ግንባታ ቦታ ቁፋሮ እና መዘዙ ትንሽ ልበልና ልሰናበት::

ይህ ለህንፃ ግንባታ በሚል የተከለለ ቦታ ቀድሞ አዲስ ባንክ ይባል ነበር:: ከዛ በፊት ግን የእነኪንግ ጆርጅ ባር፣ ሲኒማ አድዋ እና የመሳሰሉ ህንፃዎች የሚገኙበት ስፍራ ነበር:: በፒያሳና አካባቢው የሚኖሩ ወጣቶች መደሰቻም ስፍራ ነበር:: ለማ ክብረት የቀድሞው የባህር ትራንዚት ስፖርት ክለብ እና የብሔራዊ ቡድናችን ግብ ጠባቂ ለመሆን የበቃ፣ ረዘነ፣ እንዲሁም ዲናሬ (ግርማ) የኦጋዴን አንበሳ ሙዚቀኛና ኳስ ተጨዋች የነበሩ እና ሌሎችንም ማፍራት የቻለ ታሪክ

**መንግስት የተባለው አካል እዚህ ላይ ተወቃሽ ሲሆን ይታያል:: ለምሳሌ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ፊት ለፊት በአንደኛ የእሳት አደጋ ብርጌድ እና በማእከላዊ የወንጀል ምርመራ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚሰሩት ግዙፍ ህንፃዎች እየተጠናቀቁ ባሉበት ሁኔታ እንኳን የእግረኛ መንገዶች በአጥር ስለታጠሩ ሰዎች ከመኪና ጋር እየተጋፉ መሄድ ግዴታ ሆኖባቸዋል:: ይሄ የሰብዓዊ መብት ገፈፋ አይሆን እንዴ?**

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

# የመጭው አምስት ዓመት የመንግስት የእድገት ተግዳሮቶች



በየሁለም ሀሳብ

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድረጅት በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በኩል የመንግስትን የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ይፋ አድርጓል:: እናም ይህንን ተከትሎ የሚደረጉ ውይይቶችን መነሻ በማድረግ ነው የሚከተለውን ዳሰሳ ለማቅረብ የወደድኩት::

ይህ እቅድ፣ በሕጋዊ አግባብ በሕዝብ ተመርጬ ሥልጣን ይዣለሁ የሚል መንግስት ሊያደርገው የሚገባ ዋና ተግባር በመሆኑ ሊያከናውናቸው ከሚገቡ ነገሮች ተቀዳሚውን እርምጃ እያደረገ ስለሆነ ይበል የሚያሰኘው ነው::

የተለያዩ አመለካከቶችንና እምነቶችን የሚያራምዱ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ፉክክር ሲያደርጉ፣ ለሥልጣን የሚበቁ ከሆነ ለመረጣቸው ሕዝብ ሊያደርጓቸውና ሊወስዷቸው የሚችሏቸውን እርምጃዎች በቅድሚያ ማሳወቅ እና ቁርጥ ያለ እቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል:: እናም አንደኛቸው (ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች) ሥልጣን ለመያዝ ከበቁ፣ እነዚያ በፉክክር ወቅት እናደርገዋለን ያሏቸውን እቅዶች ከግብ ማድረስ እንዳለባቸው የሚያጠያይቅ አይደለም:: እናም፣ ሥልጣን የያዙ መሪዎች የእቅዳቸው መፈጸም አለመፈጸም ሊገመገም ከሚችሉባቸው ዘዴዎች መካከል ያ አንዱ ነው:: የተስፋ ቃል ሰጥቶ በቃሉ መሰረት ያከናወነ የፖለቲካ ድርጅት (መንግስት) በቀጣይ ለመመረጥ የተሻለ ብቻም ሳይሆን ተመራጭ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ቃሉንም ያላከበረ በተፃራሪው አይንህን ለአፈር መባሉ የማይቀር ነው::

በግንቦት 15/2002 በተካሄደው ምርጫ አብላጫውን ድምጽ በማግኘት ማሸነፉ በምርጫ ቦርድ የተነገረን ኢሕአዴግ፣ አገራችን እና ሕዝቦቿ ልንደርስበት የምንችለውን የጉዞ እርቀት በሚዳሰስ መለኪያ (Objective Standard) አስቀምጧል:: ስለዚህም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚገነባበት፣ ለዜጎቿና ለሌሎች ሕዝቦች መኖሪያነት ተመራጭ እንደምትሆን፣ በተለይ ከስንዴ ልመና ሙሉ በሙሉ ነፃ እንደምትሆን፣ የግብርናው የኢኮኖሚ ዘርፍ የመሪነቱን ስፍራ ለኢንዱስትሪ እንደሚለቅ፣ 2000 ኪሜ ያህል የባቡር ሀዲድ የሚገነባ አልያም መሰረቱ እንደሚጣልና ሌሎችም ተዘርዝረዋል::

እንደ እኔ አመለካከት፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እነኝህና መሰል በጎ ነገሮች በአገሩ እውን ሆነው ማየት የሚጠላ አይመስለኝም:: የትኛውንም አይነት የፖለቲካ አቋም የሚያንጸባርቅ ኢትዮጵያዊ፣ በስደት የሚኖር የየትኛውም እምነት ተከታይ፣ ማንኛውንም አይነት የፍልስፍና መርህ አራምዳለሁ የሚል፣ የአገርን በጐ ነገር ሊጠላ የሚችልበት ሞራል የሚኖረው አይመስለኝም:: በመሆኑም፣ እነኝህ በመንግስት ይፈፀማሉ ተብለው የተነገሩ ነገሮች እውን መሆናቸውን የሚጠላ ኢትዮጵያዊ የሌለ መሆኑን ማመኑ የተሻለ ይሆናል::

ቀጣዩ ጉዳይ ግን እውነት መንግስት እንደተናገረው በቀጣዩቹ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ እዚህ ደረጃ ልትደርስ ትችላለች? እነዚህ ነገሮች እውን ሊሆኑ ስለመቻላቸው ያለን ተስፋዎች በቂ ናቸውን? አለዚያም ደግሞ ይህ የአምስት ዓመት የእድገትና የለውጥ እቅድ ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደርጉ የሚችሉ ማነቆዎች ወይንም ችግሮች ይኖሩ ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችን በግልጽ አንስቶ መነጋገርና ለተግዳሮቶቹ ከወዲሁ መላ አበጅቶ መጠበቅ የተሻለ ይሆናል:: እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት ተነጋግሮ እና ተራርሞ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቢያንስ ቢያንስ የሞራል ግዴታ ያለበት ይመስለኛል:: በመሆኑም የድርሻዬን ለመወርወር ያህል እነሆ ይህንን ሀሳቤን አቅርቤአለሁ::

ሁላችንም ልንነጋገርበትና መንግስትም ቢሆን አትኩሮት ሊሰጣቸው ያሻል የምላቸውን የዚህን የአምስት ዓመት እቅድ ተግዳሮቶች /መሰናክሎች/ ለመዘርዘር ልሞክር::

## የሚዲያው ሚና

አሁን ባለንበት ዘመን ለአንድ የመንግስት ሥርዓት ሕልዎት ሚዲያ ወሳኝ ነ ሚና ይጫወታል:: ሚዲያ ገለልተኛና ጠንከራ ሆኖ ከሰራ መንግስት ግዴታዎቹን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ እንደግብአት የሚያገለግል ሲሆን ሚዲያው ወገናዊና ልፍስፍስ ከሆነ ደግሞ መንግስታት በህዝብ ላይ በአደባባይ እንዲሳለቅ መንገድ ጠራጊ በመሆን ያገለግላል:: ለዚህም ነው በዳበረው የመንግስት የሥልጣን ቁጥጥር አስተሳሰብ መሰረት ሚዲያው እንደ አራተኛ የመንግስት የሥልጣን መቆጣጠሪያ ተቋም ተደርጐ የሚታየው:: በመሆኑም ጠንካራና ገለልተኛ ሚዲያ ያለው አገር የዳበረ ዴሞክራሲን መገንባት ሲችል የወገናዊውና የልፍስፍሱ ሚዲያ ባለቤት የሆነ አገር ደግሞ ከሰብአዊ መብቱ ጥሰትና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ሁሌም ቢሆን ስሙ አንደተቆራኘ ይሆናል:: የሆነ ሆኖ የአገራችን ሚዲያስ ከየትኛው ወገን ነው? ለመሆኑ መንግስትን ይቆጣጠራል ወይስ ይከላከላል?

ከኢትዮጵያ ሚዲያዎች በአንደኛው ተቀጥሮ ከሚሰራ ወዳጄ ጋር ሻይ ቡና እያልን ስንጨዋወት በመሀል የስራ ጉዳይ ተነሳና ስራ እንዴት ነው? አልኩት:: ወዳጄም ስራ ሸጋ እንደሆነና «ልማታዊ ጋዜጠኛ» እንደሆነም ነገረኝ:: ታዲያ እኔም ልማታዊ ጋዜጠኛ ማለት ምን እንደሆነ አበክሬ ጠየቅኩት:: «ልማታዊ ጋዜጠኛ ማለት መርዶ የሚይናገር፣ ደግ ደጉን ብቻ እየመረጠ የሚዘግብ» እንደሆነ ነገረኝ::

ታዲያ ልማታዊ ጋዜጠኛና ልማታዊ ሚዲያ ተይዞ ወዴት ይደረሳል? ስል አሰላሰልኩ:: እንበልና አንድ አመራር ጥፋት ቢያጠፋ ጥፋቱ ይፋ የማይሆን /የልማታዊ ጋዜጠኛ ተግባር አይደለምና/፣ መንግስት እያከናወነ ያለው ተግባር የሆነ ቦታ ላይ ችግር ቢፈጥር እርምት ይወሰድበት ዘንድ ሚዲያው የቁጥጥር ስራውን ካልሰራ፣ ዜጎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲደርስባቸው ጥሰቱን የፈፀሙት አካላት ሀይ ይባሉ ዘንድ ሚዲያው ግዴታውን ካልተወጣ ምኑን አራተኛው የመንግስት የስልጣን ቁጥጥር አካል ሆነው? እንደልማታዊ ሚዲያ እና ልማታዊ ጋዜጠኛ አስተሳሰብ ለህዝብ ጆሮ መድረስ ያለበት መረጃ ህዝቡን ለልማት የሚያነቃና በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የፖሊሲና የፕሮግራም ጉድለቶች እየነቀሰ መንግስትን የማይገዳደር ማለት ነው::

በመሆኑም፣ ሚዲያው የሁሉንም ወገኖች ሀሳብ በማንጸባረቅ ከተከላካይነት ይልቅ የተቆጣጣሪነት ሚናውን መወጣት ከቻለ፣ «ልማታዊ ጋዜጠኞች» በሚል በየሚዲያዎቹ የሚሰሩ ባለሞያዎች ሞያው የሚፈልገው ነፃነት ተከብሮላቸው የመንግስት የገደል ማሚቶ ብቻ ሳይሆኑ በገለልተኝነት ህዝቡን ካገለገሉ፣ በተጨማሪም በብዙሀኑ ህዝብ መድረስ የሚችሉ የግል ሚዲያዎች (በተለይም ኤሌክትሮኒክስ) እንዲቋቋም ድጋፍ ካደረጉ ብቻ ነው መንግስት ያቀደው እቅድ እውን ሊሆን የሚችለው::

**ሚዲያው የሁሉንም ወገኖች ሀሳብ በማንጸባረቅ ከተከላካይነት ይልቅ የተቆጣጣሪነት ሚናውን መወጣት ከቻለ፣ «ልማታዊ ጋዜጠኞች» በሚል በየሚዲያዎቹ የሚሰሩ ባለሞያዎች ሞያው የሚፈልገው ነፃነት ተከብሮላቸው የመንግስት የገደል ማሚቶ ብቻ ሳይሆኑ በገለልተኝነት ህዝቡን ካገለገሉ፣ በተጨማሪም በብዙሀኑ ህዝብ መድረስ የሚችሉ የግል ሚዲያዎች (በተለይም ኤሌክትሮኒክስ) እንዲቋቋም ድጋፍ ካደረጉ ብቻ ነው መንግስት ያቀደው እቅድ እውን ሲሆን የሚችለው::**

## ጠንካራና ወገናዊ ያልሆነ የሲቪል ሰርቪስ ተቋም

የዳበረ የዴሞክራሲ ባህል ባላቸው አገራት የሲቪል ሰርቪስ ተቋም፣ ዜጐች በውድድርና በችሎታ የሚገቡበትና የማንኛውንም አይነት የፖለቲካ ወገን ወይንም ቡድን ፍላጐትና ሀሳብ የማያንፀባርቅ ተቋም ነው:: ይህ ተቋም ልክ እንደሚዲያው ሁሉንም ወገን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የመንግስት ተቆጣጣሪ አካል ተደርጐ ይወሰዳል:: ይህ ተቋም በይልጥ በተጠናከረባቸው አገራት፣ ተቋሙና በተቋሙ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች በውድድርና በችሎታ የገቡ በመሆናቸው የመንግስታት መቀያየር አያሳስባቸውም:: በመሆኑም ሰልጣን ላይ ያለው መንግስት ግዴታውን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የቁጥጥር ሚናቸውን በአግባቡ ይወጣሉ:: ለየትኛውም የፖለቲካ ቡድን የማያደሉና ወገናዊ አለመሆናቸውንም በተግባር ያረጋግጣሉ::

በመሆኑም የአገራችን የሲቪል ሰርቪስ ተቋም ሰራተኞቹ በውድድር እና በብቃት የሚቀጠሩበት፣ ተቋሙም የሁሉንም ወገኖች በተለይም በተቃውሞው የፖለቲካ ጎራ ተሰልፈው የሚገኙትን ወገኖች ጭምር በገለልተኝነት ለማስተናገድ በሚያስችል መልኩ የተዋቀረ ነውን? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ወደአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ሄዶ ሰራተኞቹን ማናገር በቂ ይመስለኛል::

በአንድ መስሪያ ቤት ከተሰበሰቡ ሰራተኞቹ መካከል ጠጠር ብንወረውር ጠጠሯ «የድርጅት» አባል ካልሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ይልቅ አባል ከሆኑ ሰራተኞች ላይ የማረፍ እድሏ ያለማጋነን 80 በመቶ መሆኑ አያጠራጥርም:: ታዲያ ይሄ ሁሉ ሰራተኛ አምኖበትና ብሎም አገሩን ከድህነት ለማላቀቅ ይህንን የፖለቲካ ድርጅት ተቀላቅሎ ይሆን? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም:: በመሆኑም፣ ይህ የመንግስት ሰራተኛ አምኖበት ከሆነ ድርጅቱን የተቀላቀለው፣ ድርጅቱ ለያዘው እቅድ መከወን አይነተኛ ግብአት ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ሳያምንበትና ሆዱን ለመሙላት ፎርም የሞላ ከሆነ ግን የሲቪል ሰርቪስ ተቋሙን ከማንቀዝ አልፎ መንግስትንና ራሱን ደርጅቱን አዙሮ በጭንቅላቱ የማይደፋው ስለመሆኑ ማንም እርግጠኛ አይደለም:: ታዲያ ምን ይደረግ?

ማንኛውም የኢትዮጵዊ የመደራጀትና የሚመስለውን የፖለቲካ አስተሳሰብ የማራመድ መብት እንዳለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ይደነግጋል:: በሲቪል ሰርቪስ ተቋም ውስጥ ተቀጥረው

ወደ ገፅ 23 ዞሯል



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ዘላቂ ትዳር ጠቋሚ ሆርሞኖች

*በአብዱ መሐመድ*

የሥነ-ልቦና ተመራማሪዎች፣ ፈላስፋዎች፣ የማህበራዊ ጥናት ባለሙያዎችና ደራሲዎች ለእውነተኛ ፍቅርና ለዘላቂ ትዳር መሰረት የሆኑ ነባሪዊ መላምቶችን በንባብና በፊልም አጠናክረው ለዕይታ ማቅረብ ከጀመሩ በርካታ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ፍቅርና የሰው ልጅ ታሪክ የማይነጣጠሉ ለመሆናቸው «ዓለምን የሚያንቀሳቅሳት ፍቅርና ረሃብ ነው» በሚለው ጥቅስ ቋጭተን ካላለፍነው፣ የተራራ ቁልል ከሚሚሩ መረጃዎች ውስጥ ገብቶ ከመዳከር ባለፈ በቀላሉ ልንወጣው የማንችል አብይ ጉዳይ ነው፡፡

ምሁራን ለዘመናት በደከሙበት፣ ብዙዎች ህይወታቸውን ባጡበት፣ አያሌ ሙዚቀኞች ላቀነቀኑለትና ለተወኑለት ለእውነተኛ ፍቅርና ትዳር መሰረቶች ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ መፈቃቀድ፣ መተሳሰብ፣ ስኬት፣ ሃይማኖት፣ የወሲብ መጣጣም፣ እምነት፣ እወቀት እና ክህሎት በመጀመሪያዎቹ ረድፍ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከምሁራን መላ ምት በተጨማሪ እያንዳንዱ ግለሰብ ለዘላቂ ትዳር መሰረቱ ምን እንደሆነ የሚገልፀውን የራሱን መዝገብ ቃላት እየገለጠ የራሱን ትርጓሜ ያስቀምጣል፡፡ የሰዎች ጓዳም እየገባ የባለትዳሮችንና የፍቅረኛሞችን ጓዳ ሲያምስና ሲፈትሽ መዋል ከዕለት ተግባሩ አንዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

*ታይም* «The Science of Romance» በሚል ርዕስ ባቀረበው የልዩ ጥንቅር ጽሑፉ መተሳሰብ፣ መፈቃቀድ፣ የተክለ ሰውነት ምርጫ ወዘተ ለዘላቂ ትዳር መሰረት ናቸው የምንል ካለን ስንጃጃል እንደቆየን ነግሮናል፡፡ ቀደም ሲል ለዘላቂ ትዳር መሰረትነት የቀረቡ መስፈርቶች፣ ትዳርን ሰብስበው የሚይዙ ገበቴዎችና ማጣፈጫዎች፣ ፍቅርን በሁለት እግሩ የሚያቆሙ የትዳር ትሩፋቶች እንዳልሆኑና እንደውም ወደስህተት የሚመሩ እንደሆኑ ተደምጧል፡፡

ሰፋ ያለ ዳሌና ያጐጠጐጡ ጡቶችን ማራኪ ተክለ ሰውነት እያየ እርሷን የሚመኝ ጐረምሳ፣ ምርጫውን ለማግኘት ህይወቱን ሳይቀር ሊገብር ይችላል፡፡ ሰፋ ያለ ደረት ላይ ማረፍ፣ በዘለግላጋ ወንድ መታቀፍ የፈለገች ሴትም የፍላጐቷ እስኪደርስ አይኗን ከወዲያ ወዲህ እየወረወረች ስታማልል ዕድሜዋን ልትገፋ ትችላለች፡፡ ይሁንና ሁሉም የራሱን መስፈርት አስቀምጦ የፍላጎቱን ካገኘና ከቡፌው ተቋድሶ ትዳር ከመሰረተ በኋላ ፍቅር እንደጉም በኖ ይጠፋል፡፡

በምሁራኑ በቀረበው ሳይንሳዊ መረጃ፣ ትዳር የሚታመሰውና የሚፈርሰው ለተቃራኒ ጾታ ከልብ የመነጨ ፍላጎት የሚፈጥረው ከአንደኛው/ዋ አጋር የሚወጣው ጠረን ሳይንሳዊና ተፈጥሮአዊ መስፈርቱን ያላሟላ ወህደት ሲፈጥርና ወህደቱን የሚያዛባ ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ የሰው ልጅ፣ የሴቷን ብልት አሽትቶ ለስሪያ እንደሚሰማራ ውሻ፣ ለዘላቂ ትዳር መሰረት የሆነውን መረጃ የሚያገኘው ከንፈሩን ከወዳጁ ከንፈር ላይ ሲያሳርፍ፣ ከወዳጅ የሚወጣውን ጠረን በአፍንጫ ምጎ ወደ አእምሮው በመላክ በሚያኘው ምላሽ ነው፡፡

የጥናት ውጤቱን ካቀረቡ ምሁሯን ውስጥ አንዷና በአሜሪካ ቴክሳስ ዩኒቨርስቲ የሥነ-ተዋልዶ መምህር የሆኑት ማርቲ ሀኒስተን እንዳስፈሩት፣ ሁለት ጥንዶች መተሻሸትና መሳሳም ሲጀምሩ ከሰውነታቸው ድራይቪንግ ፌርሞን የተባለ ጠረን መመንጨት ይጀምራል፡፡ ለመፈላለግ ስሜት ምላሽ የሚሰጠውን ይህንን ሆርሞን የሚያመነጨው ሜጀር ሂስቶ ኮምፓቲቢሊቲ ኮምፕሌክስ የተባለው ጂን ወይም ቅንጣተ-ሴል ነው፡፡

በነዚያ ቅንጣቶች የተፈጠረ ጠረን የማጉ የተቃራኒ ጾታ አፍንጫዎች፣ ጠረኑን በአእምሮ የታችኛው ክፍል ለሚገኘው ዶፓማይን የተባለ ኬሚካል ለያዘው ማጣሪያ ያስተላልፋል፡፡ ዶፓማይን በራሱ ጆብር እንደደረሰው ቁማርተኛ፣ ወይም የሚያስጐመጅ ምግብ እንደቀረበለት ሰው የአዎንታ ወይም የአሉታ ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት የሚወጣ ቢሆንም የደረሰው ጠረን የመጀመሪያ ከንፈራቸውን ካሳረፉ ወዳጆች ከሆነ የራሱን ውሳኔ በማስፈር ወሳኝ ወደሆነው ወደ አእምሮ ማዕከላዊ ክፍል ያስተላልፋል፡፡ ኑክለስ አከምበስ የደረሰው የጠረን መረጃ ሴሮቶኒን እና ኦክሲቶሲን የተባሉ ሆርሞኖች የመጨረሻ ማጣሪያ ካለፈ በኋላ፣ የመፈላለግ ኳድሮ ይበራል ወይም የስሜት አለመጣጣም የሚፈጥርና ለወሲብና አለመፈቃቀድ የሚዳርግ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ይህንኑ በተመለከተ በፊላደልፊያ ሞኔል ኬሚካል ኢንሰቲቲዩት ፕሮፌሰር የሆኑት ቻርልስ ዊሶስኪ «Evolution and Behaviour» የሚል ርዕስ ያለው የጥናት ጽሑፍ በዝርዝር እንደሚያስረዳው፣ ከተቃራኒ የፍቅር ጓደኛ የሚወጣ ጠረን ጥሩ መአዛ ኖረው አልኖረው ምንም ልዩነት አያመጣም፡፡ ዋናው ጥንዶቹ በተፈጥሮ የሚያመነጩትና ጠረን የሚያመነጨው ሲፈጠሩ ይዘውት የተወለዱት ሆርሞን ነው፡፡ ሁለት ጥንዶች ወደስሜት የሚያመራ ውህደት ሊፈጥሩ የሚችሉት በተፈጥሮአቸው የተለያየ ሆርሞን የሚያመነጩ ከሆነና አእምሮአቸው ይህንን ጠረን ተቀብሎ ኦክሲቶሲን የተባለውን አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጥ ውህደት ከፈጠረ ነው፡፡

የሕክምና ባለሙያዎች ለዘላቂ ትዳርና ፍቅር የጠረን ውህደት ትልቁን ሚና እንደሚጫወት ቀደም ያለ መረጃ ያሰባሰቡ ቢሆንም፣ ይህን ጥምረት የሚፈጥረው ድራይቪንግ ፌርሞን በሴቶች ላይ የወር አበባ የጊዜ ዑደት ተከትሎ የሚለዋወጥ መሆኑን የደረሱበት በቅርብ ነው፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ሴቶች ከወንዶች የሚወጣውን ጠረን ተቀብለው ወደ ፍላጐት የሚያነጉድ ስሜት የሚፈጠርባቸው፣ ዘር ለመቋጠር የሚችል ደረጃ ላይ የደረሰ ዕንቁላል ባዘጋጁበት ወቅት ነው ብለዋል፡፡

በእንግሊዝ የሊቨርፑል የህክምና ባለሙያዋች ያቀረቡትን የጥናት መረጃ ባካተተው የታይም ዘገባ፣ ሴቶች የወሊድ እንክብል ሲውጡ ከሰውነታቸው የሚወጣው ጠረን እንደሚለዋወጥ ይገልፃል፡፡ ይህ የጠረን መለዋወጥ ሴቶቹ ተመሳሳይ ሆርሞን ከሚያመነጩ ወንዶች ብብት ስር በመውደቅ መጨረሻው የማያምር ጥምረት እንዲፈጥሩ የሚያደርግ ስህተት ላይ ይጥላቸዋል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ፣ የፀነሱት ፅንስ ሊጨናገፈ ይችላል፡፡ ይህ የሚያሳየው በጋብቻ ወቅት ለትዳር መፍረስ ትልቁን ሚና የሚጫወተው የወሊድ እንክብል መሆኑን ነው፡፡

ተመራማሪዎች ለዚህ መፍትሄ ብለው ያስቀመጡት፣ ወንዶች በተፈጥሮአቸው የሚያመነጩት ጠረን በምራቃቸው ውስጥ በከፍተኛ መጠን የሚገኝ በመሆኑ ሴቶች በስሜት የሚቆራኛቸውን ወንድ ለመምረጥ የሚያስችል መረጃ በቀላሉ ማግኘት የሚችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህን መረጃ ለማግኘት ከሱስ የፀዱ የወንድ ከንፈሮች ላይ ከንፈራቸውን በማሳረፍና የመጀመሪያውን የስሜት ቅምሻ ማድረግ ይኖረባቸዋል፡፡ ይህን ሲያደርጉ ደግሞ ከወሊድ ዕንክብል መራቅና ለፅንስ የደረሰ ዘር ያዘጋጁበት የወር አበባ ዑደት ላይ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡

የህክምና ባለሙያዎች ለዘላቂ ፍቅር መረጃ የሚገኘው በከንፈር ላይ ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሁለት ፍቅረኞች መካከል በፍላጐት የሚከናወውን የመሳሳም ሂደት 26 ካሎሪ ኃይል አለው፡፡ ይህን ኃይል ለማውጣት ፊታችን ላይ የምናንቀሳቅሳቸው 26 ጡንቻዎች የፊታችንን መሸብሸብ በመከላከል ከእርጅና እንደሚጠብቁንም መስክረዋል፡፡

ለዘላቂ ትዳር መረጃው ከንፈር ላይ ይገኛል ስለተባለ ያገኙትን ልቅመስ ማለት የማይሞከር መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም፡፡ *ዘ ጋርዲያን* ዓለም የከንፈር መሳሳምን እንዴት ይመለከተዋል በሚል ባጠናቀረው መረጃ ከዓለማችን ሕዝብ 10 በመቶ የሚሆነው ከንፈር ለከንፈር መሳሳምን ቦታ አይሰጠውም የሚል ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የባህል ተፅእኖ ነው እንዳይባል አንድ አይነት ዝርያና ባህል ባለው የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ የሚሳሳሙም የማይሳሳሙም ግለሰቦችን እናገኛለን፡፡ ወደ ምድር ዋልታ አካባቢ የአየሩ ፀባይ ቀዝቃዛ በመሆኑ ከንፈር ለመክፈት በማይቻልበት የአየር ፀባይ እየኖሩ ሲሳሳሙ እንመለከታለን፡፡

በሆሊውድ መሳሳም የጓዳ ምስጢር ነው፡፡ በመካከለኛው ምስራቅና ከሰሀራ በታች ባሉ አገራት ከንፈር ለከንፈር መሳሳም የወሲብ አንዱ ክፍል ተደርጎ አይቆጠርም፡፡ አንትሮፖሎጂስቶች፣ በጥንታዊ የፊንላንድ ዝርያዎች መሳሳም እንደ ባህል ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው፣ በቻይና ደግሞ እንደ ነውር እንደሚቆጠር የሚገልፅ መረጃ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

በሰለጠነው የዓለም ክፍል መሳሳም እንዲህ በቀላል የሚታለፈ የስሜት መገለጫ አይደለም፡፡ በፈረንሳይ ምላስን ወደ ተቃራኒ አፍ መክተት የወሲብ ጥያቄ ለመቀበል ፍቃደኛ መሆንን የሚያመለክት ነው፡፡ ጀርመኖች ለ30 የመሳሳም አይነቶች 30 የተለያዩ መልዕክቶችን የሚገልጽ ባህል አላቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ ናችካሴን ከንፈር በመነካካት የራቀ ወዳጅን ለማስታወስ የሚቀርብ ሰላምታ ነው፡፡

በሆሊውድ ፊልም በተደጋጋሚ የምንመለከተው ከንፈር ለከንፈር መሳሳም በማህበራዊ ኑሮ እንዲህ በቀላሉ የሚተገበር አይደለም፡፡ በአሜሪካ ከንፈርህን በተቃራኒ ጾታ ላይ ከማሳረፍህ በፊት ለያንዳንዷ እንቅስቃሴ የወዳጅን ፈቃድ ማግኘት ግድ ይላል፡፡ ጥያቄህ የይለፍ ፍቃድ ከተሰጠው ደረጃውን ጠብቀህ ከንፈሯ ላይ ከንፈርህን ማሳረፍ ትችላለህ፡፡

*አሜሪካ የገባህ ባዕድ ወይም የውጭ ዜጋ ከሆንክ፣ ጥያቄህ በወረቀት ሰፍሮ በእማኝ ፊት በፌርማ ቢፀደቅ የተሻለ ነው ያሰኛል፡፡ ከዚህ ባለፈ፣ አሜሪካኖች በመብቶቻቸው ቅንጣት ስለማይደራደሩና በጭናቸውና በቦርሳቸው ሽጉጥ ስለማይጠፋ፣ ስለመሳም ባሞጠሞጠው አፍህ እንደ ኢንዶስኮፒ ጥይት አጉርሰውህ እስከወዲያኛው ልታሸልብ ትችሳለህ፡፡*



አሜሪካ የገባህ ባዕድ ወይም የውጭ ዜጋ ከሆንክ፣ ጥያቄህ በወረቀት ሰፍሮ በእማኝ ፊት በፌርማ ቢፀደቅ የተሻለ ነው ያሰኛል፡፡ ከዚህ ባለፈ፣ አሜሪካኖች በመብቶቻቸው ቅንጣት ስለማይደራደሩና በጭናቸውና በቦርሳቸው ሽጉጥ ስለማይጠፋ፣ ለመሳም ባሞጠሞጠው አፍህ እንደ ኢንዶስኮፒ ጥይት አጉርሰውህ እስከወዲያኛው ልታሸልብ ትችላለህ፡፡

የምትመከረውም የዘላቂ ትዳር ጓደኛህን ለማግኘት ከንፈርህን ተቃራኒ ጾታ ከንፈር ላይ ከማሳረፍህ በፊት ፈቃደኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ያላሰብከው የከንፈር ግብዣ ሲቀርብልህም ፈጠን ብለህ፣ «ጉንፋን ስለያዘኝ ለሌላ ቀን ብናስተላልፈው ይሻላል» ብለህ በዘዴ ማለፍ ነው፡፡ መተከዣ እንዲሆን በ1840 «ኪሲንግ» በፖስታ መላላክ የጀመረውን ሮላንድ ሒልን እያስታወስክ የ«ኪሲንግ» መልዕክት በማስተላለፍ ጊዜህን መግፋት ነው፡፡




ፎቶ:- ሲሳይ ጉዛይ [091-1245811]



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



በታምራት ታረቀኝ

# ወ/ት ብርቱካንን ማነው የሻራቸው?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ቢወጣ 92 ፓርቲዎች አይኖሩም በሚል ርዕስ በሁለት ተከታታይ ሳምንት ያቀረብኩትን አስተያየት በክፍል ሶስት ለማጠናቀቅ መረጃ ሳሰባስብ ነበር ወደ ምርጫ ቦርድ ድረ- ገጽ ጎራ ያልኩት:: አንድ ሁለት ገጾችን ከቃኘሁ በኋላ ዋናው ጉዳዬ የሆነውን የ 92 ፓርቲዎች ዝርዝር ለማየት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚለውን ተጫንኩ:: ያገኘሁት ግን አንዳሰብኩት የ92 ፓርቲዎች ዝርዝር ሳያሆን የ79 ፓርቲዎችን ዝርዝር የያዘ ሰንጠረዥ ብቻ ነበር::

ቅደም ተከተሉ የተሰራበት መስፈርት ባይታወቅም በቁጥር አንድ ላይ የሚነበበው የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ ሊቀመንበሩ አቶ ቶሎሳ ተስፋዬ የሚለው ነው:: ዝቅ ስል በአንድ ሰው መሪነት የተመዘገቡ ሶስት ፓርቲዎችን አየሁ:: አንድ ሰው የሶስት ፓርቲ መሪ ከመሆኑ በላይ ያስገረመኝ ፓርቲዎቹ ሀገራዊና ክልላዊ መሆናቸው ነው:: አንድ ሰው በዓላማም በአደረጃጀትም የሚለያዩ ፓርቲዎች መሪ መሆን እንዴት ይቻለዋል? በዚህ እየተገረምኩ ሰንጠረዡን ቁልቁል ስወርድ የብዙዎች ፓርቲዎች ህጋዊ እውቅና ያገኙ ብት የሚለው ቦታ ባዶ ነው:: እንዴት ነው ነገሩ! ምርጫ ቦርድ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት እየተወጣ አይደለም ብዬ ስሞግት ይባስ ብሎ ለመዘገባቸው ፓርቲዎች ምስክር ወረቀት የሰጠበትን ቀን አንኳዋን የማያውቅ ሆኖ ተገኘ ማለት ነው?

እንዲህ እንዲህ እያልኩ 73ኛው ተራ ቁጥር ላይ ስደርስ የተመለከትኩት ግን በጣሙን የሚያስገርም የሚያጠያይቅም ነው:: ይህም በዝምታ ሊታለፍ የማይችል ከጀመርኩት ርዕሰ ጉዳይ ጋርም ቀጥተኛ ተዛምዶ ያለው በመሆኑ ለዛሬ ያልኩትን ማጠቃለያ መለወጥ ግድ ሆነብኝ:: እኔ ያየሁትን እናንተም እያያችሁ አንዋያይ ዘንድ ይሄው በቀጥታ ኮፒ አደርጌ አሰፈርኩት:: ሠንጠረዡን ሲያዩ ምን ተሰማዎት?

| ተራ ቁጥር | የፓርቲው ሙሉስም | አህጽሮተ ቃል | ህጋዊ እውቅና ያገኙበት ቀን | አገራዊ | ክልላዊ | የሊቀመንበሩ ሙሉ ስም | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 73 | አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ | አንድነት | 16/12/02 | • | | ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው | 0118-400811 |

በሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየው አንድነት ተመሰረተ የተባለበት ነሐሴ 16ቀን 2002 ዓም ዛሬ በመሆኑ ተራ ስህተት ነው ብለን ብናለፈው የቦርዱን አሰራር አንዴትነት ማሳበቁ ግን አይቀርም:: በአንድ ትልቅ ተቋም የመረጃ መረብ የሚሰራጭ መረጃ ከመነሻው በጥንቃቄ ሊሰራ ይገባዋል:: ከዛም እየተከታተሉ አዳዲስ መረጃዎች ይጫናሉ: የታዛባ ይስተካከላል የተሳሳተ ይታረማል::
አንዴ ጭኖ ዝም ማለት ግን ድረ ገጹን ባለቤት የሌለው ሥራውንም የግብር ይውጣ ሥራ ያስመስለዋል::

የአንድነት ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው የሚለው ግን በምንም መልኩ ስህተት ሊባል አይችልም:: ለድርጊቱ እንዴትነትም ከምርጫ ቦርድ ውጪ ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል አካል አይኖርም:: የድረ ገጹ ህጋው ባለቤት እርሱ ነውና:: ታዲያ በይፋ የምትታወቀው የአንድነት ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሆና ሳለ አንዴት ኢ/ር ግዛቸው ተብሎ ሊገለጽ አንደቻለ መጠየቅ ለብርቱካን ከመቆርቆር ሳይሆን ለህግ የበላይነት መረጋገጥ ከመቆም የሚመነጭ ነውና አግባብነት አለው::
ቦርዱ ኢ/ር ግዛቸው የአንድነት ሊቀመንበር መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከፓርቲው ደርሶኝ ነው ሊል ይችል ይሆናል:: ነገር ግን በፓርቲው ውስጥ ሥልጣን የሚያዝበትም ሆነ የሚሻርበት አግባብ በቦርዱ እጅ በሚገኘው መተዳደሪያ ደንብ የተገለጸ በመሆኑ መረጃ ደርሶት ከሆነ የኢ/ር ግዛቸው ሹመት የመተዳደሪያ ደንቡን ሕጋዊ መስመር ተከትሎ ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ አለበት:: ጥቂቶች ተስማምተው ተፈራርመው የሚያቀርቡለትን ተቀብሎ ይሁንታ የሚሰጥ ከሆነ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ በመሄድ «ለመፈንቅለ ሥልጣን» ተባባሪ መሆን ነው::

## መፈንቅለ ሥልጣንን የሚፈቅድ ሕግ የለም

በሀገር ደረጃ ስልጣን የሚያዘው ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መንገድ ሲሆን በፓርቲ ደረጃ ሥልጣን የሚያዘው ደግሞ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚደነግገው መሰረት ስለመሆኑ ለማንም ሰው አዲስ ነገር አይሆንም::
የአንድነት መተዳደሪያ ደንብም ሰዎች ለኃላፊነት ቦታ እንዴት በማንና መቼ አንደሚመረጡና አንደሚሻሩ በግልፅ አስፍሯል:: የደንቡ አንቀጽ 10.2.2 « አምስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮማቴ በመሰየም የብሔራዊ ምክር ቤትንና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላትን ይመርጣል » በማለት ኃላፊነት የሰጠው ለጠቅላላ ጉባዔው ነው:: ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም ከ110 ዕጩዎች ጋር ተወዳድራ ለምክር ቤት አባልነት የተመረጠችው ሰኔ 11/2000 ዓም በተካሄደው መስራች ጉባዔ ነው::
በሊቀመንበርነት የተመረጠችው ደግሞ በአንቀጽ 11.1 « የፓርቲውን ሊቀመንበር ም/ሊቀመና ብርት: ዋና ጸኃፊና ሌሎች የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል» ተብሎ ሥልጣን የተሰጠው ምክር ቤት ወዲያውኑ ተሰብስቦ «በፓርቲው ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ላይ የአመራር አካላት ምርጫ አንድ አባል አንድ ድምጽ በሚለው መርህ መሰረት ምርጫው በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ያከናወናል» ተብሎ በተገለጸው አንቀጽ 26 መሰረት ለሊቀመንበርነት ዕጩ ሆነው ለቀረቡት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለኢ/ር ግዛቸውና ለአቶ ተመስገን ዘውዴ አንደ ቅደም ተከተላቸው 33 18 እና 3 ድምጽ በመስጠት ነው::

ይህም ብቻ አይደለም ወ/ት ብርቱካን በታሰረች በአራተኛው ቀን ታኅሣሥ 25/ 2001 ዓም የተሰበሰበው ብ.ም.ቤት « ወ/ት ብርቱካን ትናት ዛሬም ሆነ ወደፊት የአንድነት ሊቀነብር ነች» በማለት በአጽንኦት ገልጸዋል:: ሚያዚያ 10/2002 ዓም የተካሄደው ልዩ ጉባዔም የወ/ት ብርቱ ካንን ሊቀመንበርነት ያረጋገጠው በሙሉ ድምጽ ነው:: ታዲያ ኢ/ር ግዛቸው ሊቀመንበር ተብለው በምርጫ ቦርድ ድረ ገጽ የሰፈሩት እነዚህን ሕጋዊ ውሳኔዎች መቼ በምንና አንዴት አሽረው ነው? ምርጫ ቦርድስ ምን ሕጋዊ ማረጋገጫ ይዞ ነው ሊቀመንበር ሊላቸው የበቃው? ::
አቶ አስራት ጣሴ በአውራ አምባ ታይምስ ጋዜጣ የመጋቢት 26/2002 ዕትም « ም/ቤቱ መሰብሰብ ስላልቻለ በኮሪደርና በቤት ውይይት እያደረገ ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስየ ምክትል ሊቀመናብርት አድርጎ መረጠ» በማለት የገለጹትን ሕገ ወጥ ሹመት በተቀበለበት መንገድ: ኢ/ር ግዛቸው ከሪፖርተር ጋዜጣ የሚያዝያ 24/2002 ዕትም ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፕሮግራሙን ያብራራው ማነው» ለሚለው የጋዜጠኛው ጥያቄ « እኔና አቶ አስራት» በማለት በገለጹት ሁኔታ ለተለወጠው ፕሮግራም እውቅና በሰጠበት አሰራሩ የኢ/ር ግዛቸውንም ሹመት (በርግጥ ተሾመው ወይንም ራሳቸውን ሾመው ይህንኑ ለቦርዱ ሪፖርት አድርገው ከሆነ) ተቀብሎ ከሆነ ቦርዱ ሕግ የጣለበትን ኃላፊነት ያለመወጣት ብቻ ሳይሆን ሕገ ወጥ ተግባርም እየፈጸመ መሆኑን ነው የሚያሳየው:: በመሆኑም ቦርዱ ኢ/ር ግዛቸውን የአንድነት ሊቀመንበር ብሎ በድረ- ገጹ ላይ ያሰፈረው ከአንድነት ሰዎች መረጃ ይዞም ይሁን በራሱ ፍላጎት ተነሳስቶ ደረጃው ይለያይ አንደሆነ አንጂ ከተጠያቂነት አያነፃውም::
የፓርቲውን ፕሮግራም መለወጣቸውም ሆነ እንደ አንድ ሰው ሳይሆን አንደ ፓርቲ የሚታዩ ናቸው ብለው ዶ/ር ነጋሶንና አቶ ስዬን ም/ል ሊቀመንበር አድርገው መሾማቸው ሌላው ሌላው ዓላማን ፍላጎት አንዳለ ሆኖ ከአንድነት ጋር የተያያዘውን የብርቱካን ስም ለማደብዘዝ «በትላልቆቹ ሰዎች» ጎልቶ መታየት ብርቱካን አንድትረሳ ለማድረግ አንደነበረ ጉዳዩን በቅርብ ለሚከታተል ሁሉ ግልጽ ነው:: ይህን ሁሉ ያደረጉ ሰዎች በለመዱት መንገድ በኮሪደር ዶልተው ብርቱካንን ለመሻር አይደፍሩም ለማለት ይቸግራል::

> ቦርዱ ኢ/ር ግዛቸው የአንድነት ሊቀመንበር መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከፓርቲው ደርሶኝ ነው ሲል ይችል ይሆናል:: ነገር ግን በፓርቲው ውስጥ ሥልጣን የሚያዝበትም ሆነ የሚሻርበት አግባብ በቦርዱ እጅ በሚገኘው መተዳደሪያ ደንብ የተገለጸ በመሆኑ መረጃ ደርሶት ከሆነ የኢ/ር ግዛቸው ሹመት የመተዳደሪያ ደንቡን ሕጋዊ መስመር ተከትሎ ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ አለበት

አላደረጉት ከሆነ ደግሞ ቦርዱ ያሰራጨውን መረጃ እያዩ ዝም ማለት አልነበረባቸውም:: አሁንም ቢሆን የሚፈልጉትን ግን በአደባባይ ሊናገሩት ያልደፈሩትን ቦርዱ ስላደረገላቸው ተደስተው ካልሆነ ጉዳዩን ግልጽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: የአንድነት ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን መሆኗን አረጋግጠው ለሕዝብ መግለጽም ይኖርባቸዋል:: «መፈንቅለ ሥልጣኑን » አድርገውት ከሆነም ለምን? አንዴት? መቼና በማን አንደፈጸሙት ማሳወቅ አለባቸው:: ጓዳ ለጓዳ በሽፍንፍን በሚሰራ ፖለቲካ እውነትን መዳፈን ለአሸናፊነትም መብቃት አንደማይቻል ያለፈው ቢረሳ የትናንቱ የምርጫ 2002 የመከራ ምክር የሚረሳ አይመስለኝም:: ነጻ የሚያወጣው ለዘላቂ ድልም የሚያበቃው እውነት ብቻ ነው::

## የምርጫ ቦርድ ድርጊት ሕገ-ወጥ የሚሆነው

ምርጫ ቦርድ ኢ/ር ግዛቸውን የአንድነት ሊቀመንበር በማለት በድረ-ገጹ ያሰራጨው በራሱ ይሁንታም ይሁን ከፓርቲው ሰዎች መረጃ ይዞ ድርጊቱ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም የምንለው ለምርጫ ቦርድ ኃላፊነትና ሥልጣን የሰጡትን አዋጆች መሰረት በማድረግ ነው::
የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ 573/2000 የፖለቲ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ስላለው ነጻነት በሚገልጸው አንቀጽ 16 በንኡስ አንቀጽ 1 «ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራሙንና የመተዳደሪያ ደንቡን የሚያጸድቅበትንና የሚያሻሽልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚያካሂድበትን ሥነ- ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል» ሲል ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወስነው መሰረት የፖለቲካ ሥራውን የሚመሩ: ውሳኔ የሚሰጡና የሚያስፈጽሙ የአመራር አካላት ይኖሩታል» ይላል:: ከእነዚህ ሁለት የአዋጅ 573/2000 አንቀጾች በግልጽ መረዳት የሚቻለው የአንድን ፓርቲ የአመራር አካላት ለመምረጥም ሆነ ለመሻር የሚቻለው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ደንጋጌ መሰረት ሥልጣን በተሰጣቸው የፓርቲው አካላት ብቻ መሆኑን ነው:: በአንጻሩ ምርጫ ቦርድ የአንድን ፓርቲ አመራር የሚሾምበትም ሆነ የሚሽርበት አንቀጽ በሁለቱም አዋጆች ውስጥ ተፈልጎ አይገኝም:: ስለሆነም ኢ/ር ግዛቸውን የአንድነት ሊቀመንበር በማለት በመረጃ መረቡ ያሰራጨው ቦርዱበራሱ ፍላጉት ከሆነ ድርጊቱ ሕገ ወጥ ነው ::
ከፓርቲው በተሠጠኝ መረጃ ላይ ተመስርቼ ነው: መረጃውም በእጄ ይገኛል ቢልም ድርጊቱን ህጋዊ አያደርግለትም:: ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ 573/2000 አንቀጽ 19 « ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲን አንቅስቃሴ ይከታተላል ተገቢውን መረጃ ይይዛል» በማለት ያሰፈረውን በአንቀጽ 9/4/ «በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረግ እንቅስቃሴ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ማብራሪያ ወይንም መረጃ ሊጠይቅ ይችላል» ተብሎ ለቦርዱ ከተሰጠው ኃላፊነት ጋር አጣምረን ስናይ ቦርዱ የተነገረውን ብቻ ተቀብሎ ይሁንታ የሚሰጥ በአንድ ወገን የቀረበለትን ብቻ ተመልክቶ መረጃ ሳይጠይቅ የሚወስን አንዳልሆነ ወይንም መሆን እንደሌለበት አንረዳለን::
አዋጁ ከዚህም ያለፈ ሥልጣን ለቦርዱ ሰጥቷል: ፓርቲዎችም ትክክለኛ መረጃ ለቦርዱ መስጠት እንደሚገባቸው ግዴታ ጥሏል:: ቅጣትም ወስኗል:: ከላይ የጠቀስነው አዋጅ አንቀጽ 20/2/
« አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይንም የሰጠው መረጃ ሀሰት መሆኑን እያወቀ የሰጠ ከሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39/1/መ/ የተደነገገውን እርምጃ ከመውሰድ በተጨማሪ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል» ይላል::
እንግዲህ ቦርዱ ኢ/ር ግዛቸውን የአንድነት ሊቀመንበር በማለት በመረጃ መረብ ያሰራጨሁት ከፓርቲው በደረሰኝ መረጃ ነው ቢል መረጃውን ከማሰራጨቱ በፊት ከላይ በተገለጠውና በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በእጁ ከሚገኘው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና ብርቱካን በሊቀመንበርነት ከተመረጠችበት ቃለ ጉባዔ ጋር በማመሳከር ማጣራት ነበረበት:: ሁለትና ሶስት ሰዎች እየተባደኑ የሚወስኑት የፓርቲ ውሳኔ መሆን ከቻለ መተዳደሪያ ደንብ ለምን ያስፈልጋል:: ደንቡን ለቦርዱ መስጠትስ ምን ይረባል::

አሁን አንድነትን የያዙት ሰዎች ጉባዔ ስለማካሄዳቸው አይታወቅም:: ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው የመምረጥና የመሻር ሥልጣን ደግሞ የጠቅላላ ጉባዔው ነው:: ይህ ባልሆነበት ከአባላትና ከደጋፊው ተደብቆ ሹም ሽር ተከሂዶ ከሆነ የድርጊቱ ፈጻሚዎችም ሆኑ ሕገ ወጡን «መፈንቅለ ሥልጣን» ተቀብሎ ያጸደቀውና በመላው ዓለም በመረጃ መረቡ ያሰራጨው ቦርድ ጠያቂ ከተገኘ የሕግ ተጠያቂነት አለባቸው::
አጥፊው እንዲታወቅ ስህተቱ አንዲታረም ከመፈለግ በይሆናል የጀመርነውን ክርክር ከሁለቱም ወገን ምላሽ ያስፈልገዋል:: ከምላሹ አንዱ ወገን ራሱን ነፃ ሊያወጣ ይችል ይሆናል:: አሊያም ደረጃው የተለያየ ጥፋት ሁለቱም ላይ ሊገኝ ይችላል:: ምንም ሆነ ምን ላለፈው መተማመን ለወደፊቱም ጥንቃቄ ለማድረግ መግባባት ከተፈጠረ የዚህ አስተያየት ዓላማ ይኸው ነው:: ከአፈርኩ አይመልሰኝ ከተባለ ግን በይሆናል የተጀመረው ክርክር ከምላሹ በሚገኘው መረጃ «ነው» ወደሚል ደረጃ ያድጋል:: መልስ መንፈግ ግን አይበጅም ዝም ማለት ማመን ነውና::
የክርክራችን መሰረቱ ድርጊቱ ሕግን ተከትሎ የተፈጸመ አለመሆኑ አንጂ ኢ/ር ግዛቸው ለምን ሊቀመንበር ተባሉ አይደለም:: የሀገሪቱን ሕግ በሚፈቅደው የፓርቲውም ደንብ በሚደነግገው መሰረት ማንም ሰው ሥልጣን መያዝ ይችላል:: እስከተፈለገ እስከተመረጠና ችሎታው እስካለው ድረስ:: በአንጻሩ የፓርቲ ሥልጣን ርስተ ጉልት አይደለምና ማንም ሆነ ምን ሕጉ በሚፈቅድው አግባብ ሊሻር ይችላል:: በዚህ መልኩ የሚከናወንን ሂደት መቃወም ህግን መጻረር ነው የሚሆነው::
በትክክል ለህግ የበላይነት መረጋገጥ የቆመ ግለሰብም ሆነ ተቋም ሕገ ወጥ ድርጊትን የሚቃወመው ከፈጻሚውና ከተፈጸመበት ሰው ወይንም ቡድን ማንነት ጋር በማያያዝ መሆን የለበትም:: ማንም ፈጸመው ማን ሕገ ወጥ ድርጊት ሕገ ወጥ ነው:: የተፈጸመው በምንወደውም ሆነ በማንወደው ሰው ላይ ይሁን እኩል ሊሰማን ይገባል:: ፖለቲከኞቹም ይህን አይተውና ሰምተው ዝም ሊሉ አይገባም «ነግ በእኔ ነውና»:: ስለሆነም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመረጃ መረብ ላይ የሰፈረው የኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው የአንድነት ሊቀመንበርነት አንዴት በማን መቼ ወዘተ ነው የሆነው ብሎ መጠየቅ የህግ የበላይነት አንዲረጋገጥ የሚሻ ዜጋ ሁሉ ጥያቄ መሆን አለበት:: ይህን ማድረግ ስንችል ነው ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የፍትህ ሥርዓት መፍጠር የምንችለው:: በደፈናው «ነጻ» አይደሉም ከሚል ተቃውሞ ወጥተን የተቋማቱን ተግባር እየተከታተልን መተቸት ስንችል ድክመትና ስህተታቸውን ሲያልፍም ሕገ ወጥ ተግባራቸውን በመረጃ ማጋለጥ ስንችል ነው ለሰዎች ሳይሆን ለህግ ተገዢ የሆኑ ተቋማት ሊኖሩን የሚችሉት:: ቸር እንሰንብት የሳምንት ሰው ይበለን::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

## ል ዩ ቅ ኝ ት




ፎቶ፡- ሲሳይ ጉዛይ [091-1245811]

# ያፈነገጠው ባህላዊ ሁነት «ሆያ ሆዬ»

በአቤል ዓለማየሁ

ደብረ ታቦር በእስራኤል አገር የሚገኝ ተራራ ሲሆን ትርጓሜውም «ታቦር የሚባል ተራራ» ማለት ነው:: (ደብር ማለት ተራራ ማለት ነው) እየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ ወደ ታቦር ተራራ በመውጣት ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ቀን በመሆኑ ነው በዓሉ የሚከበረው::

«ወንድማማቾቹ ዮሐንስና ያዕቆብ እንዲሁም ጴጥሮስን ይዞ ወደ ተራራው ከወጣ በኋላ ከእነሱ ተሰውረው የነበሩትን ኤልያስን ህያው ነበረና ከገነት፣ ሙሴን ከመቃብር አምጥቶ ሲነጋገሩ ታዩአቸው:: እየሱስ ክርስቶስም ብርሃነ መለኮቱን ገለፀ:: መልኩ አበራ፤ ልብሱም እንደ ብርሐን ነጭ ሆነ:: ደቀ-መዛሙርቱም ደነገጡ:: መላክ ስለመሆኑም ተገልጦ ታይቷቸው «ከነብያት አንዱ እሱ ማነው?» እያሉ ይጠራጠሩት የነበሩት ጥርጣሬያቸውን በማስወገድ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ብርሃነ መለኮቱን ያሳየበት ቀን ነው::: «አርሞኤና ታቦር በአንተ ስም ይደሰታሉ» የሚለውም ትንቢት የተፈፀመበት ቀን ነው::» ሲሉ በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን መምህር ሐዲስ ትኩነህ ስለ በዓሉ አከባበር ምክንያት ያስረዳሉ::

በዓሉ በተለያዩ አካባቢዎች የራሱ የሆኑ ባህላዊ ዳራዎች አሉት:: በገጠር ቤተ-ክረስቲያናት በተለይ የቆሎ ተማሪዎች ሙልሙል ዳቦ፣ ጠላና ቆሎ አዘጋጅተው ዝክር ይዘክራሉ:: ካህናት ቁመት ይቆማሉ:: ታሪኩን የተመለከተ የያሬድን መዝሙር ይዘምራሉ፣ ድጓውን ይቃኛሉ:: ምዕመናንም በአምልኮ ስፍራዎች ተገኝተው በዓሉን ያከብራሉ::

## ቡሄ Vs ደብረ ታቦር

ከሣቴ ብርሃን ተሰማ አማርኛ መዝገበ ቃላት «ቡሄ» የሚለው ቃል ከዓረብኛ እንደተወሰደና ትርጓሜውም «ብርሃን» ማለት መሆኑን አስፍሯል:: ቡሄ ከደብረ ታቦር በዓል ጋር ተያይዞ በባህላዊ መልኩ የሚከበር በዓል እንጂ ምንም ሃይማኖታዊ ትርጓሜ የለውም:: መምህር ሐዲስ «ደብረ ታቦር ከቤተ-ክርስቲያን በዓላት አንዱ ሲሆን ቡሄ ግን በባህል/በተለምዶ ደብረ ታቦርን ተጠግቶ የሚያከብሩት በዓል ነው» ሲሉ ኃይማኖታዊ ትርጓሜና መልዕክት እንደሌለው ይገልፃሉ:: በክርስቲያናዊ በዓላት በዋዜማና በዕለቱ እንደሚከበሩ ሁሉ የደብረ ታቦርም ተመሳሳይ ነው:: በዓሉ መከበር የተጀመረበት በውል የታወቀ ጊዜ ባይኖርም ክርስትና በኢትዮጵያ ከተዋወቀበት ከአራተኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ እንደሆነ የኃይማኖት አባቶች ይናገራሉ::

በበዓሉ ችቦ የሚበራው በታቦር ተራራ እየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የነበረውን የብርሐን ብልጭታና ያሳየውን ብርሃን ለመመሰል ነው:: በደብረታቦር ዋዜማ ችቦ የሚያበሩ ክልሎች አሉ:: የሃይማኖት አባቶች ግን መብራት ያለበት በተገለጠበት ቀን ነሐሴ 13 መሆኑን ይናገራሉ:: ነሐሴ 16 የፍልሰታ ፆም ፍቺ ቀን ችቦ የሚለኩሱም አሉ::

በጐንደር አካባቢ ቡሄ ተብሎ የሚከበረው ነሐሴ 16 እና 17 መሆኑን መምህር ሐዲስ ትኩነህ ይገልፃሉ:: «በአገራችን በጐንደር ነሐሴ 16 እና 17 በዓሉ ይከበራል:: በተለይ የክርስትና አባትና ልጅ የሚጠያየቁበት ነው::»

የተገመደ ጉንጉን ጅራፍ የሚጮኸው ደግሞ እየሱስ ክርስቶስ ኤሊያስና ሙሴን ይዞ በተገለጠ ወቅት ከባድ የነጎድጓድ ድምፅ ስለተሰማ ያንን ለማሳየት እንደሆነ ይነገራል::

ደብረ ታቦርን ታከው «ሆያ ሆዬ» ጨዋታና ሙልሙል ደቦ ማዘጋጀት የተለመደ ነው:: ሁለቱም ግን ባህላዊ እንጂ ሃይማኖታዊ ስርዓት አይደሉም::

## ጐቤ

ለቡሄ፣ ለአዲስ ዓመትና ለመስቀል [ከቡሄ-መስቀል] በአዲስ አበባና አካባቢዋ የሚገኙ ቁጥራቸው ከአራት እስከ ስድስት የሚደርሱ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ዱላቸውን በመያዝ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ትኩረት ሳቢ ጭፈራ ማካሄዳቸው የተለመደ ነው::

ጐቤ ከቡሄ እስከ መስቀል በዓል ማዳረሻ የብሔሩ ተወላጆች የሚያካሂዱት ጭፈራ ነው:: ተስፋዬ አሰፋ፣ ደረጀ አሰፋ (ወንድማማች ናቸው)፣ በለጠ አኬኔ፣ በቀለ ነጋሽ፣ ብርሃኑ ነጋሹ የአንድ ቡድን የጐቤ ጭፈራ አባላት ናቸው:: ሁሉም የግብርና ባለሙያ ሲሆኑ የመጡት ከሰላሌ ነው:: ከነሐሴ 11-13 የጐቤ ጭፈራን ለማካሄድ ከገርጂ-መገናኛ፣ ከካዛንቺስ-ፒያሳ፣ ከኮተቤ-ሜክሲኮ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ቀናት አዳርሰዋል:: መኖሪያ ቤት፣ ምግብ ቤት፣ መጠጥ ቤት፣ የንግድ ሱቆችና ካፌ ብለው ሳይለዩ ሁሉምጋ ሰተት ብለው ገብተው ቦታውን ያደምቁታል::



እርጥብ ሳርና አልፎ አልፎም ጤና አዳም እንደ ዱላ ሁሉ በእጃቸው ላይ አይታጣም:: ገብተው ጭፈራቸውን በሚያስነኩበት ቤት ይበትናሉ ቀርበውም ላገኙት ሰው ይሰጣሉ:: ምልክቱም «እንደ ሳሩ ለምለምና እርጥብ ሁኑ፤ መልካም ይግጠማችሁ» ብሎ ለመመኘት ነው:: በጐዳና ላይ መንገድ ሲያቋርጥ ያገኙትንም ሆነ የትራፊክ መብራት ያስቆመውን ሰው ከበው በመጨፈር፣ እርጥብ ሳር (ቄጠማ) በመስጠት ኪሱን እንዲዳብስ ያግባቡታል:: ባህሉን በጠበቀ ሁኔታ እንደሚጨፍሩ የገለፀው በለጠ ያኬኔ ምንም እንኳ ከንግግሩ በፊትና በኋላ አስር ብር እንደሸልመው ያግባባኝ የነበረ ቢሆንም ዋና ትኩረታቸው ባህሉን እንዳይረሳ ማድረግ እንጂ ገንዘብ አለመሆኑን ይናገራል:: «መልካም ሰው ካገኘን እስከ ሃምሣ ብር ድረስ ይሸልመናል ክፉ ሰው ደግሞ እንዴት እየዞራችሁ ትውላላችሁ ብሎ ይናገረናል» ይላል ደረጀ አሰፋ ከኀ/ንጉርጉሩ ገጠመኛቸው መሃከል በጥቂቱ ጨልፎ ሲያሳይ::

የቡድኑ አባላት ከአስር ብር ያነሰ ሽልማት ያን ያህል ትኩረታቸውን ባይስበውም አልፋዳ (ክበሩ)፣ ጅራዳ (ኑሩ) ብለው ከመመረቅ ግን አይሰስቱም::

የአላፊ አግዳሚውን ስሜት በቀላሉ ከመስረቃቸውም በላይ የሚከተሏቸው ወጣትና ህፃናት አሉ:: ይህም በለጠ «ሰው ይወደናል» ብሎ ደስተኛ እንዲሆን አድርጐታል:: በተቃራኒውም «ለምን?» ብለው እንዲጠይቁ የሚያደርጉ አጋጣሚዎችን ያስተናግዳሉ:: ከሰሞኑ ባይገጥማቸውም ለጭፈራ በወጡባቸው ዓመታት «ርችት» መሀከላቸው፣ ኪሳቸውና ጫማቸው ውስጥ በመክተት እንዲደነግጡ የሚያደርጉ አሉ:: ደረጀ «ጥሩ አይደለም» ሲል ይህን አስነዋሪ ተግባር ይኮንናል:: ይህ ኢትዮጵያዊ መልክ የሌለው አዋኪ ድምፅ በዓላት በመጡ ቁጥር አካባቢዎችን ሲንጥ ሃይ ባይ አለማግኘቱ አስገራሚ መሆኑን እንደ ደረጀ ሁሉ ብዙዎችም ይገረሙበታል::

የእነ ደረጀ የጐቤ ቡድን «በገ ነጋን ሲገሄ» (እንኳን አደረሳችሁ) ብለው ገብተው «ኦጋ ኦጋን ሰኒ ሃገኡ» (ዓመት ዓመት ያድርሳችሁ) ብለው መርቀው እስኪወጡ ያገኙትን ገንዘብ መሳለሚያ ከፍለው ለማደሪያ፣ ለመመገቢያ፣ አንድ ሁለት እያሉ ከመገባበዝ የተረፈውን ሰላሌ ላይ ለመስቀል በሬ ገዝተው በማረድ ከወዳጅ ዘመድ ጋር በጋራ ደስታቸውን ይጋራሉ:: ጥሩምባ በመንፋት፣ ከቦታ በቦታ በመዘዋወር፣ እየዘለሉ በመጨፈር (ረገዳ) ያወጡትን ጉልበት እንደመተኪያም ይቆጥሩታል:: ቡሄ መጥቶ «ጐቢላ... ጐቢላ ጉቤ ጐቤን ጌሰኒ አደራ ሚካዔላ» እያሉ ወደ አዲስ አበባ መጥተው እስኪጨፍሩ ድረስ ባሉት አስራ ሁለት ወራት ግን ሽልማታቸው ስራ ነው፤ 85 በመቶ የኢትዮጵያ ህዝብን ቁጥር የያዘው ክፍል አካል (ገበሬ) ናቸውና የኋላ ደጀንነታቸውን ሞፈርና ቀንበር ሲያገላብጡ በመዋል ያረጋግጣሉ::

## «ሆያ ሆዬ ሆ...»

«ሆያ ሆዬ» ባህላዊ የልጆች ጭፈራ በብዙዎቹ የአገራችን ከተሞች ይደረጋል:: በአሁን ሰዓት ያሉት የጭፈራ አይነቶች ከቀድሞዎቹ ጋር ፍፁም ልዩነት እያሳዩ ብቻ ሳይሆን ንግድ ተኮር ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ ይነገራል::

አቶ ሰለሞን መንገሻ የተባሉ አንጋፋ አባት አገራቸው አንኮበር የነበረውና ኑሯቸውን በመሰረቱበት በአዲስ አበባ ያለው አጨፋፈር «ጐራማይሌ ነው» ይላሉ:: ቁጥራቸው ከአንድ መቶ የሚሻገር አዳጊዎች በቡድን ተከፋፍለው በደብረ ታቦር ዋዜማና በዕለቱ እንዲሁም በደመራና በመስቀል ቀን ብቻ በአንኮበር እየተዟዟሩ ይጨፍሩ እንደነበር ያስታውሳሉ:: «ሙልሙል ዳቦና ገንዘብ ይሰጠናል:: ገንዘቡን አጠራቅመን በሬ እንገዛበትና አርደን፣ ድንኳን ደኩነን በሬው እስከሚያልቅ ድረስ እንበላ ነበር፤ የምናድረውም እዚያው (ድንኳን ውስጥ) ነበር» ይላሉ:: በርበሬ ገዝተው ቀይ ወጥ፣ ቅቅልና ቁርጥ ለገበታ በማሰናዳት የሚመገቡት በጭፈራው የተሳተፉ ብቻ ናቸው:: «ያልተሳተፉት ድርሽ እንዲሉ አንፈቅድላቸውም ነበር::» በጭፈራ ወቅት

«የኔማ ጌቶች የሰጡኝ ሙክት
ግንባረ ቦቃ ባለ ምልክት
መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት»

እያሉ ያሞግሱ ነበር:: ዛሬ ግን መኪና እንኳን ሊነዳ መኪና ማቆሚያ የሌለውን ቤት እንዲመታ ብቻ በተሰደረ ግጥም

«እዚያ ማዶ በረኪና
እዚህ ማዶ በረኪና
የኔማ... ባለመኪና» እያሉ መሸንገን ባህልን እንደመሸርሸር ይቆጥሩታል:: «በቀድሞ ጊዜ እኛ ባህላዊ ስርዓቱን ጠብቀን እንጫወት ነበር:: አሁን ባህል እየተበረዘ ነው» በማለት አቶ ሰለሞን ግራ በተጋባ ስሜት ይገልፃሉ:: ይህን ስሜት ብዙዎችም ይጋሩታል:: መጪው ትውልድ «ሆያ ሆዬ»ን በቅጡ ሊያውቀው ስለመቻሉም ይጠራጠራሉ::

ባለ ዶክትሬቱን ባለ ዲግሪ፣ ሻለቃውን ሻምበል ባሻ በማለት ከክብርና ከደረጃ የሚያወርዱ፣ እግረኛውን ባለመኪና፣ ቤቱን ማስተዳደር ያልቻለውን የኢትዮጵያ ጀግና ብለው በሀሰት የሚያንቆለጳሱ ጭፈራዎች ከጨፋሪዎቹ ህፃናት አፍ ይደመጣል:: ሀበሻኛ ያልሆኑ ስሞችም እንደ ትልቅ ምርቃት ሐረግ ተቆጥረው ለማወደሻነት ይውላሉ:: ማይክል ጃክሰን (ነፍስ ይማር)፣ ባራክ ኦባማ፣ እግር ኳስ አንከባላዮቹ ክርስቲያኖ ሮናልዶና ሊዮኔል ሜሲ ይህ እድል ከደረሳቸው ውስጥ ይጠቀሳሉ::

«ጡት ጠብተው ያልጨረሱ» ተብሎ ቢገለፅ ብዙም ተጋነነ የማያስብሉ ህፃናት የጭፈራው አካል ናቸው፤ ሴት ህፃናትም እንዲሁ:: ህፃናቱ በሳንቲም ቤት ሲሰጣቸው ደስታ እንደማይሰማቸው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ ያገኘነው ቡድኑን የሚመራ ዮሴፍ ሰለሞን የተባለ ህፃን ነግሮናል:: በልጅነት አንደበቱ «የምጨምረው ለገንዘብ አይደለም በዓል (ባህል) ስለሆነ ነው» ቢልም «አድርሰናል» እያሉ ወይም እንዲጨፍሩ ባለመፍቀድ የሚያባርሯቸው ሲገጥማቸው ግን ንዴት ይወረው ነበር::

ሌሎች አስተያየት ሰጪዎች በልጆቹ ላይ ብቻ መፍረድ እንደማይቻል ይናገራሉ:: «ልጆቹን ማን ይንገራቸው? ያደጉት የሚያወርዱትን ጨፈራ እየሰሙ ከሆነ እንዴት እነሱ ባህሉን ጠብቀው ሊጫወቱ ይችላሉ?» ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ::

እንደ ደብረ ታቦር ባህላዊ ጭፈራዎች ሁሉ በበዓሉ ጅራፍ ማጮህና ጥሩምባ መንፋትም እየተረሳ የመጣ ይመስላል:: ቀጣዩ ትውልድጋ የሚደርሰው የቡሄ አጨፋፈር የትኛው እንደሆነ ማረጋገጫ መስጠት የሚችልም የለም:: ያፈነገጠው አጨፋፈር ራሱን ፈልጎ ያገኝ ይሆን?



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

## ዜ ና ዎ ች

# ኢንጅነር ግዛቸው በመርህ ይከበሮች ላይ መሰከሩ

በኤልያስ ገብሩ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ በዲሲፕሊን ጉደለት ምክንያት እንዳገዳቸው ከገለፀ በኋላ ራሳቸውን «መርህ ይከበር» በሚል መጠሪያ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም መሪነት በሚንቀሳቀሱት በ12 ግለሰቦች ላይ «ጠብና ሁከት ፈጥረዋል» በሚል በቀረበው ክስ ላይ በትላንትናው ዕለት በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ ፍትሐ ብሔር ችሎት የምስክሮች ቃል ተደመጠ::

ግለሰቦቹ የተከሰሱት በ1997 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 815 እና 823/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ሲሆን ተከሳሾች በ20/08/2002 ዓ.ም ከቀኑ 5:00 ሰዓት ሲሆን በቂ/ክ/ከ/ ቀበሌ 17/18 ክልል ልዩ ቦታው ባምቢስ ፊት ለፊት ገባ ብሎ ባለው አንድነት ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ውስጥ የድርጅቱ የፓርቲ አባላትና ሰራተኞች በስራ ላይ እያሉ ሰላም በመንሳት፣ ድንጋይ በመወርወርና ጠብ በመፍጠር በፈፀሙት ተግባር መከሰሳቸውን የወንጀል ዝርዝሩ ያስረዳል::

በዕለቱም በምርመራና ክስ ኤክስፐርት ከሳሽነት አምስት የሰው ማስረጃዎች በችሎት በመገኘት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል:: አንደኛ ምስክር የሆኑት አቶ ገዛኸኝ d¾K [የፓርቲው የጥበቃ ሰራተኛ] ችግሩ በተከሰተበት ወቅት በቦታው እንደነበሩ በመግለጽ የሚያውቁትን መስክረዋል::

ሁለተኛ ምስክር ወ/ሮ ገነት ሞገስ [የፓርቲው ፅዳት ሰራተኛ] ጥዋት ወደ ስራ ሲመጡ «የውጪ በር አይከፈትም» በመባሉ ወደ ውስጥ መግባት አለመቻላቸውንና ከግቢው ውጪ መቆማቸውን እንዲሁም ፖሊሶች ከመጡ በኋላ ፀብ አለማየታቸውን ገልፀዋል:: ከተከሳሾችም መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር::

ሦስተኛ ምስክር አቶ ወንደሰን ክንፈ [የፓርቲው አባል] በዕለቱ በጽ/ቤቱ ስራ ስለነበረበት ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ገደማ በስፍራው ሲደርስ ተከሳሾች ወደ ጽ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንገባለን ሲሉና በሌላኛው ወገን «አትገቡም» በሚል ፀብ መፈጠሩን፣ ድንጋይ ወደ ጽ/ቤቱ መወርወሩንና የውጪው በር መገንጠሉን ገልፀዋል::

ተከሳሾቹ ምስክሩ በዕለቱ ወደ ጽ/ቤቱ ቅጥር ግቢ እንደገቡ በማስታወስ እንዴት ወደ ውስጥ ሊገቡ እንደቻሉና ለበሩ መከፈትስ የእ/ር ግዛቸው እጅ አልነበረበትም ወይ? የሚል መስቀለኛ ጥያቄ ለምስክሩ አቅርበውላቸው ነበር:: ምስክሩም በወቅቱ የምርጫ ቅስቀሳ ስለነበር አባላት ወደ ውስጥ ገብተው ስራ መስራት ስለነበረባቸው በዚህ ምክንያት መግባታቸውን ጠቅሰው ኢንጂነር ግዛቸው በሩ ከመከፈቱ በፊት መኪና አስነስተው ከአካባቢው መሄዳቸውን ተናግረዋል:: በወቅቱ የተፈነከተ ሰው ነበር? ለተባሉትም «በድንጋይ የተመታ ሰው ቢኖርም የደማ ሰው የለም:: ከባድ ባይሆንም እኔም ተመትቻለሁ» ብለዋል:: በመጨረሻም ፖሊስ ከመጣ በኋላ ተከሳሾችን ከውጪ በር ላይ ይዟቸው እንደሄደ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል::

አራተኛ ምስክር የሆኑት አቶ ፋንታሁን መሀሪ [የፓርቲው ጥበቃ ሰራተኛ] በወቅቱ አዳሪ ጥበቃ ሰራተኛ እንደነበሩ፣ ከንጋቱ 12:00 ሰዓት ላይ በሚኒባስ መኪና የመጡ ግለሰቦች «በሩን ክፈትልን፤ እነ ኢንጀነር ለቅቀዋል» እንዳሏቸው፣ «በሩን አልከፍትም» በማለት ንጋት 12:30 ሰዓት ላይ ለኢ/ር ግዛቸው ስለጉዳዩ ስልክ መደወላቸውን፣ ኢ/ሩም «እኛ እስክንመጣ ድረስ ማን እንዳታስገቡ» ባሏቸው መሰረት ሰራተኞችንም ጭምር እንዳይገቡ እንዳደረጉ ተናግረዋል:: አያይዘውም ከተከሳሾች መካከል በዕለቱ ያዩዋቸውን ጠቁመው፤ በሩን ለመክፈት በሚታገሉበት ወቅት ከመከላከል ይልቅ በልመና መልክ ጉዳዩን ለማረጋጋት ጥረት ማድረጋቸውንና ድንጋይ ሲወረወር ማየታቸውን ገልፀዋል::

በዚህ ወቅት 5ኛ ተከሳሽ አቶ ታምራት ታረቀኝ በወቅቱ ስለነበረው ነገር ምስክሩን መስቀለኛ ጥያቄ እየጠየቁ እያለ አቃቤ ሕግ አቶ ታምራት «ለተከሰሱት ሰዎች እንደጠበቃ ሆነው መጠየቅ አይችሉም:: ራሳቸውን ብቻ የሚወክል ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው» በማለት ለፍ/ቤቱ ተቃውሞውን አቅርቧል::

አቶ ታምራትም «በተናጥል የቀረበብኝ ክስ የለም» ካሉ በኋላ ምስክሩን «እኔ እንግባ ስልና በር ጥሼ ስገባ አይተውኛል? በሚኒባስ መኪና ውስጥስ ነበርኩኝ?» ላሉት ጥያቄ «ሁላችሁም ከመኪናው ወርዳችኋል» ቢሉም ተከሳሹን ማየት አለማየታቸውን መመለስ አልቻሉም::

የመጨረሻው ምስክር ባሁኑ ወቅት የመድረክ ሊቀመንበር የሆኑት ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራሁ ሲሆኑ በዕለቱ ጥዋት ላይ ጥበቃው ስልክ ደውሎ ስለተፈጠረው ነገር እንደነገራቸው፣ በወቅቱም ሰዎች በቡድን መጥተው ወደ ፓርቲው ጽ/ቤት ለመግባት በፈለጉትና በፓርቲው አባላቶች መካከል የቃላት ውርወራ እንደነበር፣ ከቂርቆስ ፖሊስ መምሪያ ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር እና ም/ኮሚሽነሩ ድረስ ለችግሩ እልባት እንዲሰጥ ጥረት ማድረጋቸውን በመጨረሻም ካዛንቺስ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው «የፖሊስ ኃይል ይመጣል» እንደተባሉ ገልፀዋል::

ተከሳሾችም በተናጠል በወቅቱ እኔ ነበርኩኝ ወይ? አይተውኛል ወይ? ብለው ሲጠይቁ የተወሰኑት ደግሞ ጽ/ቤቱ ግቢ ውስጥ አብረን እንግባ ብለውን አልነበረም ወይ? ብለው ላቀረቡላቸው መስቀለኛ ጥያቄ «በወቅቱ የሰው ብዛት፣ ግርግር፣ የቡድን ስብስብ ስለነበር በተናጥል እከሌ፣እከሌን አይቻለሁ ለማለት እቸገራለሁ» በማለት በተደጋጋሚ ተናግረዋል:: እንዲሁም «ወደ ግቢ ውስጥ ለማስገባት አልፈቀድኩም» ሲሉ መስክረዋል::

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ለ19/12/2002 ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል::

# በከባድ የውንብድና ወንጀል ጥፋተኛ የተባለው ለብይን ተቀጠረ

ኤልያስ ገብሩ

በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛና 3ኛ ወንጀል ችሎት በከባድ የውንብድና ወንጀል ተከሶ እና የክስ ሂደቱ ታይቶ ጥፋተኛ የተባለው ግለሰብ በትላንትናው እለት በተሰየመው ችሎት ለመጨረሻ ብይን ተቀጠረ::

ሲሳይ ተሾመ የተባለው ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/1/1/ለን በመተላለፍ ካልተያዙ ሁለት ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ማግኘት ወይም ማስገኘት አስቦ በ27/10/98 ዓ.ም ከምሽቱ 3:30 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/05 ልዩ ቦታው ቦሌ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት የግል ተበዳይን አቶ አማኑኤል ታደሰን ያገኛቸዋል:: ግለሰቡንም በጩቤ የግራ ታፋቸውን እና የቀኝ እጃቸውን አውራ ጣት አንድ ጊዜ በመውጋት ራሳቸውን እንዳይከላከሉ ያደርጋቸዋል:: ያልተያዙ ግብረአበሮቹ ደግሞ ግምቱ 2400 ብር የሚሆን ኖኪያ ሞባይል፣ ሰባ ብር፣ ሦስት ግራም የአንገት ወርቅ እና 21 ካራት ግምቱ 750 ብር የሚያወጣ ሌላ ወርቅ ከተበዳይ በመውሰዳቸው ተከሳሹ ከላይ በተገለፀው ወንጀል እንደተከሰሰ የክስ ዝርዝሩ ያስረዳል::

ነሐሴ 3/2002 ዓ.ም ጥፋተኛ የተባለው ተከሳሽ በሌላ ክስ ከዚህ በፊት ተፈርዶበት ታስሮ የወጣ በመሆኑ የእድሜውን ግማሽ በወንጀል የኖረ እና መተዳደሪያው ያደረገ ስለሆነ እና ከህብረተሰቡ ጋር ሰላማዊ ሆኖ ይኖራል ተብሎ ስለማይታመን በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ አቃቤ ህግ ለፍ/ቤቱ አመልክቶ ነበር:: ፍ/ቤቱ በተከሳሹ ላይ ብይን ለመስጠት ለፊታችን ሰኞ ቀጠሮ ይዟል::

# ፖሊስ በህገ ወጥ መንገድ የገባን 36 ኪ/ግራም ሄሮይንና 276 ኪ/ግራም ካናቢስ በቁጥጥር ስር አዋለ

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት (2002) ብቻ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ሊዘዋዋር የነበረ 36 ኪሎ ግራም ሄሮይንና 276 ኪሎ ግራም ካናቢስ መያዙን አስታወቀ::

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽኑ የወንጀል ምርመራ ቡድን መሪ የሆኑት ዋና ኢንስፔክተር አስማማው ሂርቃ እንዳስታወቁት በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ በማስገባትና በማዘዋወር ሂደት የተሳተፉ 11 የውጭ ዜጎችና 25 ኢትዮጵያውያን በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስታውቀዋል::

ይህ አይነቱን ዕፅ የሚያዘዋውሩ ግለሰቦች የተለያዩ ዘዴዎች እንደሚጠቀሙ የገለፁት ዋና ኢንስፔክተሩ በተጠናቀቀው የበጀት አመት ኮሚሽኑ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ ይህ አይነቱ ወንጀል ካለፉት አመታት ጋር ሲነጻጸር በዚህ አመት እጅግ መቀነሱን ጠቁመዋል::

ኢትዮጵያ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ለመግታት የተባበሩት መንግስታት ኮንቬንሽን ከፈረሙ አገራት አንዷ መሆኗ ይታወሳል::

# ቤቴል ሜዲካል ኮሌጅ፣ ኪያሜድና ኬር ዩኒቨርሰቲ ኮሌጅ ዛሬና ነገ ተማሪዎችን ያስመርቃሉ

ቤቴል ሜዲካል ኮሌጅ በነርሲንግ፣ በፋርማሲ እና በላብራቶሪ ቴክኒሻንነት ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች ዛሬ በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎ በሚገኘው የስብሰባ ማዕከል ያስመርቃል:: ኮሌጁ በወንድ 55 በሴት 185 በድምሩ 240 ተማሪዎችን ያስመርቃል::

ኪያሜድ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በበኩሉ በነርሲንግ፣ በፋርማሲ እና በላብራቶሪ ቴክኒሻንነት ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች ነገ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ያስመርቃል:: ዩኒቨርስቲ ኮሌጁ 581 ሴት ተማሪዎችን እና 167 ወንድ ተማሪዎችን በድምሩ 748 ተማሪዎችን ነገ ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ያስመርቃል:: ዩኒቨርስቲ ኮለጁ ከሚያስመርቃቸው ተማሪዎች 32 ነፃ የትምህርት እድል ያገኙ እ ንደሆኑ ዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል::

ምተያያዘ ዜና ኬር ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በኬሚካል ነርሲንግ 94 ሴት ተማሪዎችን እና 39 ወንድ ተማሪዎችን በድምሩ 133 ተማሪዎችን ነገ ሐምሌ 16 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ስብሰባ ማዕከል እንደሚያስመርቅ አስታውቋል:: ኬር ዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ለ7 ተማሪዎች ነፃ የትምህርት እድል ሰጥቷል::

# ፀረ - ሙስና ኮሚሽን . . .

«ሙስናን ለመግታት ሀብትና ንብረት የመመዝገብ መርህ ግብር በተጠናከረ መልኩ እንደሚጀምር» ይግለጽ እንጂ አንዳንድ ወገኖች ግን በኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ላይ የተለያዩ ትችቶች ይሰነራሉ:: ከሚሰነዘሩ ትችቶች መካከል የኮሚሽኑ ትኩረት ከትልልቅ ባለስልጣናት ይልቅ ትንንሽ ባለስልጣናትን ብቻ ነው የሚያሳድደው፤ ትልልቆቹ ባስልጣናት ትኩረት የሚደረግባቸው ከፓርቲው ሲያፈነግጡ አልያም በ1993 ዓ.ም በህወሓት የተፈጠረው አይነት ክፍፍል ሲፈጠር ብቻ ነው በማለት ከአቶ ስዬ አብርሀ ውጭ ይህ ነው የሚባል ከፍተኛ ባለስልጣን በዚህ ጉዳይ እስካሁን አለመጠየቁን ያወሳሉ::

ሀብትና ንብረት የመመዝገብ አዋጅ ከአምስት ወር በፊት በመጋቢት ወር አጋማሽ በፓርላማ መጽደቁ ይታወሳል::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ



ሴቶች የሚወዱትን ወንድ እንደ መፈተን ምን ያስደስታቸዋል? ብትለኝ «ምንም» ነው መልሴ:: ለዛ የተዘጋጀህ ሁን:: በጓደኛዋ ልትፈትንህ ትችል ይሆናል:: አንተ ታዲያ ጥንካሬህን ካሳየህ ለእሷ እንዳንተ የሚያኮራት ሰው የለም::

ፍስሐ
vip@gmail.com

# በሷ ልብ እንድትቆይ...

## «በእኔ እይታ»

ብዙ ሴቶች በፍቅር ዓለም ውስጥ ያገኙት የመጀመሪያው ወንድ ሁሌ ከልባቸው አይጠፋም ይባላል:: ለምን ይመስልሃል?

ገና መጀመሪያ ግንኙነት ያወቀችው ሰው ለሷ አንዱ ለአንዱ ማሰብ መጀመርን ያስተማራት ሰው ነውና አትረሳውም፤ ለሷ ልክ ይሄን ዓለም መጀመሪያ ስትቀላቀል እንዳየችው ዓይነት ሰው ነውና አትዘነጋውም:: እሱ ለሷ ትክክል ነው - ፍፁም ትክክል::

ያን ዓለም እየተላመደች ስትመጣ ግን ነገሮችን ማገናዘብ ስለምትችል ከሱ ትክክለኛነት በተሻለ ደካማ ጎኑንም ማየት ትጀምራለች:: ያኔ መቃረን ሊመጣ ይችል ይሆናል:: አለመግባባት ቢፈጠር እንኳን በህይወቷ ቅድሚያ ለገባው ሰው ቶሎ ተስፋ ቆርጣ አትተወውም:: ነገር ግን ነገሮች ግድ ሆነው መለያየት ቢሆን እና ሌላ ከሱ የተሻለ አስተሳሰብ ያለው ሰው ጋር ብትተዋወቅ ይህን ሰው አትረሳውም:: ለሷ የሚቀጥለውን ሰው ማስተዋያ የሆናት የመጀመያው ነውና::

አንተም ከዛ ከመጀመሪያው ሰው በልጠህ መገኘት አለብህ እንደውም ከሱ ጋር እያነፃፀረች «በዚህ፤ በዚህ ይበልጠዋል» ብላ እንድታስብ በልቧ ውስጥ እንደ ቅርስ የሚቀመጡ አጋጣሚዎችን እና ልማዶችን ልታከማችላት ትችላለህ:: «የመጀመሪያው ሰው በህይወቴ ውስጥ መኖሩ ስህተት ነበር» እስክትል ድረስ አንተ በልጠህ ብትገኝ በአፀፋው ከሷ የምታገኘው ምላሽ ከአንተ በእጥፍ እንደሚሆን አትጠራጠር::

### በሷ ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዲኖርህ ትፈልጋለህ?

«አዎ» ለሆነው መልስህ ይሄን ልንገርህ:: አንዳንዶች አንድ የሚገርመኝ ባህሪ አላቸው:: የሴትን ልብ መሳብ የሚችሉት በሚመነዝሩት ብር ብቻ የሚመስላቸው [የሷን ልብ ለማማለል የአንድ ማኪያቶ ሒሳብ ለመክፈል የአንድ ውስኪ ሂሳብ ከኪሳቸው የሚያወጡ እንዳሉ ልብ ይሏል] እንዲሁም ባላቸው ታዋቂነት ብቻ የሚመስላቸው አሉ:: ታዋቂነትህና መንዛሪነትህ ለሷ ሁለተኛው ነገር ሊሆን ይችላል:: አንደኛው እና ዋንኛው ነገር ቢሆን እንኳ የሚጎዳው አንተኑ ነው:: እነዚህ ነገሮች ሲያልቁና ሲያበቁ ከሷ ጋር ያለህ ነገር ያከትማል::

### ማድነቅን ተማር

አንተ ልታስደስታት፣ ልትማርካት የምትችለው በዚህ ሊሆን ቢችልስ? ውጫዊ ውበቷን ማድነቅህ የሚጠበቅ ይሁን:: እሷ ያላትን ቆንጆ ነገር እንድታደንቅላት ትፈልግ ይሆናል:: ያ ብቻም አይደለም ውስጣዊ ውበቷን ከምንም ነገር በላይ እንደምታደንቅላት ንገራት::

### ለሷ ቅድሚያ እንደምትሰጥ አሳያት

እንበልና፤ አንተ ከሳምንት ውስጥ በአንዱ ቀን ከጓደኞችህ ጋር ለአንድ ሰዓት ተቀምጦ የማውራት ልምድ ቢኖርህ እሷ ያሉትን የተቀሩትን ሰዓቶች ላትፈልግህና ያቺን 1 ሰዓት ካንተ ጋር ማሳለፍ ልትጠይቅህ ትችላለች (ሆን ብላም ሊሆን ይችላል):: «ከጓደኞቼ ጋር እሆን ነበር.. ነገር ግን ከነሱ ጋር መሆን ከአንቺ ጋር እንደመሆን አያስደስተኝም» በላት - ያኔ ለሷ ቦታ እንዳለህ ትረዳለች::

### ለፈተና ራስህን አዘጋጅ /አትሸነፍ

ሴቶች የሚወዱትን ወንድ እንደ መፈተን ምን ያስደስታቸዋል? ብትለኝ «ምንም» ነው መልሴ:: ለዛ የተዘጋጀህ ሁን:: በጓደኛዋ ልትፈትንህ ትችል ይሆናል:: አንተ ታዲያ ጥንካሬህን ካሳየህ ለእሷ እንዳንተ የሚያኮራት ሰው የለም::

### አትዋሽ

ዛሬ ሆነ ብለህ የነገርካትን ሌላ ቀን ደግመህ እንድትነግራት ልትጠይቅህ ትችላለች:: ስለዚህ ከመዋሸት ተጠንቀቅ:: ቀድሞ የሰጠሀት መልስ እና ያሁኑ አንድ አይነት ካልሆነላት ሌላም ነገር ላይ እንዲህ እንደምትዋሻት አድርጋ ስለምታስብ ምን አልባትም ፍቅሯ ከስጋት ጋር የተቀላቀለ ሊሆን ስለሚችል ትክክለኛ ተናጋሪ ሁን::

### አስተውል

ዓይን ለማየት ብቻ የምትጠቀምበት ነገር መስሎህ ሊሆን ይችላል:: የየሰው የስሜት አገላለጽ ይለያየል:: ብዙውን ግዜ ሴቶች ለሚወዱት ወንድ ጠቅላላ ስሜታቸውን በዓይናቸው መግለጽ ያስደስታቸዋል:: ድምፃዊ ቴዎድሮስ ታደሰስ ቢሆን

«ትጥያለሽ አሉ በዓይን ቋንቋ ወሬ

እባክሽ አንሽልኝ አይንሽን ለዛሬ» ያለው ያለምክንያት ይመስልሃል:: አዝና ሊሆን ይችላል፣ ጥለሃት እንዳትሄድ ፈልጋ ሊሆን ይችላል፣ ብቻችሁን እንድትሆኑ ፈልጋ ሊሆን ይችላል:: ይሄን ሁሉ የምትነግርህ በአስተያየቷ ነውና አይኖቿን ማንበብ ተማር:: የውስጧን ካወቅክ ለእሷ እንዳንተ አስተዋይ ሰው የለምና ታስገርማታለህ::

### ፍላጎቷን ተከተል

በተለያየ አጋጣሚ እሷ «በፍቅር ዙሪያ» የሚሰማትን ስሜት በመረዳት አንተ ተግባር ላይ አውለው:: ምናልባት ያ ነገር ቀላል መስሎ ሊታይህ ይችላል ነገር ግን ለሷ ትልቅ ትርጉም ያለውና ስለሷ እንደምታስብ የምትረዳበት አንዱ መንገድ ነው:: አንዳንዴ ፊልም እያያችሁ ሊሆን ይችላል በሌላም አጋጣሚ ያየችውን ወንድ አፍቃሪ ድርጊት እንዳስደሰታት ባወቅህ ጊዜ አንተም ለሷ ስትል ድርጊቱን ለሷ ብትደግምላት ያን ክስተት ሁሌም የምታስታውሰው ሊሆን ይችላል:: የግድ የአንተን ማንነት የሚያሳጣህ መሆን ግን የለበትም::

ራስህን መጠበቅም ዋናውና መነሳት ያለበት ነገር ነው:: በአንድ ወቅት አንድ በቅርብ የማውቀውን ሰው «ከሴት ልጅ ከጥንቃቄ ጉድለት የሚረብሽህ ምንድነው?» ስል ጠየቅኩት:: «እጆቿ ላይ ያሉት ጥፍር ቀለሞች ሙሉ ቅብ ካልሆኑ (ወይ መልቀቅ አለበት ወይ ሙሉ ለሙሉ መቀባት አለበት)» ያ ስሜቱን እንደሚረብሸው ነገረኝ::

ሴቶችም በሚወዱት ሰው ላይ እንዲህ ያለ ጉድለት ካገኙ የመረበሽ ነገር ሊፈጠር ይችላል ባይ ነኝ:: ከላይ የጠቀስኳቸውን ነገሮች ከአንተ የልምድ ተሞክሮ ጋር በማጠናከር ተግባር ላይ ካዋልካቸው እና ለፍቅርህ የተጠየቀውን መስዋዕት ከከፈልክ - እመነኝ አንተ የእሷን ልብ ለዘለዓለም ትከራየዋለህ::

የእነዚህ ተቃራኒ ነገሮች የሚያስደስታቸው ሴቶች እንዳሉ አውቃለሁ:: ነገር ግን ትክክለኛ እና ጤናማ የሆነ ግንኙነት እነዚህ ነገሮች ያስፈልጉታል ባይ ነኝ::

በመጨረሻም ከቀድሞዋ «ህዳር» ጋዜጣ ያገኘሁትን አጭር አባባል ላካፍላችሁ::

«ሴት ልጅ የምትሰጣቸው የቤት ስራዎች አያቋርጡም:: የቤት ሥራ፣ ሌላ የቤት ሥራ፣ የቤት ሥራ ወዘተ ነው:: ስለዚህ ሁል ጊዜ ንቁ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበሀል:: አለዚያ አንድ ሚሊዮን አመት ሙሉ የደከምክበትን ውጤት ከአይን በፈጠነ ጊዜ ልታጣው ትችላለህ::

አንድ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር:: «...ሄዋንን በአምባገነንነት፣ በገንዘብ ወይም የልጅ እናት በማድረግ አስረህ ማስቀመጥ አትችልም:: እነዚህ ነገሮች የሚያስሩት መልሰው አንተኑ ነው!»

ለዚህ አባባል ፈላስፋውን ሳላመሰግን አላልፍም::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com



ጤ ና ካ ስ

◆ በኤልያስ ገብሩ

# በዓለም ዙሪያ ሚሊዮኖችን የሚያሰቃየው «የአጥንት መሳሳት»ሕመም

**በዛሬ «ጤና ካለ» አምዳችን የአጥንት መሳሳት «ኦስቲዮፓሮሲስ» ተብሎ የሚጠራውን የጤና ችግር ምንነት፣ መንስዔዎቹንና ሕመሙን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች መረጃዎችን በማጣቀስና ዶክተር አፅምሮ ከበደ የተባሉ የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት በማነጋገር ተከታዩን ጽሁፍ አዘጋጅተናል::**

የአጥንት መሳሳት ወይም «ኦስቲዮፓሮሲስ» ቃል በቃል ሲተረጎም «የተበሳሳ አጥንት» የሚል ፍቺ አለው:: ይህ ህመም ድምጽ አልባ ተብሎ የተጠራው አጥንት በድንገተኛ ጭነት፣ ግጭት ወይም መውደቅ ምክንያት እስኪሰበር ድረስ መሳሳቱን የሚጠቁም ምልክት ስለማይታይ ነው:: ስብራቱ በአብዛኛው የሚከሰተው ዳሌ፣ ጉድን፣ አከርካሪ ወይም የእጅ አንጓ ላይ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ኦስቲዮፓሮሲስን የሚያያይዙበት አቅም ደካማ ከመሆኑና በእድሜ ጠና ካሉ ሴቶች ጋር ነው:: ይሁን እንጂ ከጤና ሁኔታ ማየት እንደሚቻለው ኦስቲዮፓሮሲስ ወጣቶችንም ሊያጠቃ ይችላል::

## የበሽታው ችግርና መንስዔዎች

የአጥንት መሳሳት ብዙ ገጽታዎች ሲኖሩት «ፊዚዮሎጂካል» ከሆነ የዕድሜ መግፋት ጋር ተያይዞ በሰውነት ውስጥ ያለው የካልሲየም መጠንና ከአጥንት ወደ ደም፤ ከደም ወደ አጥንት የሚገባው የካልሲየም ዝውውርና ቁጥጥር እየተዛባ፣ አጥንት እየሳሳ በምግብ አማካኝነት ወደ ሰውነታችን የገባውንና ልንጠቀምበት የምንችለው የካልሲየም መጠን እየቀነሰ ይመጣል:: የአጥንት መሳሳቱ ችግር ተያይዞ ለመገጣጠሚያ በሽታዎችና ለአጥንት ስብራት ሊዳርግ ይችላል:: ስለዚህ የእድሜ መግፋት በኦስቲዮፓሮሲስ የመጋለጥን አጋጣሚ ይጨምራል:: በአብዛኛው በዕድሜ የገፉ ሰዎች አጥንታቸው እየደከመ ይሄዳል:: አንዳንድ ሰዎችም ከባድ የሚባሉ ጉዳቶች ሳያጋጥማቸው፤ ነገር ግን ስብራት ቢደርስባቸው «pathological fracture» ተብሎ የሚጠራው ችግር ሊያጋጥም የሚችልበት ሁኔታ አለ:: ሌላው ደግሞ በሽታ ሳይሆን ከወር አበባ መቅረት ጋር ተያይዞ የወር አበባን የሚቆጣጠሩ ሆርሞኖች በካልሲየም ቁጥጥር ላይ የራሳቸው ሚና ስላላቸው አጥንቱ እየሳሳ ይመጣል:: ሴቶች በሚያርጡበት ጊዜ አጥንት እንዳይሳሳ የሚከላከለው ኤስትሮጂን የተባለው ሆርሞን ይቀንሳል:: በኦስቲዮፓሮሲስ የሚሰቃዩ ሴቶች ቁጥር ከወንዶች በአራት እጥፍ ያህል የሚበልጠው በዚህ ምክንያት ነው:: የአንዲት ሴት ዘር አመንጪካል (ኦቫሪ) ቀዶ ሕክምና በመወገዱ ምክንያት የኤስትሮጅን ማነስ ስለሚፈጠር ከዕድሜ በፊት ማረጥ ሊያጋጥም ይችላል::

ይህንኑ ለመከላከል በተለይ ለነጭ ሴቶች የወር አበባቸው ከቆመ በኋላ ካልሲየም ይሰጣል:: እንዲሁም እንደበሽታ ሆኖ አጥንት መሳሳት የሚከሰትባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: ከነዚህ ውስጥ ኩላሊት እየታወከና እየደከመ ከመጣ የራሱን ቫይታሚን ዲ የተባለውን ንጥረ ነገር በመቆጣጠር ችግሩ እንዲከሰት ያደርጋል:: ይህም እንደ አንድ የበሽታ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል:: የስኳር በሽታ፣ እንቅርትና ካንሰር የመሰሉ የጤና ችግሮችም ለአስቲዮሮፓሮሲስ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በተጨማሪም ሆርሞኖች ለአጥንት መሳሳት መንስዔ ይሆናሉ:: በተለይ ፓራታይሮይድ ግላንድ ወይም ሆርሞን የሚባለው በደም ውስጥ ያለውና ወደ አጥንት እየገባ የሚወጣውን የካልሲየም መጠን በመቆጣጠር የዚህ ሆርሞን መብዛትና ማነስ ለአጥንት መሳሳት አስተዋጽኦ አላቸው::

ወላጆች የዳሌ አጥንት ስብራት አጋጥሟቸው ከነበረ ተመሳሳይ የሆነ ስብራት በልጆች ላይ የመድረሱ አጋጣሚ በእጥፍ ይጨምራል:: ሌላው መንስዔ አንድ ልጅ በእናቱ ማህፀን እያለ የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘቱ የተነሳ ከልጅነቱ ጀምሮ የአጥንት መሳሳት የማያጋጥመው መሆኑ ነው:: አንድ ሰው የአመጋገብና የአኗኗር ዘይቤውን በመለወጥ ለኦስቲዮፓሮሲስ የመጋለጥ አደጋን ሊቀንስ ይችላል:: ካልሲየምና ቫይታሚን ዲ ያነሰው አመጋገብ ለአጥንት መሳሳት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ ነው:: ብዙ ጨው መመገብም ሰውነት ብዙ ካልሲየም እንዲያስወጣ ስለሚያደርግ ለአጥንት መሳሳት መንስዔ ይሆናል:: ከመጠን በላይ አልኮል መጠጣት የአመጋገብ ሥርዓት ስለሚያዛባ ለአጥንት መሳሳት አስተዋጽኦ ያደርጋል::

አንድ ሴት በኦስቲዮፓሮሲስ የሚጠቃው የአመጋገብ ሥርዓት ከተዛባ፣ ይህ የአመጋገብ ልምድ የአልሚ ንጥረ ነገሮች እጥረት፣ መጠን ያለፈ የክብደት መቀነስና የወር አበባ ጥፋት ያስከትልባታል:: በዚህም የተነሳ ሰውነት ኤስትሮጂን የተባለውን ሆርሞን ማመንጨት ስለሚያቆም አጥንት ሊሳሳ ይችላል::

እንዲሁም ሰው በኦስቲዮፓሮሲስ እንዲጠቃ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት በቂ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ እንቅፋት የሚሆን የአኗኗር ዘይቤ መከተል ነው:: በተጨማሪም ማጨስ በአጥንት ውስጥ የሚገኙ ማዕድናትን ስለሚሸረሽር ለአጥንት መሳሳት ችግር ከሚያጋልጡ ዋነኛ መንስዔዎች መካከል አንዱ ሲሆን የዓለም ጤና ድርጅት እንደገለፀው የዳሌ አጥንት ስብራት ከሚደርስባቸው ስምንት ሰዎች አንዱ ይህ አደጋ የሚያጋጥመው በማጨስ ምክንያት መሆኑ ይነገራል:: ይሁን እንጂ አንድ ሰው ማጨስ ሲያቆም አጥንቱ የመሸርሸሩና ለስብራት የመጋለጥ ዕድሉ እንደሚቀንስ ጥናቶች ያመለክታሉ:: ከዚህ ባሻገርም ሰዎች በአብዛኛው በዚህ በሽታ የሚያዙት በዘር ውርስ ነው:: አንዳንድ ዝርያዎች ላይ በዚህ ምክንያት ለስብራት የመጋለጥ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል::

> በአብዛኛው በዕድሜ የገፉ ሰዎች አጥንታቸው እየደከመ ይሄዳል:: አንዳንድ ሰዎችም ከባድ የሚባሉ ጉዳቶች ሳያጋጥማቸው፤ ነገር ግን ስብራት ቢደርስባቸው «patho-logical fracture» ተብሎ የሚጠራው ችግር ሊያጋጥም የሚችልበት ሁኔታ አለ

## የአጥንት ስብራት

ዓለም አቀፍ የኦስቲዮፓሮሲስ ማሕበር እንደገለጸው «በአውሮፓ ሕብረት አገሮች በየ30 ሴኮንዱ አንድ ሰው በኦስቲዮፓሮሲስ ምክንያት አጥንቱ ይሰበራል» በዩናይትድ ስቴትስ 10 ሚሊዮን የሚያህሉ ሰዎች ኦስቲዮፓሮሲስ ያለባቸው ሲሆን 34 ሚሊዮን የሚያህሉ ሰዎች ደግሞ አጥንታቸው በመሳሳቱ ምክንያት በዚህ በሽታ ይጋለጣሉ የሚል ስጋት አለ:: ከዚህ በላይ ከሆናቸው ሁለት ሴቶች መካከል አንዷ አሊያም ከአራት ወንዶች መካከል አንዱ በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ ከአስቲዮፓሮሲስ ጋር ተያያዥነት ያለው የአጥንት መሠበር ያጋጥማቸዋል:: ለወደፊቱም ቢሆን ሁኔታው እንደሚሻሻል የሚያሳይ አዝማሚያ አይታይም::

የዓለም ጤና ድርጅት በኦስቲዮፓሮሲስ ምክንያት የሚደርስ ስብራት በመላው ዓለም በቀጣዮቹ 50 ዓመታት በእጥፍ እንደሚጨምር ገልጿል:: ይህ ትንበያ፣ እየጨመረ ይመጣል ተብሎ የሚታሰበውን የአረጋውያንን ቁጥር መሠረት ያደረገ ሳይሆን እንደማይቀርም ይገለጻል:: ያም ሆኖ የሚያስከትላቸው ውጤቶች በጣም የሚያስፈሩ ናቸው:: ኦስቲዮፓሮሲስ በአካል ጉዳት ወይም ለሞት የመዳረጉ አጋጣሚ በጣም ሰፊ ነው:: ሃምሳ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሆኗቸው የዳሌ አጥንት ስብራት ካጋጠማቸው ሰዎች መካከል ወደ 25 በመቶ የሚሆኑት በሚደርስባቸው የጤና ችግር ምክንያት ችግሩ በተከሰተ በዓመቱ እንደሚሞቱ ይነገራል::

## ችግሩን ለመከላከል

ኦስቲዮፓሮሲስን ለመከላከል የሚያስችል የመጀመሪያው እርምጃ መወሰድ ያለበት በልጅነትና በጉርምስና ዕድሜ ላይ ሲሆን የአንድ ሰው አጥንት 90 በመቶ የሚገነባው በዚህ ዕድሜ ላይ ነው:: ለአጥንት ጥንካሬ ወሳኝ የሆነው ካልሲየም ዋነኛ ምንጭ ከሆኑት የምግብ አይነቶች መካከል ወተት እንዲሁም እንደ እርጎና አይብ ያሉ የወተት ተዋጽኦዎች፣ የታሸገ ሰርዲንና ሳልመን (ከነአጥንቱ ሲበላ)፣ አልሞንድ የተባለው የለውዝ ዘርያ፣ አትሚል (ሲናር)፣ ሰሊጥ፣ የአኩሪ አተር ቺዝ (ቶፉ) እና ጠቆር ያሉ አረንጓዴ ቅጠላ ቅጠሎች ይገኙታል::

ካልሲየም በሰውነት ውስጥ እንዲዋሃድ ቫይታሚን ዲ የግድ አስፈላጊ ነው:: ይህ ቫይታሚን ቆዳችን ውስጥ የሚመረተው በፀሀይ ብርሃን በመሆኑ የውስጥ ደዌ ሐኪምና የሜክሲኮ የአጥንትና የማዕድናት ውህደት ማህበር አባል የሆኑት ማንዌል ግራስ ኦርቴጋ «በየቀኑ ለአሥር ደቂቃ ያህል ፀሀይ መሞቅ 600 ዩኒት የሚያክል ቫይታሚን ዲ ስለሚያስገኝ ኦስቲዮፓሮሲስን ለመከላከል አስተዋጽኦ ያደርጋል» የሚል ሙያዊ ምክር ይለግሳሉ::

በተጨማሪም ይህ ቫይታሚን ከእንቁላል አስኳል፣ በጨዋማ ባሕር ውስጥ ከሚኖሩ ዓሣዎች፣ ከጉበትና ከመሳሰሉት የምግብ ዓይነቶች ይገኛል::

ኦስቲዮፓሮሲስን ለመከላከል የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የላቀ ነው:: አካላዊ እንቅስቃሴ በልጅነትና በጉርምስና ዕድሜ አጥንት እንዲጠነክርና እንዲደነድን ሲያደርግ በእርጅና ዕድሜ ደግሞ አጥንት እንዳይሳሳ ይከላከላል:: በአጥንቶች በመገጣጠሚያዎች ላይ ብዙ ጫና ሳይፈጠር ጡንቻዎች እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርጉ እንደ ክብደት ማንሳትና የሰውነት ሃይል መቋቋምን የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ጥሩ እንደሆነ ይመከራል:: በእግር መሄድ፣ ደረጃ መውጣትና መጨፈር ወይም መደነስ ቀላል ሆኖም ውጤታማ የሆኑ የእንቅስቃሴ አይነቶች ናቸው::

ይህን ድምጽ አልባ በሽታ ለማሸነፍ አስቀደሞ የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ ነው:: ይህ ደግሞ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው አጥንት እንዳይሳሳ በአመጋገብና በአኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ ማድረግን ይጨምራል:: ብዙ እንቅስቃሴ የማይጠይቅ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ሰዎች በዚህ ረገድ ለውጥ ማድረግ ቀላል እንደማይሆንላቸው ይጠቀሳል:: ይሁን እንጂ አስፈላጊውን ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች በርካታ ጥቅሞች ያገኛሉ:: ከሚያገኟቸው ጥቅሞች መካከል የመጀመሪያው በዓለም ዙሪያ በኦስቲዮፓሮሲስ ከሚሰቃዩ በሚሊዮኖች ከሚቆጠሩ ሰዎች መካከል አንዱ ከመሆን መዳን ነው::


ማስታወቂያ ◁

ሠላም
የህፃናት መንከባከቢያና ማቆያ
SELAM DAY-CARE
• በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ባካበቱ ሙያተኞች
• ምቹና ፅዱ በሆነው ማቆያችን
ከ4 ወር - 3 ዓመት ድረስ ያሉ ልጆችዎን
ከ1፡30 - 12፡00 ሰዓት ድረስ ተንከባክበን እናቆይልዎታለን
አሁን እርሶ ቀኑን ያለስጋት በስራዎ ያሳልፉ!
ቅድሚያ ይምጡና ይጎብኙን
በተጨማሪም፡- ከ3 ዓመት በላይ ላሉ ለ2003 ዓ.ም ከነርሰሪ ጀምሮ ምዝገባም ጀምረናል::
አድራሻ፡- መገናኛ ሰም ሆቴል ፊትለፊት
☎ 0116 18 7477 0911 667143 /148881

ኤክስትሪም ኢንስቲትዮት
ወላጆች ፡- ልጆችዎ ትምህርታቸውን ሳይሰላቹ በቀላሉ ማጥናት ይችላሉ?
ያጠኑትንስ በአእምሯቸው በማስቀመጥ በፈተና ወቅት በአግባቡና በቀላሉ መመለስ ይችላሉ?
እንግዲያውስ
⇨ ከእንግዲህ ተማሪ ልጆችዎ በቀላሉ ማጥናት እንዲችሉ
⇨ ለቀጣይ በትምህርታቸው የተሻለና ውጤታማ እንዲሆኑ
⇨ የአእምሮ ብቃታቸው እና በራስ መተማመናቸው ጭምር እንዲጎለብት የሚያስችል
ይህን መሰረታዊ የሆነ ሳይንሳዊ ዘዴዎች እና ሥነ ልቦናዊ ጥበቦች
የአጭር ጊዜ ልዩ ሥልጠና
እንደ አምናው ለዘንድሮም በኤክስትሪም ኢንስቲትዩት አማካኝነት
በከፍተኛ ሳይኮሎጂስቶች ጥምረት
ፒያሳ በሚገኘው ካቴድራል ት/ቤት ግቢ
ለክረምቱ በከሰዓት በኋላ ፈረቃ ይሰጣል
አሁኑኑ ከ1ኛ ደረጃ—ኮሌጅ መሰናዶ ያሉ ልጆችዎን አስመዝግበው ያስጀምሯቸው::
በተጨማሪም ፡-ለቢጋው በወትር ቅዳሜ ጠዋት ለሚሰጠው ፕሮግራም ከወዲሁ ምዝገባ መጀመራችንን እናሳውቃለን::
ለበለጠ መረጃ- 0913 61 87 58 ☎0116 55 49 86

ተጠየቅ

በኤልያስ ገብሩ

# የአክሲዮን ማሕበራት አዲስ የምዝበራ ሥልት

## (የመጨረሻ ክፍል)

ሰፉት ሶስት ሳምንታት በ«ተጠየቅ» አምዳችን የ«አክሲዮን ማህበራት ጋጋታና አዲስ የምዝበራ ስልት» በሚል ርዕስ የአክሲዮን ማህበራትን በሚመለከት፣ ህብረተሰቡን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች በመያዝ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በቻልነው አቅም በማነጋገር ተገቢውን መረጃ ለህብረተሰቡ ለማቅረብ ጥረት አድርገናል:: በጉዳዩ ላይ በሶስት ተከታታይ ክፍሎች ያቀረብናቸው ሀሳቦች ትምህርት ሰጪ ናቸውም ብለን እናምናለን:: አዎንታዊ እንዲሁም አሉታዊ አስተያየቶችም ደርሰውናል::

አዲስ ነገር ወደአገራችን በሚገባበት ጊዜ ወቅቱን የጠበቀ ትክክለኛ ግንዛቤን የሚፈጥር መረጃ በፍጥነት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ በአገራችን አልተለመደም:: እናም አክሲዮን ማህበራትን በተመለከተ ያሉ ችግሮችን፣ ድክመቶችን፣ ጥንካሬዎችንና ሊስተካከሉ እንዲሁም ሊወሰዱ ስለሚገቡ እርምጃዎች በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ግንዛቤ የመፍጠርና ትክክለኛ አቅጣጫ መጠቆም ተገቢ ነው እንላለን::

ባቀረብናቸው ጽሑፎች ላይ አስተያየታቸውን ከሰጡን የአክሲዮን ማሕበራት መካከል ጃካራንዳ አግሮ ኢንዱስትራ አ.ማ አንዱ ነው:: የአክሲዮን ማህበሩ ዋና አደራጅና ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ደምመላሽ፣ በዝግጅት ክፍላችን የወጡት ጽሁፎች እንዳስደሰታቸው በመግለጽ፣ «ከእናንተ [አውራምባ ታይምስ] ዘገባ በኋላ በአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት ንግድና ልማት የሚለው ጋዜጣ የአክሲዮን ማህበራትን አደረጃጀትና ሂደት አስመልክቶ» ዘገባ መውጣቱን አስታውሰው፣ «የአክሲዮን ማህበራት የሚሰሩት ከግለሰቦች ጋር ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡም ጋር ስለሆነ፣ ዘገባው ህብረተሰቡ አውቆበት ለሚመጣው ነገር የተሻለ ነገርን ይፈጥራል» ብለዋል:: ጨምረውም፣ «ለህብረተሰቡ ጥሩ ጥሩ ጥያቃዋች ስለተጠየቁ፣ ለጥያቃዎቹ ጥሩ መልስ ያገኘ ሰው ወደአክሲዮን ማህበራት ሲመጣ በተወሰነ ደረጃ ገልጽ ሆኖሎት ነው:: ማን ምን እየሰራ ነው? እንዴት ማድረግ ይሻላል? ማህበራቱስ ለእኔ ምን ይጠቅሙኛል? የሚሉትን ነጥቦች አውቆ ሲመጣ የሚወስነው ውሳኔ ትክክል ሊሆን ይችላል» ሲሉ ተናግረዋል::

ጽሑፎቹ ሕብረተሰቡን የማንቃት ሚና፣ ለሕብረተሰቡን እና ለመንግስት ድጋፍ የሚያደርጉ ሀሳቦች እና የመንግሰትንም ስራ የሚያቃልል ሁኔታን በጥቂቱም ቢሆን እንደሚፈጥር ጠቅሰው፣ በዘርፉ ህብረተሰቡ አንዴ እንደተጭበረበረ ከተሰማው አክሱዮን ማሕበራትን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም የማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንሚችልና ያ ከሆነ ደግሞ አገሪቷን ወደተሻለ የልማት ጐዳና ለማሸጋገር ከግለሰባዊ ባለኃብትነት ባሻገር ማህበራዊ የኃብት ባለቤትነት የግድ አስፈላጊ እንደሆነ አቶ ደምመላሽ ገልፀዋል: ድርጅቶች ጥሩ የሕግ መሰረት ይዘው ካልሄዱ፣ ከመነሻቸው ችግር ከተፈጠረባቸው ህብረተሰቡ በነሱ ውስጥ ለመሳተፍ የማይችልባቸው ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ጠቁመዋል::

ምናልባት በጽሁፎቹ ላይ የነበሩ ድክመቶች፤ መነሳት የነበረባቸው ነገር ግን ያልተነሱ ነገሮች ካሉ እንዲገልፁልን ለዋና ሥራ አስኪያጁ ጥያቄ አቅርበንላቸው ነበር:: በምላሻቸውም፣ «በጽሁፉ ላይ አሁንም ይቀረዋል ብለን የምንላቸው ነገሮች አሉ:: ዘገባውን የተወሰኑ የአሰራር ክፍተት ያለባቸው ማሕበራት ላይፈልጉት ይችላሉ:: የአሰራር ጥንካሬ ያላቸው ግን ሊደግፉትና ሊያመሰግኑ ይገባል» ካሉን በኋላ፣ «አክስዮን ማሕበራት ለሕብረተሰቡና ለአገር ልማት ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳላቸው፣ ማሕበራቱን ለማቋቋምና አብዩታዊ ለውጡ ለምን እንደሚያስፈግ፣ ለዚህም የሕግ መሠረቱ ሊኖር የሚገባው እንዴት እንደሆነ የሚሉት» ቢካተቱ ጥሩ እንደሚሆን ተናግረዋል::

በአዋሽ፣ በቡኢ፣ በናዝሬት፣ በሐዋሳና በአዲስ አበባ ከተማዎች ማሕበራቸው ለበርካታ የአካባቢዎቹ ሰዎች፣ ለመንግስት አስፈፃሚ አካላት፣ ለኢትዮጵያ ንግድ ም/ቤት ህዝብ ግንኙነት ባለሙያና ለ10 የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች ስለኩባንያው ዓለማ፣ የስራ ሂደትና፣ ሕጋዊ የአመሰራረት ሁኔታዎች እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ አምስት የግንዛቤ ማስጨበጫ ፎረሞችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ግንዛቤን ከመፍጠር አኳያ የቻሉትን እንደሰሩ የጃካራንዳ ዋና ስራ አስኪያጅ አስረድተውናል::

ስለማሕበራቸው መረጃ ለሕዝብ ሲያስተላልፉ የተጠቀሙት ማስታወቂያ ግነት የነበረው መሆን አለመሆኑን ጠይቀናቸው፣ «ማንኛ ውም የኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያ ለጃካራንዳ ማስታወቂያ ከመስራቱ በፊት የሚሰሩ ስራዎችን በስራ ቦታ ወይም «ሳይት» ድረስ በአካል ተገኝቶ በመመልከት፣ የሚሰሩትን ነገሮችና ያለውን ነገር በማረጋገጥ ብቻ» እንዲተዋወቅ ማድረጋቸውን በማስታወስ ስራ አስከያጁ ምላሻቸውን ሰጥተውናል::

«ጃካራንዳ ከመጀመሪያው ጀምሮ አሁን እስከሚገኝበት ደረጃ ድረስ በንግድ ሕጉ ላይ የተደነገጉትን ሕጎች ተግባራዊ እያደረገ መጥቷል ወይ? በአካሄዳችሁስ ላይ ችግር አልነበረም?» ለሚለውም፣ «ማንኛውም ድርጅት ሲቋቋም የሚገጥሙት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ስለዚህ ጉዳይ እኛ ከምንናገር ይልቅ እኛን ሊመረምር የሚችል ስልጣን ያለው አካል ቢያይልን ደስ ይለናል:: ሆኖም እስከዛሬ ድረስ ምንም ነገር ሳይሰማብን እዚህ ጥሩ የስራ ሂደት ላይ የደረስነው በንግድ ሕጉ መሰረት የተገለፀውን ተግባራዊ በማድረጋችን ነው» ሲሉ መልሰውልናል::

«በግለሰብም ሆነ በተቋም ደረጃ፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስህተት ሊሰራ ስለሚችል፣ እናንተ በዚህ ረገድ ከሕግ አግባብ ውጪ የወጣችሁበት ሁኔታ በጭራሽ የለም?» ለሚለው ጥያቄያችን ስራ አስኪያጁ፣ «እስከ አሁን የታየ ነገር የለም» ካሉ በኋላ፣ «በንግድ ሕጉ ላይ በግብርና ዘርፍ ላይ የሚቋቋሙ አክስዮን ማህበራት በምን ያህል የገንዘብ ካፒታል መጠን ስራ መጀመር እንደሚኖርባቸው ባለመገለጹና ዘርፉንም የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ «ባለማወቅ የተሳሳትነው ነገር አልነበረም» በማለት ምላሽ ሰጥተውናል::

በአክሲዮን ማሕበራት ላይ ለሚነሱ ችግሮች ሁሉም ማሕበራት በጅምላ መታየት እንደማይኖርባቸው ከአንድ የዘርፉ አዳራጅ የተገለጸ አስተያየት አንስተንባቸው «ሚዲያ መፈጠሩ ማን ጥሩ እና ማን በትክክል እንደማይሄድ፣ ማን ተሳስቷል? ማን መስተካከል አለበት? አሁን ያሉት ማሕበራት ላይ ህብረተሰቡ እምነት እንዲኖረው መጠንከርና መከተል ያለባቸውን መመሪያ አውቀው በመያዝ እንዲሄዱ» እንደሚያደርግ የተናገሩት አቶ ደምመላሽ፣ «ችግሮች ችግር ይባላሉ እንጂ ችግሮች አስተማሪዎች ናቸው፣ ከችግር በመነሳት መፍትሔ ማምጣት ይቻላል፤ የዘገባው መውጣት እያንዳንዱ ራሱን እንዲፈትሽ፣ ፍተሻውም ለጥሩ ብቃት የሚያበቃ ነው» ብለው እንደማይገምቱ ጠቁመው «ሁሉም አንድ ላይ ተጨፈለቀ አልተጨፈለቀ ብቃት ያለው ብቃቱን ይዞ ይሄዳል:: ብቃት የሌለው ደግሞ ብቃት እንዲኖረው ራሱን ይገመግምበታል» በማለት ሀሳባቸውን አጠቃልለዋል::

በአንጻሩም የህብር ስኳር አክስዮን ማሕበር ኃላፊ የሆኑት አቶ ምናላቸው ስማቸው በሰጡት አስተያየት ማሕበራቸው ሕግን ተከትሎና አክብሮ እየሰራ እንደሆነ፣ ማንኛውም አካል ሕግን ተከትሎ መስራት እንዳለበት፣ ህብረተሰቡም በህጋዊ መንገድ እየሰሩ የሚሄዱትን ማሕበራት አጣርቶ አክስዮን መግዛት እንደሚኖርበት ምክራቸውን ከለገሱ በኋላ በዝግጅት ክፍላችን የቀረቡትን ተከታታይ ጽሁፎች በተመለከተ «ከርዕሱ ጀምሮ ትክክል ነው ብዬ አላምንም:: በትክክልና በሕጋዊ አካሄድ የሚሄዱ ማሕበራትን በአጠቃላይ በጅምላ የመፈረጅ አዝማሚያ አይቼበታለሁ» ሲሉ ተናግረዋል::

አቶ ሰለሞን ልዑልሰገድ የተባሉት የሸገር ሜትር ታክሲ አክስዮን ማህበር ስራ አስያኪያጅ ድርጅታቸው አክሲዮኖችን ሙሉ በሙሉ ሸጦ አለመጨረሱን፣ ለዚህም ሕብረተሰቡ ባለው አክሲዮኖችን የመግዛት እውቀት ማነስና የማስታወቂያ ችግር ምክንያት እንደሆነ በመግለጽ ሊያስራቸው የሚችለውን የገንዘብ መጠን ስለሰበሰቡ ለተግባራዊ ስራው የመኪኖችን ግዢ ጨርሰው በጥቅምት ወር 2003 መጨረሻ ላይ ስራ እንደሚጀምሩ ያስረዳሉ::

የሕብረተሰቡ የእውቀት ማነስ ችግር ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አክሲዮን ሽያጭ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ባሉት ጊዜያት ባለመኖሩ ምክንያት ህብረተሰቡ የአክስዮን ማስታወቂያዎችን ከተመለከተ፣ ከሰማና ካነበበ በኋላ ሳይወተውት እንደማይገዛ ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል:: በተገቢው ጊዜ አክሲዮኖችን ሸጠው ወደስራ ለመግባት ያልቻሉበትን ትክክለኛ ምክንያት አቶ ሰለሞን ሲያስረዱ አክሲዮን ሽያጩን የጀመሩት በመስከረም (ጥቅምት 2000 ዓ.ም) ሆኖ ሳለ በስድስት ወር ውስጥ ለማጠናቀቅ ቢያቅዱም የሽያጭ ገበያው እንዳሰቡት ቀላል ስላልነበር ሽያጩን ለአንድ ዓመት ያህል አራዝመው የሰበሰቡት ገንዘብ በመያዝና ጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት ከባንክ ተጨማሪ ብድር የሚያገኙበትን ሁኔታ በማለም ወደ ቀጣይ እርምጃ መግባታቸውን፣ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ መ/ቤት ጉዳያቸውን ለመጨረስ ጊዜ ስለፈጀባቸው «ሁሉም ነገሮች በቀላሉ የሚጠናቀቁ አልነበሩም» የሚሉት ስራ አስኪያጁ መ/ቤቱ ስራ በዝቶበት ዛሬ ነገ እያለ እንዳጓተተባቸው በመጥቀስ ድርጅታቸው ያቀረበው የሰነድ ዝርዝር ብዛት ስለነበረውና ለስራ የመረጡት ዘርፍ አዲስ በመሆኑ የተወሰኑ ቃለ-ጉባዔዎችን በማስተካከል ቢያንስ በሁለት ወር ማለቅ የነበረበት ጉዳይ አምስት ወር መፍጀቱንና ለዚህም የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ መ/ቤትን ቀዳሚ ተጠያቂ ቢደርጉም በመጨረሻ ተመስጋኝነው መለያየታቸውን አቶ ሰለሞን ገልጸዋል::

እንዲሁም ከባንክ ብድር ለማግኘት ሶስት ወራት እንደፈጀባቸው አልሸሸጉም:: «ለመዘግየታችሁ ሕብረተሰቡን እና አስፈፃሚ አካላትን እንደዋነኛ ምክንያትነት አቅርባችኋል:: እናንተ አደራጆች ተጠያቂ አልነበራችሁም ማለት ነው?» በማለት ላቀረብንላቸው ጥያቄ፤ «ችግሩ የለም አንልም፤ አለ:: እቅድ ሲወጣ በምን ያህል ጊዜ የአክስዮን ግዥ ተገኝቶ ይጠናቀቃል የሚባልበትን ትክክለኛ ጊዜ ያለማወቅ ችግር ነው:: ከዚህ በፊት ተሞክሮ አልነበረንም:: አክስዮን ሸጠን እንጨርሳለን ያልንበት የጊዜ ግምት ትክክል አልነበረም» በማለት ስራ አስኪያጁ ችግር እንደነበረባቸው አምነዋል::

«ማህበሩን አቋቁማችሁ በተባለው ጊዜ ባለመጀመራችሁ ምክንያት ባለአክስዮኖች ዝም ነበር ያሉት?» ለተባሉት አቶ ሠለሞን፤ ባለአክስዮኖች መጥተው የሚጠይቁ መኖራቸውን አስረድተው ወደስራ ለመግባት የዘገዩበትን ምክንያት በመንገርና ዋነኛ የችግራቸው ምንጭ ሶስተኛ አካል እንደሆነ በማስረዳት ከባለአክስዮኖች ጋር መስማማት ላይ መድረሳቸውን አስታውሰው፣ አክስዮን የገዛ አንድ ግለሰብ ከባድ ችግር እንደደረሰበት በማስታወቁ ገንዘቡ እንደተመለሰለት አስረድተዋል:: ይህ አክስዮን ማህበር በመቶ ታክሲዎች ስራ ለመጀመር አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ በ2000 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ አክስዮን መሸጥ ሲጀምር 100 ያህል ዘመናዊ ታክሲዎችን በመያዝ ስራ እንደሚጀምር ቢያቅድም፣ ከታቀደው በታች ወደስራ መግባታቸው በገቢያቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደማይፈጥር ገልጸዋል::

> **«የአክሲዮን ማህበራት የሚሰሩት ከግለሰቦች ጋር ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡም ጋር ስለሆነ፣ ዘገባው ህብረተሰቡ አውቆ ለሚመጣው ነገር የተሻለ ነገርን ይፈጥራል»**

ባለፈው ዓመት አክሲዮን በመሸጥ ላይ የነበረው ኮሞሮስ አጠቃላይ ንግድ ሥራ አ.ማሕበር በአሁን ወቅት ስላለበት ደረጃ ለመጠየቅ በአደራጆች ስልክ ደውለን ስልካቸው አልተነሳም ነበር:: ከዚያም በተደጋጋሚ ባደረግነው ጥረት ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉት አደራጅን በሞባይላቸው አግኝተናቸው ነበር:: ስለጉዳዩ ስንነግራቸውም ክ/ሀገር መሆናቸውን ገልፀውልን «ማስታወቂያ ፈልጋችሁ ነው ወይ?» የሚል አስገራሚ ምላሽ ሰጥተዋል:: አገሬ ኮንስትራክሽንና ሙሉ መሶብ ፋስት ፉድስ የተባሉ አክሲዮን ማህበራትም በአሁኑ ወቅት ምን እየሰሩ እንደሚገኙና ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለመጠየቅ ጥረት ብናደርግም፣ የአደራጆቹ ተንቀሳቃሽ ስልክ ዝግ እና «መስመሩ አገልግሎት ላይ አልዋለም» የሚለውን የቴሌኮሙኒኬሽን አውቶማቲክ መረጃ ሰጪዎች በተደጋጋሚ ስላደመጥን በዚህ ጽሁፍ ላይ አስተያየታቸውን ማካተት አልቻልንም::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# «የኢትዮጵያ ተጨዋቾች እንኳን አሰልጣኝን አምላክን ያታልላሉ»



በአቤል ዓለማየሁ
abel.awramba@gmail.com

በኢትዮጵያዊው የሮምና የቶክዮ የማራቶን ድል ባለቤት አበበ ቢቂላ ስም በአዲስ አበባና በአዳማ ሁለት የመታሰቢያ ስታዲየሞች አሉ፡፡ የአዳማው የመጫወቻ ሜዳ በዓመቱ መጀመሪያ መጠነኛ እድሳት ሳይደረግለት በፊት «እግር ኳስ ሜዳ» ብሎ ለመጥራት ያሳፍር ነበር፡፡ የአዲስ አበባው አበበ ቢቂላም ቢሆን ያለንን የድህነት ደረጃ ግምት ውስጥ ከትቼም ቢሆን ደፍሬ «የእግር ኳስ ሜዳ» ለማለት ብደፍር «ደፋር» እንደምትሉኝ አስባለሁ፡፡ በተለይ ዝናብ ሲጥልና በክረምት ወራት ለምርጊት እንደተዘጋጀ ጭቃ በመላቆጥ እንኳን ኳስ ለማንከባለል ለመሮጥ አያስችልም ነበር፡፡

ዛሬ የአዳማው ሜዳ ባይሰምርለትም በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፈር ቀዳጁ አትሌት ስም የተሰየመው የአዲስ አበባው ስታዲየም ሜዳ ግን ያለፈ ታሪኩ የሚያስረሳ ቀን ወጥቶለታል፡፡ ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማኀበር (ፊፋ) ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በመፍቀድ ሰው ሰራሽ ሳር፣ ለሳሩ ማልበስ የሚረዳ አሸዋና ረጂ ማሽኖች አዲስ አበባ በመድረስ ሜዳውን አዘምነውታል፡፡ ከተጠናቀቀ ሁለት ሳምንት የሞላው የክልል ሴቶች እግር ኳስ ሻምፒዮናም ሜዳውን አሟሽቶታል፡፡

በሳምንቱ አጋማሽ ከዚህ ውብ ሜዳጋ የተፋጠጥኩት በእንግሊዛዊው ኦፌም ኦኔራ የሚሰለጥነው የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ላለበት ጨዋታ አቋሙን ለማወቅ ይረዳው ዘንድ ከኬኒያ አቻው ጋር ያደረገው የወዳጅነት ጨዋታን ለመመልከት ነበር፡፡

የደደቢቶቹ ተከላካዮች ዳንኤል ደርበና መንግስቱ አሰፋን፣ የቅ/ጊዮርጊሶቹን ሳምሶን ሙልጌታ (አምበል) እና አበባው ቡጣቆ ከኋላ በማቆም በመጀመሪያው 45 ደቂቃ ወደ ሜዳ የገባው የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ይሄ ነው የሚባል ሊወራ የሚችል እንቅስቃሴ ሳያደርግ የመሐል ዳኛው ኢንተርናሽናል አርቢትር ዘካሪያስ ግርማ የመጀመሪያው የጨዋታ ክፍል መጠናቀቁን የሚገልፅ የፊሽካ ድምፅ ተሰምቷል፡፡

የቡድኑ አሰላለፍ በጨዋታ ላይ አይደለም፤ በአቋቋም እንኳን ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ኳስን በአግባቡ ለመቀባበልም ሲቸገሩ ተስተውሏል፡፡ የቡድኑ የግራ መስመር ተመላላሽ ተከላካይ የሆነው አበባው ቡጣቆ ከመሀከልና ከመስመር ተሰላፊዎች የሚደረሱት ኳሶች እያመለጡት በተደጋጋሚ ወደ ውጪ ይወጡበት ነበር፡፡ ሁሉም የተከላካይ ክፍል ተጨዋቾች ማለት ይቻላል ደካማውን በአንጋፋው አሸናፊ ግርማ የሚመራውን የመሐል ክፍል ለመርዳት የሚያደረጉት ጥረት ደካማ ነበር፡፡ ያለ ኳስ ምንም አይነት እንቅስቃሴ አያደርጉም ነበር፤ «ኳስ ካቀበላችሁ በኋላ ቁሙ» የሚባል መመሪያ የወረደላቸውም ጭምር፡፡

የመሐል ክፍሉ የተሳኩ አጭርም ሆነ ረዥም የኳስ ቅብብሎሽ ሲያደርግ አልታየም፡፡ አሸናፊ ግርማ የሚታወቅበት የተሳኩ ረዥም ኳሶቹና ማራኪ አንድ ሁለት ቅብብሎቹ አብረውት አልነበሩም፡፡ የቡድኑ አጨዋወት እንዲጠፋ አድርጎታል፡፡ ከሀዋሳ ከነማ የተመረጠው የግራ መስመር አማካዩ ሽመልስ በቀለ ተፈጥሯዊ የኳስ ችሎታ እንዳለው ቢያስታውቅም ግራ አጋቢው የዋልያዎቹ አጨዋወት ከቡድን ይልቅ በግል ስራ ላይ እንዲያተኩር አድርጎት ነበር፡፡ በቦታ አያያዝ ከቀኝ መስመር ወደ ጐል ኳስ ይዞ እንዲገባ ኃላፊነት የተሰጠው የሙገሩ በዳሶ ሆራ ያገኛቸውን ነፃ ኳሶች በተቃራኒ ግብ ክልል ውስጥ ላሉ ባልደረቦቹ ለማድረስ ቢያሻግርም በኬኒያ ብ/ቡድን ተከላካዮች



ይመለሱበትና ወደ ውጪ ይወጡበት ነበር፡፡ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረው ከኢትዮጵያ ቡና ወደ የመን መዛወሩ የተረጋገጠው አጥቂው ታፈሰ ተስፋዬ ከቅርበትም ሆነ ከርቀት ወደ ጐል ሙከራዎችን ሲያደርግ ነበር፡፡

የኬንያው 11 ቁጥር አለን ዋንጋ በ11ኛው ደቂቃ ከግራ ክንፍ ከቅጣት ምት የተሻገረለትን ኳስ ከመረብ አሳርፏል፡፡ ጐሉ የተከላካዮች ሰው በሰው ያለመያዝና የበረኛው ቢኒያም ሀብታሙ የተቃራኒ ቡድን ነፃ ተጨዋቾችን ያለማስያዝ ችግር ታይቶበታል፤ ምክንያቱም አጥቂው ጐል ሲያገባ ብቻውን ነበርና ነው፡፡

በሁለተኛው 45 ደቂቃ የአማካይ ተከላካዩ ተስፋዬ አለባቸውን አስቀርቶ አስር ተጨዋቾች ለውጦ ወደ ሜዳ የገባው የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ይበልጡኑ ግራ ገብቶት ተመልካቹን ግራ አጋብቶት አምሽቷል፡፡ በሁለተኛው አርባ አምስት 11ኛ ደቂቃ ላይ ለሀራምቤ ስታርሶቹ ሁለተኛ ጐል አስገኝቷል፤ አግቢው አሁንም 11 ቁጥሩ አለን ዋንጋ ነበር፡፡ ለግቡ መገኘት የበረኛው ሳዳት ጀማል አስተዋጽኦ (ኳስ ይዞ መልቀቅ) ታክሎበታል፡፡ በ71ኛው ደቂቃ ሌቪ ሜሞካ ለኬንያ ሦስተኛ ጐል አስቆጥሯል፡፡ የሚገርመው ሦስቱም ግቦች የተገኙት ከቅጣት ምት ከተሻገሩ ኳሶች መሆኑ ኦሬም ኦኔራ በዚህ ላይ እንዲሰሩበት መልዕክት አስተላላፊ ሆኗል፡፡ በዚህ ክፍለ ጊዜ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን መለያ ወክለው ሜዳ ከገቡት ተጨዋቾች ውስጥ ጐልቶ ለመውጣት አይደለም ስለመኖሩ ሊታወስ የሚችሉ ተጨዋቾች አልነበሩም፡፡ በተለይ የአማካይ ክፍሉ በቦታ አያያዝና አጠባበቅ ላይ ተቸግረው ሲርመሰመሱ ነበር፡፡

በመከላከያና በደደቢት ቆይታው አሰልጣኝ የሚያለውን ከማድረግ ይልቅ በሚያምንበት አጨዋወት በመጓዝ ራሱን የሚያስደስው ዳዊት እስጢፋኖስ [ወደ ኢትዮጵያ ቡና ተዛውሯል]እንደ ሌሎቹ አማካዮች ሁሉ እሱም ሲባዝን ነበር፡፡

## እውነታና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ህዝብ ግንኙነት ያወጣው መግለጫ «ቡደኑ ያደረጋቸው ተደጋጋሚ ሙከራዎች ባይሳኩም ጥሩ እንቅስቃሴ ግን አድርጓል» ሲል ይገልፃል፡፡ መግለጫው እግር ኳስ ጨዋታን ማየትና የስራ ኃላፊነት ያላቸውን ልዩነት ያሳየ ይመስለኛል፡፡ ጨዋታው እኔም ሆነ አጠገቤ ለነበሩ የሙያ ጓደኞቼ አልገባንም ነበር፡፡ የመጀመሪያ ነው ብለን የወቀሳ አስተያየቶችን ከመለዋወጥ ተቆጠብን እንጂ፡፡ የፌዴሬሽኑ መግለጫ ግን ህዝብ ግንኙነት የእውነት ሳይሆን የማስታመም የግዴታ ስራ ያለበት አስመስሎታል፡፡ ነው ወይስ ዋሊያዎቹና ሐራምቤ ስታርስ ሌላ ጨዋታ አድርገው ነበር?

## አምላክን ያታልላሉ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ የተካተቱት ብዙዎቹ አዳዲስ ፊቶች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ብዙም የሚታወቁ አይደሉም፡፡ እንደ አሸናፊና ሳዳት አይነት ረዥም ዓመት የተጫወቱም ይገኙበታል፡፡ እንግሊዛዊው አሰልጣኝ በተለይ ስለ አንድ የቡድኑ ተጨዋች ባድናቆት ሲናገሩ የሰማ አንድ ጋዜጠኛ «ተሸወዱ» የሚል እምነት በመያዝ «የኢትዮጵያ እግር ኳስ ተጨዋቾች እንኳን አሰልጣኝን አምላክንም ያታልላሉ» ሲል ገልፆታል፡፡ አባባሉ እውነታ ያለው ይመስላል፡፡

## ሳይጀመር ተቃውሞ ለምን?

የኦፌም ኦኖራ ቡድንና ተጨዋቾች በዕለቱ ጨዋታውን ለመከታተል ከስታዲየም ከተገኘው ህዝብ በጨዋታው መሀከልና ከጨዋታው በኋላ የተቃውሞ ድምጽ ቀርቦባቸዋል፡፡ ገና በመጀመሪያ ጨዋታ መቃወም እግር ኳስ በእውቀት ሳይሆን በስሜት የሚመለከቱ ሰዎች የሚሰነዝሩት ነው፡፡ አዲስ አሰልጣኝ፣ አዲስ ተጨዋቾችና አዲስ ሜዳ በአንድ ቀን ይግባባሉ ብሎ መደምደም ስህተት ነው፡፡ ስህተቶች ካሉም መጠቆምና ማሳየት (በሚገኙ አጋጣሚዎች) ላይ ማተኮር ይገባል፡፡ የሚደግፉት ክለብ ተጨዋችን በተናጠል መደገፍም ይታይ ነበር፡፡

ደጅ ተጨዋቾቹ ወደ መኪና ሲገቡ ተቃውሞውን ያሰማው ስፖርት አፍቃሪ ለኬኒያዊያን ተጨዋቾች ያሳየውንና ፍቅር የተሞላበት ሽኝት ለአገሪሩ ልጆችም ሊነፍግ አይገባውም ነበር፡፡ የኬኒያ ብ/ቡድን በቅ/ጊዮርጊስ ክለብ ሰርቪስ አካባቢውን በነፃነት ሲለቁ ኢትዮጵያውያኑ ግን በፖሊስ መታጀብ ግድ ብሏቸው ነበር፡፡

## ሌላ አሳፋሪ ነገር

በዕለቱ የኢትዮጵያ ብ/ቡድን የለበሰው አረንጓዴ መለያ ቀለሙ ተቀራራቢ ይሁን እንጂ ሁለት አይነት ነበር፡፡ የአንዳንድ ተጨዋቾች የጀርባ ቁጥርም በፕላስተር ተሰምሮ ነበር፡፡ የመለያና የቁምጣ ቁጥራቸው የተለያዩ ተጨዋቾችም ነበሩ፡፡ ይህ በጣም አሳፋሪ ተግባር ነው፡፡ መሰረቷ አቅርቦት ባላሟላ ቡድን ፀጉር መንጨትና ተቃውሞ ድምጽ ማሰማት አይገባም ባይ ነኝ፡፡ ለነገሩ ጨዋታውም፣ የአገሪቷም እግር ኳስ ለአቅመ ማናደድ መቼ ደረሰና?

ከፌዴሬሽኑ ያገኘነው መረጃ ቡድናችን ነሐሴ 30 የጊኒ አቻውን ከመግጠሙ በፊት ኬኒያን በአገሯ፣ ደ/አፍካንና ቻድን ደግሞ ጋብዞ ወይም ሄዶ ለመግጠም ጥረት ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ መልካም ዕድል!!!

# ህልም ብቻ እንዳይሆን...

በዓለም ላይ የመሳሪያ እሽቅድድም እንዳይኖር በማሰብ ድርጅቱ ለማህበራዊ ኑሮ የሚያገለግሉ እቃዎች እንዲያመርት የገንዘብ እርዳታ ለገሰ፡፡ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የገንዘብ እርዳታውን ተቀብሎ በፋብሪካው ጥይት ማምረትን ትቶ የሙከራ ምርት ሜዳሊያ ማምረት ሲጀምር ጦርነቱ ፈነዳ፡፡ አዲስ አበባ ያሉት ባለ ስልጣናት «በሀገር ምርት እንኩራ» የሚል አዲስ ብሂል ስላመጡ ጥይት ማምረታቸውን ቀጠሉ፡፡ ዋሽንግተን ፋብሪካው የጦር መሣሪያ እንዳያመርት ለማሰናከል ያወጣችው ወጪ ከሰረ፡፡ ከብሩ ይልቅ እኛን ያናደደን ፋብሪካው የጦር መሣሪያ ማምረቱ ነው፡፡

«እስራኤላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ ኢትዮጵያዊ መልኩን፣ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይቀይራል ከማለት ኢትዮጵያዊ ተንኮሉን እባብ መርዛምነቱን መተው ያቅተዋልን? ቢል ጥሩ ነበር፡፡ ...

«ዴቪድ ለነሱ ጥሩ አመለካከት የለህም»

«እንዴት ይኖረኛል? የአሁኖቹ ባስልጣናት ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት ስቴት ዲፓርትመንት ተጠርተው መመሪያ ሲሰጣቸው ነበርኩ፡፡ ሰዎቹ ያን ሽምቅ ውጊያ መሪዎች ነበሩ፡፡ የተሰጣቸው መመሪያ ሕዝቡን በብሔር መለያየት...» በማለት በብሔር፣ በባንዲራና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትችቱን የሰላ ትችቱን ያቀርባል፤ መመሪያዎች ከምዕራባዊያን ዘንድ ስለመላኩ በመተንተን፡፡

«አሁን ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆኑት ሰው ሰንደቅ አላማውን ጨርቅ ብለው በአደባባይ እንዲሳለቁ ያደረጋቸው፡፡ ... መንግስት ሕዝቡን በዘር ቢከፋፍለውም ሕዝቡ ግን አልተከፋፈለም፡፡...» ይህን ስመለከት ኢትዮጵያ ውስጥ በነፃነት እንዲህ አይነት መፅሐፍት በመታተማቸው እንድገረም አድርጎኛል፡፡ ሌላው፣ የደራሲው ድፍረታዊ አፃፃፍ እውነት ያለውን ከማሳየት ባለፈ ይህን መሰል አፃፃፍ የተከተሉ በዝናም ሆነ በገንዘብ ተጠቃሚ መሆናቸውን ተመልክቶ ይሆን? የሚል ጥያቄ እንዳጭርም አድርጎኛል፡፡

መጽሐፉ ሌላው ይዞ የተነሳው የኒኮሌር ጉዳይ ነው፡፡ ኒኩሌር ለጦር መሳርያ ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ለልማትም የሚያገለግል የኃይል ምንጭ ነው፡፡ ይህን የኒኩሌር ፕሮግራም ኢትዮጵያ መስራት ስትሞክር የሚገጥማትን እንቅፋቶች እንዴት እንደምትወጣ መጽሐፍ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ከዚህ በፊት ብዙ የውጪ ሃገር የስለላ መጽሐፍት አንብበናል፡፡ «ያልተፈታው ህልም» መጽሐፍን ሳነብ ሃገራችን ውስጥም የስለላ መፅሐፍ መፃፍ እንደተቻለ እንደተቻለ ያሳየ ይመስለኛል፡፡

በመፅሐፉ ላይ አንዳንድ ስህተቶችን ተመልክቻለሁ፡፡ በመደበኛ የኑሮ ሂደት ላይ የሚታወቁ ሰዎች ከነ ሙያ መደባቸው ማስቀመጡ ልብ-ወለድ ከሚለው ፅንሰ ሀሳብ ጋር በመጠኑ ያፈነገጠ ይመስላል፡፡ የመጽሐፍ የፊት ሽፋኑ ላይ ከላይ የደራሲው ስም ሰፍሯል፡፡ ይህም የመፅሐፉ ርዕስ «ሕዝቅያስ ፀጋዬ» ነውን ያስብላል፡፡ የመጽሐፍ ርዕስ ከግርጌ በቅጡ በማይነበብ ጽሁፍ (Font Style) ሰፍሯል፡፡ በተለምዷዊ የርዕስ ቦታ ላይ ስምን ማስፈር ለየት ለማለት ለማሰብ ነው ከማለት ይልቅ ደራሲውን ለስሙ መጨነቁን ያሳያል፡፡ ማንም አንባቢ ከርዕሱ ይልቅ ቀድሞ የደራሲውን ስም ለማንበብ ይገደዳል፡፡ ስሙ እና የርዕስ ቦታ ቢቀያየሩ ኖሮ የገጽ ሽፋኑ የበለጠ ያምር እንደነበር አስባለሁ፡፡ የስርዓተ ነጥብ አጠባበቅ ችግርም አልፎ አልፎ በመፅሐፉ ላይ ተመልክቻለሁ፡፡


አንድ የመጽሐፍ ምስል የመጽሐፍን ታሪክ 30% ከገለፀ እድለኛ ነው ይባላል፡፡ ይህ መፅሐፍ ግን ከዚያ በበለጠ መልኩ እንደገለፀ እረዳለሁ፡፡ መጀመሪያ መፅሐፉን ሽፋን ስለመከተው ለሽያጭ የተደረገ መስሎኝ ነበር፡፡ ነገር ግን መጽሐፉን ስጨርስ መጽሐፉ ላይ ያለው ምስል «ገላጭ ነው» ብያለሁ፡፡

«ያልተፈታው ህልም» መጽሐፍ ህልም ብቻ እንዳይሆን እመኛለሁ፡፡ እኛኑ የሚመለከት የስለላ ጽሑፍ ስለተፃፈ ደራሲውን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ ደራሲው በመፅሐፉ መግቢያ «...ይህ መጽሐፍ የኔን አመለካከት የሚያራምድ ነው፡፡ ማንንም ለመጥቀም ሆነ ማንንም ለመጉዳት ታስቦ የተፃፈ አይደለም፡፡ ... በሙሉ የእኔ የደራሲው እምነት ናቸው፡፡ ሊያስጠይቁኝ ወይም ሊያስቀጡኝ ከቻሉ ሁሉንም ነገር በፀጋ እቀበላለሁ፡፡...» ይላል፡፡ ለሃገራችን የስነ-ጽሁፍ እድገት እንደ ሕዝቅያስ ያሉ ደፋር ፀሐፊዎች ያስፈልጋሉ፡፡ በድፍረት ውስጥ እውነት አይተናል፡፡ በስም ባይጠቀሱም የሃገራችን ባለ ስልጣናት አስተሳሰባቸውን ገምተናል፡፡ በስም የተጠቀሱ ቁልፍ ባለስልጣናትም መጽሐፉ ውስጥ አሉ፡፡ ልብ ወለድ መሆኑ ሳይረሳ ማለት ነው፡፡

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ማስታወቂያ




# የመጭው አምስት ዓመት. . .

የሚሰሩ ሰራተኞችም ከሕገ መንግስት ማዕቀፍ ውጭ አይደሉም። ሆኖም የሚያከናውኑት ተግባር የራሳቸውን የፖለቲካ አስተሳሰብና አላማ ማራመጃ ካደረጉት ፍጹም ውጉዝ የሆነ ተግባር ነው። በመሆኑም ሰራተኞቹ በውድድር እና በችሎታ ቢቀጠሩ እና ተቋሙ ሁሉንም ወገን በእኩል አይን ለማስተናገድ ያስችለው ዘንድ ይበልጥ ገለልተኛ ቢሆን የተሻለ ይሆናል። ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ግን ተቋሙ የሀገሪቱን እድገት ለማፋጠን ከሚሰጠው ግልጋሎት ይልቅ የሰነፎች ዋሻ በመሆን የሀገሪቱን ጥሪት ለመመዝበር ለሚንቀሳቀሱ ሀይሎች እንደ የእዝ ማዘዣ ሆኖም ሊያገለግል ይችላሉ። በተጨማሪም ሰራተኞቹ ከብቃትና ወርድ መለኪያ በዘለለ በፖለቲካ ወገንተኝነት እና ባላቸው አመለካከት የሚቀጠሩ ከሆነ ፖለቲካን የድክመታቸው መለኪያ ካባ አድርገው ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ አትኩሮት ሊሰጠው ይገባል።

## ጠንካራ መድብለ ፓርቲ ሥርዓት

በአንድ ሀገር ውስጥ ጠንካራ የሆነ የመድብለ ፓርቲ ስርአት መኖር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት እሙን ነው። የዚህ ስርአት መኖር በሀገሪቱ ውስጥ ለሚኖረው መራጭ ሕዝብ በርካታ አማራጫችን ከማቅረቡ በተጨማሪ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት እንከኖች ለመራጩ ህዝብ ለማጋለጥ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል።

ነገር ግን በአንድ ሀገር ውስጥ የብዙ ፓርቲዎች መኖር በራሱ የመድብለ ፓርቲ ስርአት መኖርን በአርግጠኝነት አያመላክትም። በአንድ ምርጫ ወቅት በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሳተፋቸውን ብቻ አይተን ምርጫውን «የመድብለ ፓርቲ ምርጫ» ብለን ለመጥራት የተጣደፍን እንደሆነ ልንሳሳት እንችላለን።

በመሆኑም መድብለ ፓርቲ ስርአት ብለን ስንናገር ህዝቡ በሙሉ የኔ ነው ብሎ የተቀበለው ሕገ መንግስት ከግለሰቦችም ሆነ ከሌሎች በላይ ሆኖ የሚከበርበት ስርአት ሲሆን፣ በዚህ ሕገ መንግስታዊ ስርአት የተለያዩ ፓርቲዎች የተለያዩ ፕሮግራሞቻቸውን ይዘው በክልሎች ውስጥም በሚደረጉ ምርጫዎች የሚሳተፉበት ነው። የምርጫውም አላማ ሕዝብ ከቀረቡለት የተለያዩ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አማራጮች ይሻለኛል ብሎ የተስማማበትን ፕሮግራም ያነገበን ኃይል መርጦ የመንግስት ስልጣን እንዲይዝ ማድረግ ነው። ይህ በህዝብ ፈቃድ ስልጣን ላይ የወጣ ኃይል ደግሞ የተመረጠበትን ፕሮግራም ከስራ ላይ ለማዋል ፖሊሲዎች እየቀየሰ በሕገ መንግስቱ ተወስኖ በተሰጠው የስልጣን ዘመን ያገለግላል። ስርአቱ፣ የመንግስት ፕሮግራሙ በህዝብ ተቀባይነትን ያጣ እንደሆነ ሕዝብ ስልጣን ላይ እንዲወጣ እንዳደረገው ሁሉ ከስልጣን ለማውረድም የሚያስችለው ጭምር ነው። ሌሎች በህዝብ ይሁንታን አግኝተው መመረጥ ያልቻሉ ኃይሎች በተቀዋሚነት ታውቀውና ተከብረው የተቃውሞ ትግላቸውን ለመቀጠል የሚያስችላቸውን መንገድ ሁሌም የሚያመቻች ሥርዓት ነው - የመድብለ ፓርቲ ስርአት።

ለመሆኑ በአገራችን ጠንካራ የመድብለ ሥርዓት አለ? የተቃውሞ ኃይሎችስ ለህዝብ በአማራጭነት የሚያገለግሉ ኃይሎች ናቸውን? የፖለቲካ አየሩስ ጠንካራ መድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለመፈጠር የተመቻቸ ነውን? ከላይ ላነሳኋቸው ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ማግኘት የተቻለ እንደሆነ እናስፈጽመዋለን ብለን ለተነሳነው አላማ አጋዥ የሚሆነን ሲሆን ምላሻችን በተቃራኒው ከሆነ ደግሞ እረጅም እርቀት መጓዝ የምንችል አይመስለኝም።

የሀገራችንን ነባሪዊ ሁኔታ ስንመለከት በአሁኑ ሰዓት ከ90 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉ ይታወቃል። በመሆኑም እነኝህ በርካታ የፖለቲካ ቁጥር ያለቸው የፖለቲካ ኃይሎች እንወክላለን ብለው ለቆሙለት ህዝብ እንደቁጥራቸው ሁሉ በርካታ አማራጮችን አቅረበው በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት መቆጣጠር ብሎም እንከኖቹን ለህዝብ ማድረስ የሚችሉ ከሆነ እውነትም መድብለ ፓርቲ ስርአት አለ ብለን ደፍረን ለመናገር ያስችለናል።

ነገር ግን ቀደም ብዬ እንዳስቀመጥኩት የበርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ሀገር ውስጥ መኖር መድብለ ፓርቲ ስርአትን አያመለክትም። ይልቁንም የህዝብ ድምጽ በመከፋፈል ምክር ቤት የሚገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች አናሳውን የሕብረተሰብ ክፍል ብቻ እንዲወክሉ የሚያደርግ ነው። ለዚህ አይነተኛ ሚና የሚጫወተው የሀገራችን የምርጫ ስርአት ነው፡ በዓለማችን በጥቅም ላይ ከሚውል ሁለት የምርጫ ሥርዓቶች፣ ማለትም አብላጫ የድምጽ ሥርዓት (Majority Representation System) እና ተመጣጣኝ ውክልና (Proportional Representation System)፣ መካከል ሀገራችን የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ንዑስ የሆነውን የከፍተኛ ድምጽ ሥርዓት ትጠቀማለች። በዚህ ሥርዓት አንድ ተወዳዳሪ አሸናፊ ለመሰኘት የግድ ከሌሎች አቻ ተወዳዳሪዎች የበለጠ የመራጭ ድምጽ ማግኘት አለበት። ይህንን ሀሳብ በምሳሌ ላጠናክረው፤ በአንድ «ለ» ተብሎ በሚጠራ የምርጫ ጣቢያ ስምንት ለውድድር የቀረቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩዎች አሉ እንበል። በዚህ ጣቢያ ከተወዳደሩት መካከል ሰባቱ አስር አስር በመቶ የመራጮች ድምጽ ቢያገኙ፣ አንደኛው ብቻ ተወዳዳሪ ሰላሳ በመቶ ድምጽ ይኖረዋል ማለት ነው። በዚህ ስሌት መሰረት የሰባ በመቶ ድምጽ ውህ በልቶት የሰላሳ በመቶ ብቻ ድጋፍ ያለው አካል ምክር ቤት ይገባል ማለት ነው። ይህ ችግር ለምርጫ የቀረቡ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር በጨመረ ቁጥጥር በዚሁ መጠን ይባባሳል።

ታዲያ ምን ይደረግ? አንድ የጋራ የሆነ አገራዊ ራዕይ ለመከወን የምናስብ ከሆነ በሀገራችን ውስጥ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከመፍጠር ይልቅ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊፈጠሩ የሚችሉበት መንገድ ትኩረት መስጠት፣ የፖለቲካ ኃይሎች፣ በተለይም በተቃዋሚው ጐራ የተሰለፉት፣ እርስ በእርሳቸው በመከፋፈልና እራሳቸውን ለድክመትና ለመበጣጠስ አሳልፈው በመስጠት ከጐናቸው ሊሰለፍ የሚችለውን ህዝብ ቅስም ከመስበር መቆጠብ ወሳኝ ናቸው። የጠንካራ መድብለ ፓርቲ ሥርዓት መኖር ለመንግስት የሚጠቅም ነውና የፖለቲካ ኃይሎች እንዲዳከሙ ከማድረግ ይልቅ የሚጠናከሩበትን ስልትና መንገድ ቢያመቻች በሀገራችን ጠንካራ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መስርተን ያሰብነውን ከዳር ማድረስ ይቻለናል።

## ሙስናን መዋጋት የሚችል አመራር

በርካታ የጥናትና ምርምር ውጤቶች ይፋ እንዳደረጉት፣ ሙስና አብዛኛውን ህዝብ ለከፋ ድህነት ከመዳረግ አልፎ የሰውን ልጅ ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል ነው። ሙስና አንድንድ አገራት እስከመበታተን የሚያደርሳቸው አደጋ ሲጋርጥ ታይቷል። በመሆኑም የእነዚህ ወንጀሎች መበራከት የሰው ልጅን ህልውና አደጋ ላይ እንደሚጥለው አያጠራጥርም። በመሆኑም ሙስና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ብለን መክፈል የሚያስችሉንን ጉዳቶች ያስከትላል።

በኢኮኖሚ ጉዳቱ ረገድ ያየን እንደሆነ ሙስና ልማት እንዲቀጭጭ፣ የአገር ኢኮኖሚ እድገት እንዲገታ፣ ኪሳራና ውድቀት እንዲፋጠንና ድህነት በከፈተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ ያደርጋል። ይልቁንም እንደኛ ላለ የማያላውስ የኢካኖሚ አቅም ላላቸው አገሮች ችግሩ ከድጡ ወደ ማጡ ይሆናል። የሙሰናን ማህበራዊ ጉዳቶች ስንመለከት ደግሞ በህዝቦች ዘንድ የሞራል ውድቀት፣ የሥነ-ምግባር ቀውስና የሕግ የበላይነት አለመከበር እንዲሰፍን በድረግ ክፉኛ ከባድ ማሕበራዊ ቀውስ (ስራ አጥነት፣ ጉዳና ተዳዳሪነት፣ ዋልጌነት፣ ጥፋተኝነትና ሥርዓት አልበኝነት፣ ሴተኛ አዳሪነት ወዘተ) መፈጠርን ያስከትላል። ሙስና በሰፈነበት ሀገር በዋነኛነት ሰፌው ህዝብ የችግሩ ተጠቂ በመሆኑ በሚጋጥመው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ ብዙሀኑ ለድህነት ይዳረጋል። ሰርቼ የተሻለ ኑሮ እኖራለሁ ብሎ የሚመኘው ህዝብ ሰርቶ የመኖር ምኞቱን በማጨለም ከፍተኛ የሞራል ውድቀት እንዲደረስበት ያደርጋል። በዚህም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የህብረተሰብ ክፍል ለስራ አጥነት እጅግም ሲከፋ ለስደት እንዲዳረግ ምክንያት ይሆናል።

የሙስናን ፖለቲካዊ ችግር ስንመለከት ደግሞ ህዝብ በመንግስትና በሕግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣና በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በማድረግ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲሰፍን ያደርጋል። በመጨረሻም የሙስናን ከባቢያዊ ጉዳቶች ስንቃኝ የስግብግብነት ስሜትን አግንኖ ስለሚያወጣ የተፈጥሮ ሚዛንን የሚያዛበ ተግባሮች መፈፀሙን ጨምሮ የሰውን ልጅ የመኖር ህልውና የሚፈታተኑ ድርጊቶች ያስከትላል። በመሆኑም ይህ ድርጊት ከቀጠለ አንዲት ሀገር እንደ ሀገር መዝለቅ አዳጋች የሚሆንባት ደረጃ ላይ ልትደርስ ትችላለች።

ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች የከፋ የሚያደርጋቸው የሙስና ወንጀሉ የሚፈጸመው በአመራሩና ሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች የሆነ እንደሆነ ነው። በተለይም በሥልጣንና በአመራርነት ላይ ያለው አካል ሥልጣኑንና የአመራር ቦታውን ለሀገራዊና ህዝባዊ አገልግሎት ተግባር ከማዋል ይልቅ ለእለታዊ የዳቦ ፍጆታ የሚያውለው ከሆነ ችግሩ የከፋ ይሆናል።

ወደ ሀገራችን ነባሪዊ ሁኔታ ስንመጣ ትራንስፓረንስ ኢንተርናሽናል የተባለው ድርጅት ጥናት እንደሚያመላክተው ኢትዮጵያ አደገኛ የሆነ የሙስና ችግር ካለባቸው አገራት መካከል የምትጠቀስ መሆኗመን አስቀምጧል። በሥልጣን ላይ ያለው መንግስትም ቢሆን ሙስና የሥርዓቱ ዋነኛ ተግዳሮት መሆኑን አሌ አይለውም።

ረጅም ርቀት መጓዝ የምንፈልግ ከሆነ ሙስናን በመዋጋትና ሥልጣንን ከእለታዊ የዳቦ ፍጆታ በዘለለ በሀገርና ለወገን ግልጋሎት ለማዋል ቁርጠኛ መሆንንም ይጠይቃል። በተለይም መንግስትና ገዥው ፓርቲ በአመራር ላይ ያሉ አካላት ሙስናን በመዋጋት ረገድ ቁርጠኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቤት ስራውን ከራሳቸው ቢጀምሩ የተሻለ ይሆናል።

## ጠንካራ አገራዊ ስሜትን መፍጠር

በአንድ ሀገር ላይ የጋራ የሆነ አላማ ይዞ ከግቡ ለመድረስ የሀገሪቱ ዜጎች ልዩነቶቻውን ወደጐን በመተው አንድነታቸውንና የጋራ የሆኑ እሴቶቻቸውን በማጐልበት ወደፊት መገስገስ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የዓለም አገራት የሥልጣኔ መረዳት የምንችለውም ይህንኑ ነው። ለአገር እድገት ጠንካራ የሆነ አገራዊ ስሜት መፍጠር ጠቃሚ መሆኑን ከጃፓን የተሻለ አርአያ ሊሆነን የሚችል ህዝብ አይኖርም። ጃፓን ከድህነት ተላቃ በአሁኑ ሰዓት በኢኮኖሚ አንቱ ከተባሉ አገራት ግንባር ቀደም ለመሆን የበቃቸው አንድነት ኃይል መሆኑን አምነውና የጋራ ራዕይ ሰንቀው መንቀሳቀስ በመቻላቸው ነው።

እኛም ኢትዮጵያውያን ከጃፓን ልንወስደው የሚገባን ተሞክሮ ይኖራል። እንደ ጃፓን ህዝቦች መደጋገፍና በአገር ጉዳይ ላይ ያሉንን ልዩነቶች አስወግደን መተባበር ከቻልን ያቀድነውን የማናሳካበት ምንም ምክንያት የለም። በታሪካችን ክንዳችን አንድ የሆነው በጠላት ላይ እንደሆነና መቼም ቢሆን በሌሎች ልማታዊ ጉዳዮች ላይ አንድ ሆነን የማናውቅና ልንሆንም እንደማንችል በብዙ ጸሀፊዎች ተተችተናል፤ የራሱ የሆነ እውነትነት ያለው ትችት ነው። ክንዱን በጠላት ላይ አስተባብሮ ዳር ድንበሩን ማስከበር የቻለ ህዝብ እንዴት እድገትን ለማምጣት፣ በርሀብ የሚንገላታውን ምስኪን ህዝብ በልቶ እንዲያድር ለማድግ እንዴት ተሳነው?

በመሆኑም አገር ታድግ ዘንድ፣ ህዝቡ ጠግቦ ያድር ዘንድ፣ ከበርካታ አካላት ብዙ ይጠበቃል። በመጀመሪያ ደረጃ ህዝቡ በራሱ ቁጭት ሊያድርበትና የአገሩ ስቃይ ሊጠዘጥዘው ይገባል። በመሰረቱ የአገራችንን ችግር ህመም የሚያመን ከሆነ፣ የአገራችን ጉዳት የጐን ውጋት ሆኖ የማይወጋን ከሆነ፣ ለመፍትሄው እንረባረባለን ማለት ዘበት ነው። በመሆኑም አንድ በሚያደርገን አገራዊ ጉዳይ ላይ አንድ በመሆን ህብረታችንንና የጋራ መግባባታችንን ማጠናከር ይጠበቅብናል።

# መንፈሳዊ አባቶች. . .

ሁኔታ እንድትፈታ እየጠየቁ ባለበት ሁኔታ፣ የሃይማኖት አባቶቻችን ግን አንድም ቃል ሲተነፍሱ አልሰማንም። ደፍረው አራት ኪሎ ያሉ ባለሥልጣናትን ለማናገርም ሆነ ለመገሰጽ አልደፈሩም። ይልቅስ ይግረመንና ከኢህአዴግ ባለሥልጣናት ጎን ተቀምጠው፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ያልሆነው ምርጫ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማገዝ መግለጫዎች ሲሰጡ ነው የሰማናቸው። የምናየው ለራሳቸው ክብር ሃውልት ሲያቆሙ ነው።

ከሶስት ሺህ አመታት በፊት በእሥራኤል መንፈሳዊ መሪ የነበሩት ሊቀ ካህኑ ኤሊና ሁለት ካህናት ልጆቹ ፊንሃስና አፍኒን ነበሩ። ፊንሃስና አፍኒን በቀን የካህን ካባ ለብሰው መሥዋእት ያቀርባሉ። በማታ ግን ታቦቱ ባለበት በመቅደስ ውስጥ ያመነዝራሉ። የእግዚአብሄር ቃል ፍጹም በነዚህ አገልጋይ በሚባሉ ሰዎች ዘንድ የተናቀ ነበር።

እግዚአብሔር መሃሪ አምላክ ነው። ነገር ግን መጽሃፍ እንደሚለው የሚባላ እሳትም ነው። የእግዚአብሄር ምህረት ታላቅና ዘላለማዊ ብትሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ይቺ ምህረት አይዘበትባትም። በመሆኑም ያኔ በኤሊ ዘመን የእግዚአብሔር የፍርድና የቁጣ በትር ወረደች። በአንድ ቀን ፊንሃስን አፍኒን ተገደሉ። አባታቸውም ኤሊ፣ የልጆቹን መሞት ሲሰማ መጽሐፍ «ኤሊ በቅጥሩ በር አጠገብ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ በጀርባው ወደቀ፤ እርሱም ያረጀ ሰውነቱም የሚከብድ ስለነበር፣ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ» እንደሚለው ደንግጦ ወድቆ ሞተ። እግዚአብሄር እራሱ የነዚህ አደባባይ ካህናት ፍጻሜ ደነገገ።

የእግዚአብሔርን ቃል ንቀው፣ የራሳቸውን ክብር ለሚፈልጉ፣ በእግዚአብሔር ስም ለሚነግዱ፣ የተቀመጡበትን የተከበረ መንገድ ለሚያቀሉና ጥቅማቸውን ለሚያሳድዱ የዘመኑ የአገራችን የሃይማኖት አባቶች «ዋ» እላለሁ። ለድሃና ለተገፋው የሚያስበው የዘላለም አምላክ እግዚአብሄር የፍርድ በትሩን በርግጥ የሚያነሳበት ጊዜ ይመጣል። ለነርሱም ክብር ያሰሩት ሃውልት ናቡከደነጾር በሕልሙ እንዳየው ምስል፣ ወይንም በደርግ ግዜ በአይናችን እንዳየነው እንደ ቭላድሚር ሌኒን ሃውልት ይፈራርሳል።

በሊቀ ካህኑ አሊ ምትክ፣ በፈሪሃ እግዚአብሄር የተሞላ፣ የእግዘብሄርን ፊት በትህትና የሚፈልግ፣ ለእውነት የቆመ፣ ፍትህን የማያዛባ፣ የሃናና የሕልቃና ልጅ ሳሙኤል እንደመጣ ሁሉ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በእግዚአብሔር ቃል የሚያቀኑ፣ የኦስካር ሮሚሮና አርተር ሱሌማኖቭ አይነት ሃቀኛ፣ አይበገሬ፣ ታማኝ የእግዚአብሄር ባሪያዎችን እግዚአብሄርም ይሰጠናል። ያንን ጊዜም ያፍጥንልን!

# ይህቺ አገር. . .

ያለው ሜዳ ነበር። አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል እንዲሉ ሜዳው ወደ ጥልቅ ጉድጓድነት ሲለውጥ መቦረቂያቸውን የተነጠቁት የፒያሳና የአካባቢዋ ወጣቶች ወደጫት አመንዣኪነት ተቀይረዋል፣ ያሳዝናል። ወደፊት ኢትዮጵያ የምትከፍለው ዋጋ ሲታየኝ እንቅልፍ አጣለሁ።

ከበርቴው ሼሕ አላሙዲን ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ቢገነቡም ለወጣቱ ምኑም አይደለም። ህሊና፣ ቅን ልቦና ቢኖር የፒያሳና አካባቢዋን ነዋሪ ወደሌላ ስፍራ በማንቀሳቀስ ለልማት የተፈለገውን ቦታ መውሰድ ይቻል ነበር። የተደረገው ግን ይሄ አይመስለኝም። ሜዳው ለባለ ኃብቱ ሲሰጥ ለወጣቱ ምን ታስባለታል ብሎ የጠየቀ ያለ አይመስለኝም። ሻጭም ገዥም አልተጨነቁም። አይ የኔ ነገር፣ ወደ ሌላ ሀሳብ ወሰድኳችሁ መሰለኝ። ይቅርታ። አሁን ወደተነሳሁበት ነጥብ ልመለስና መልእክቴን ልቋጭ።

የአዲስ ባንክ ከታጠረ እነሆ አስራ አንድ ዓመት በላይ ሆነው መሰለኝ። ልብ በሉ! ከአፄ ምኒልክ አደባባይ ወደታች ስትወርዱ ከሜዳው በስተግራ በኩል የአውቶብስ ማቆሚያና ማቋረጫ የነበረ መንገድ ነበር። በልማት ስም አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ታጥሮ ይገኛል። ይሄን ለማረጋገጥ የፈለጉ እንቁላልና ዶሮ በሚሸጡበት በር በኩል ማየት ይችላሉ። ይሄ መንገድ ከ11 ዓመት በላይ በመዘጋቱ በአካባቢው ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ይታያል። አሁን ደግሞ ይባስ ብለው ዙሪያውን በሌላ የተጠናከረ አጥር አንድም የእግረኛ መንገድ ሳይተርፍ እያጠሩ ይገኛሉ። ኧረ ጎበዝ ይህቺ አገር የማን ናት?

ይህቺ አገር - ኢትዮጵያ - የእነንግስት ሕንደኬ፣ አፄ ካሌብ፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዩሀንስ፣ እምዬ ምኒልክ፣ አፄ ኃይለስላሴ፣ ኮሎኔል መንግስቱ፣ የአቶ መለስና ጓደኞቻቸው፣ ሌሎችም ሌሎችም ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች የተዋደቁላት አገር ናት። በክፉም ሆነ በበጎ ስራቸው፣ የቀድሞዎቹም ሆኑ የአሁኖቹ ገዢዎች በታሪክ ፍርድ ላይ የሚቀመጡ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ግን እስከ ወዲያኛው ድረስ ለኢትዮጵያውያን ትሆናለች ብዬ በማሰብ ልሰናበት።

/አቶ ደረጀ መላኩ የሰብአዊ መብት ጉባኤ አባል ሲሆኑ፣ በአንጋፋው ኢመማ የድሬዳዋ መምህራን የቀድሞ ፕሬዝደንት (ተጠሪ) ነበሩ/



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# 4.5%

## ከፍተኛ የወለድ መጠን በዘመን ባንክ!

ዘመን ባንክ በአሁኑ ጊዜ ከብር 25,000 በላይ በቁጠባ ሒሳብ ለሚያስቀምጡ ደንበኞቹ በሙሉ 4.5% ወለድ ይከፍላል። ይህም ሌላ ቦታ ከሚከፈለው 4.0% ወለድ መጠን ከፍ ያለ ነው።

የምንከፍለው የወለድ መጠን በሚያስቀምጡት የቁጠባ ሒሳብ የገንዘብ መጠን ልክ ከፍ የሚል ይሆናል።

ከብር 100,000 በላይ ገንዘብ ካስቀመጡ የ4.75% ወለድ ያገኛሉ።

ከብር 500,000 በላይ ገንዘብ ካስቀመጡ የ5.0% ወለድ ያገኛሉ።

በተጨማሪ በባንካችን ሂሳብ ለሚከፍቱ ደንበኞች በሙሉ፣

ለ"ATM" መጠቀሚያ የሚያገለግል ነፃ ዴቢት ካርድ (Debit Card) ያገኛሉ።

በኢንተርኔት ድረ-ገጽ ነፃ የባንክ አገልግሎት ያገኛሉ።

በስልክ ነፃ የባንክ አገልግሎት ያገኛሉ።

**የዚህ ሁሉ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ስለሚችሉ፣**
**ገንዘብዎን ወደ ዘመን ባንክ አሁኑኑ ለማዛወር ችላ አይበሉ!**

Bank Hours: 8:00 am – 7:00 pm Monday Friday / 8:00 am – 5:00 pm Saturday

Zemen BANK
ዘመን ባንክ
www.zemenbank.com

Zemen Bank S.C.
Tel +251 11 553 90 40
Fax +251 11 553 90 42
info@zemenbank.com
Joseph Tito Street
Addis Ababa, Ethiopia

Financial Solutions from A to Z
ለ የ ነ ታ ች ን . . . ዘ መ ና ዊ ነ ታ ች ን


ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com